# የቅማንት ማህበረሰብ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ

በ

አብነት ሰለሞን

የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከፊሉን
ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ታህሳስ 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የቅማንት ማህበረሰብ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ

በ

አብነት ሰለሞን

አማካሪ

ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከፊሉን

ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ታህሳስ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## የቅማንት ማህበረሰብ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ

በ

አብነት ሰለሞን

ታህሳስ 2005 ዓ.ም

### የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

______________________ ______________________
አማካሪ ፊርማ

ቴዎድሮስ ገብሬ ______________________
ፈታኝ ፊርማ

______________________ ______________________
ፈታኝ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

# አበርክቶ

የዚህ ስራ መታሰቢያነት ጥናታዊ ስራው ተፀንሶ እስኪወለድ ድረስ ሲያማክሩኝ ቆይተው በነገራዬ (defence) ማግስት ላለፉት ታላቅ ሰው ለዶክተር ዮናስ አድማሱ ይሁን።

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ አማካሪዬ፣ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ በማማከርና ጠማማውን በማቃናት ላደረጉልኝ ከፍተኛ እገዛ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል ይህን ትምህርት እንድማር ሙሉ ወጪዬን የሸፈነልኝን የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን ከልብ አመሠግናለሁ፡፡ ከዚህም ባሻገር ይህን ጥናት ለማከናወኛ የሚሆነኝን ወጪ የሸፈነልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን በጣም አመሠግናለሁ፡፡ ይህ ጥናት ያለ መረጃ አቀባዮቼ ባዶ ነው፡፡ ስለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ መረጃ ላቀበሉኝ ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በተለይም ወንበር ሙሉነህ መርሻ፣ ቄስ አማረ ሙሉነህ፣ ነጋ ጌጤ፣ አቶ ተስፋ አቦ፣ አቶ አዲሱ ታረቀኝ፣ ወ/ሮ ማታ ቸኮል፣ አቶ ዘርጋው ነገሰ፣ አቶ ስዩም ውንድይፍራው፣ ወ/ሮ አቡኔ ነጋ፣ አቶ ካሳ በለጠ፣ አቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ፣ አቶ አስራት ቢለው፣ ወ/ሮ የሺእመቤት ይርዳው፣ መምህር አለማየሁ በላይ፣ ቄስ አየልኝ ተሰማ፣አቶ አበይ መኮንን፣ አቶ አበራ ታከለና ወ/ሪት ዘመናይ አበራ ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር ሳላመሰግናችሁ አላልፍም፡፡

ማሞዬ (ዳዊት ሠለሞን) እንደ ልጅነታችን ከኋላ ከኋላዬ እየተከተልክ በጭልጋና በትክል ድንጋይ እንዳንሸበራሉ የተንከራተትከው ወንድሜ እግዚአብሔር ጉልበትህን (ልጅህን) ይባርካት፡፡ እመ ማህደረ ዳዊት መሲ፣ መረጃ ለመሰብ ሰብ በመ ጣሁ ቁጥ ር እየተንከባከብሽና ስንቅ እየቋጠርሽ ስለቸኝ ሳትይ አስተናግደሽኛልና ማህደረን ይባርክልሽ፡፡

ያንተን ሥራና ትምህርት ወደጐን በመተው የጭን ላይ ኮምፒውተርህን (Lap Top) እያዋስክ ለስራዬ መሳካት ከፍተኛ እገዛ ያደረክልኝ ትንሹ ወንድሜ አቡዬ (ሶፎንያስ መ/ማሪያም) እደግልኝ፡፡

በሃሳብና በሞራል የምታበረታኝና የመኖሬ ሚስጥር፣ የስኬቴ ሁሉ ምክንያትአባቴ ሰለሞን ታደሠ እግዚአብሔር እድሜህን ያርዝመው፡፡ እማዬ ቀን ሙሉ ቁጭ ብዬ መፅሀፍ ሣገላብጥ “እይዞህ ጠንከር በልና ዳር ድረስ” የምትይኝ የልፋቴን ፍፃሜ ልናይ ወር ብቻ ሲቀር “እናንተ በርቱ እኔ ልሂድ” ብለሽ የተለየሽኝ አያቴ እግዚአብሔር ነፍስሽን በገነት ያኑራት፡፡ ጋሽ ስንታየሁ ከነቤተሰብህ ያደረክልኝን ውስጣችን ያውቀዋልና ፈጣሪ ልጆችህን ይባርክልህ ፡፡

ጋሽ አብርሃም አለሙ መፅሀፍ በማዋስና ይህን ርዕስ በምን መንገድ ብሠራው መልካም እንደሚሆን በመጠቆም ላደረክልኝ እገዛ ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

በመጨመረሻም ስራዬ ከዳር ይደርስ ዘንድ ላበረታችሁኝ ለአንቢኮ ጃርሳ፣ እየሩሳሌም ካሳሁን፣ እንዳልካቸው መኮንን፣ አንዳርጋቸው ታዲዎስ እና ስማችሁን ዘርዝሬ ለማልጨርሰው ጓደኞቼና የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ iii
አጠቃሎ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.2 የጥናቱ አላማ ........ 2
1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 3
1.6 የመረጃ አሠባሰብ፣ የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ አቀባዮች ንሞና ........ 3
1.6.1 የመረጃ አሠባሰብና የአጠናን ዘዴ ........ 3
1.6.2 የመረጃ አቀባዮች ንሞና ........ 4
1.7 ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ........ 5
1.7.1 ቅድመ ዝግጅት ........ 5
1.7.2 የመስክ ክንውን ........ 5
1.8 በጥናቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 9
ምዕራፍሁለት ........ 11
የተዛማጅ ጥናቶች እና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ........ 11
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 11
2.2 የንድፈሀሳቦችቅኝት ........ 22
2.2.1 ቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral prose narrative) ........ 23
2.2.1.1 የቃላዊ ዝርው ተረክ ምንነት ........ 23
2.2.1.2 የቃላዊ ዝርው ተረክ ተግባር ........ 24
2.2.2 ማንነት (Identity) ........ 25
2.2.3 ማንነትና ተረክ (Identity and narrative) ........ 26
2.2.4 ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional approach) ........ 27
ምዕራፍ ሦስት ........ 29
የቅማንት ማህበረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ........ 29
3.1 የቅማንት ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ ........ 29

3.2 የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋና ሃይማኖት ........ 32
3.2.1 የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋ ........ 32
3.2.2 የቅማንት ማህበረሰብ ሀይማኖት ........ 35
3.3 የቅማንት ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ሁኔታ ........ 37
3.4 የቅማንት ማህበረሰብ መተዳደሪያ (ምጣኔ ሃብታዊ ሁኔታ) ........ 37
ምዕራፍ አራት ........ 38
በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ስለማንነት የሚነገሩ ዝርው የቃል ተረኮች ትንተና ........ 38
4.1 የቅማንት ማህበረሰብ ሀይማኖታዊ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ........ 38
4.1.1 የሀገልቦና እምነት መሪዎች ........ 39
4.1.2 የሀገ ልቦና አምላክ ........ 42
4.1.3 ሀገልቦናና ቃላዊነት ........ 48
4.1.4 የፀሎት ስፍራ ........ 49
4.1.5 የሀገልቦና ጥንታዊነትና ሀገር በቀልነት ........ 51
4.1.6 በሀገልቦና እምነት ለመብላት የተከለከሉ ነገሮች ........ 52
4.2 የቅማንት ማህበረሰብ የበአላት መከበር ምክንያት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ........ 53
4.2.1 ምዝገናና ግበሩህ ........ 54
4.2.2 ሽምኩላ (ከረመይኪኩና) ........ 54
4.2.3 የዳኒቃ በአል ........ 56
4.2.4 የዘመን መለወጫ በአል ........ 57
4.2.5 የደመራ በአል ........ 59
4.3 የቅማንት ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታ በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ........ 61
4.3.1 የጋብቻ ዘር ቆጠራ ........ 61
4.3.2. ማርኮዛ ........ 62
4.3.3. የጋብቻ እድሜ ........ 62
4.3.4. ሁለተኛ ጋብቻ ........ 63
ምዕራፍ አምስት ........ 65
ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ ........ 65
5.1 ማጠቃለያ ........ 65
5.2 የይሁንታ ሃሳብ ........ 67
ዋቢ ጽሑፎች ........ 69
አባሪ

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የቅማንትን ማህበረሰብ ዝርው የቃል ተረኮች በመተንተን በተረኮቻቸው ማንነታቸውን እንዴ ት እንደሚገነቡና እንደሚገ ልፁ የሚያ ሳይ ነው፡፡ በጥናቱ ስለቅ ማንት ማህበረሰብ አካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታ አጠቃላይ ገፅታ ተዳሷል፡፡ ከማህበረሰቡም ዝርው የቃል ተረኮች ተሰብስበዋል፡፡

የተሰበሰቡትን ተረኮች መነሻ በማድረግ የማህበረሰቡን ማንነት በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም ሃይማኖታዊ ማንነት፣ በአላትና የጋብቻ ሁኔታ ናቸው፡፡ የማህበረሰቡ አብዛኛው ክፍል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ (ከ1950ዎቹ መጀመሪያ) የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነትን የተቀበሉ ቢሆንም በአሁኑም ወቅት ቢሆን የቀደመ እምነታቸውን (ህገልቦናን) ይዘው የሚኖሩ የማህበረሰቡ አባላት አሉ፡፡ በዚህ ጥናት በሐይማኖታዊ ማንነት ስር ትንታኔ የተደረገባቸውም ተረኮች ከነዚህ የህገልቦና እምነት ተከታዮች የተሰበሰቡት ናቸው፡፡ በተረኮቹ መነሻነትም በህገልቦና እምነት አለምን ሁሉ የፈጠረው ምዝገና ሲሆን እሱ በመብረቅ ከድንግል ሴት የወለደው አይደረኪ ደግሞ የሃይማኖታዊ ክንውኖቻቸው ሁሉ መሠረት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የቅማንት ማህበረሰብ ከሌሎች አጎራባቾቹ በአላትን በሚያከብርባቸው ምክንያቶችና የጋብቻ ሁኔታው ይለያል፡፡ ማህበረሰቡ ከአማራው በተለየ ምክንያት ከሚያከብራቸው በአላት ውስጥ ምዝገናና ግበሩህ፣ ሽምኩላ (ከረመይኪኩና)፣ ዳኒቃ፣ ዘመን መለወጫና ደመራ ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡ የጋብቻ ሁኔታቸውንም በተመለከተ በጋብቻ ዝር ቆጠራቸው፣ በጋብቻ እድሜያቸውና በሁለተኛ ጋብቻ ስርአታቸው ከአማራው የተለዩ ሲሆኑ ማርኮዛም (በግንባር ላይ መስንጠብ) የቅማንቶች መገለጫ ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በቅማንት ማህበረሰብ ዝርው የቃል ተረክ ትንተና ላይ ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ ማንነቱን በተረኮች ይገነባል፤ ይገልፃልም፡፡ ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ዝርው የቃል ተረክ በማጥናት ማህበረሰቡ ስለራሱ ያለውን አመለካከት ማወቅ ይቻላል፡፡ የማህበረሰቡን ተረክ በማጥናትም የማህበረሰቡን ሃይማኖታዊ ማንነት፣ ታሪካዊ ማንነት፣ ባህላዊ ማንነትና መሠል መገለጫዎቹን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናትም የማህበረሰቡን ዝርው የቃል ተረክ በመሰብሰብ የማህበረሰቡን ሃይማኖታዊ ማንነትና ባህላዊ ማንነት ለመመርመር ይሞከራል፡፡

ከዚህ ቀደም በቅማንት ማህበረሰብ ዙሪያ የሥነ-ልሳንና የስነሰብዕ ተመራማሪዎች ጠንካራ ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡ ከነዚህም የዘላለም እና የ C-Gamst ስራዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ስራዎች ትኩረት የሚያደርጉት ቋንቋንና አጠቃላይ የማህበረሰቡን ሁኔታ (እንዳቀማመጣቸው በቅደም ተከተል) ነው፡፡ ስለዚህ ተረክ መሠረተ ነገራቸው አይደለም፡፡ የእኔ ጥናት ግን ተረኮችን ሰብስቦ ማህበረሰቡ ማንነቱን በተረኮቹ እንዴት እንደሚገልፅ ማሳየት ነው፡

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተቀነበበ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ማዕቀፍ (framework) የሚያስተዋውቁ ስምንት ንዑሳን ርዕሶች ተካተዋል፡፡ እነሱም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሠባሰብና የአጠናን ዘዴዎች፣ ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ናቸው፡፡

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የንድፈ ሃሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሠፍረዋል፡፡ በምዕራፍ ሦስትም የማህበረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ የሠፈረ ሲሆን በምዕራፍ አራት ደግሞ ከማህበረሰቡ የተሠበሰቡ ተረኮች ተተንትነዋል፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍም የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብሠፍረዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማከናወን ያነሳሳኝ ዋነኛ ምክንያት በአንድ ወቅት ወንድሜን ለመጠየቅ ጐንደር ሄጄ ከሱ ጋር ለሽምግልና ወደ ጭልጋ እንደሄድኩ ያጋጠመኝ ነገር ነው። ለሽምግልና የገባንበት ቤት ውስጥ እጅግ በጣም ውብ የሆነች ሃይማኖት የኔነህ የምትባል ልጅ ቡና ስታፈላ ተመለከትናትና ሽምግልናውን ጨርሰን ስንወጣ እኔም ወንድሜም በጣም እንደምታምር አወራን። አብሮን ከጐንደር ለሽምግልና የሄደውና ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው ሦስተኛው ሽማግሌ፣ "ምን ዋጋ አለው ይህን ጊዜ ቅማንት ናት" አለን። እኛም የማናውቀው ነገር ስለነበር፣ "ቅማንት ምንድን ነው?" ብለን ጠየቅነው። እሱም ስለ ቅማንት ምንነት የጐንደር አማራ የሚለውን አጫወተን። የዚህ ጊዜ ይህ ማህበረሰብ ደግሞ ራሱን ማን ነኝ ይላል የሚለው ጥያቄ በውስጤ ተፈጠረ።

ከዚህ በተጨማሪ ለትምህርት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመጣሁበት ወቅት የተጠኑ ጥናቶችን ሳስተውል የቅማንት ማህበረሰብ በዝርው የቃል ተረኮቹ ማንነቱን እንዴት እንደሚገነባና እንደሚገልፅ የሚያሳይ ጥናት አለማግኘቴ ለጥናቴ ሌላው አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል።

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ተቀዳሚ ዓላማ የቅማንት ማህበረሰብ የሚናገሯቸውን ዝርው የቃል ተረኮች ከሚነገሩበት ስፍራ ሰብስቦ ማንነትን ከመገንባትና ከመግለፅ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መተንተን ነው። በዚህ አብይ ዓላማም ስር የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖራሉ።

- የተረኮቹ ተግባር ምን እንደሆነ እመረምራለሁ።
- በተረኮቹ የሚነሱ ዋና ዋና የማህበረሰቡ ማንነቶች ምን ምን እንደሆኑ እመለከታለሁ።
- ተረኮቹን በማጤን የማህበረሰቡን እምነት (ሃይማኖት)፣ ታሪክና ባህል እፈትሻለሁ።

## 1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

የጥናቱን አላማዎች ከዳር ለማድረስ በጥናቱ ሂደት ውስጥ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሠጣል።

- የተረኮቹ ተግባር ምንድን ነው?
- በተረኮቹ የሚነሱ ዋና ዋና የማህበረሰቡ ማንነቶች ምን ምን ናቸው?
- በተረኮቹ መሠረት የማህበረሰቡ እምነት፣ ታሪክና ባህል ምንድን ነው?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ስለ ቅማንቶች በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የተሠሩ ምርምሮች የሌሉ ስለሆነ ለወደፊት በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ይህን ማህበረሰብ ለማጥናት ለሚሻ ተመራማሪ ይህ ጥናት እንደመነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፡-

- የቅማንትን ማህበረሰብ ያስተዋውቃል፤
- የቅማንትን ማህበረሰብ የቃል ተረኮች ከሌላው ማህበረሰብ የቃል ተረኮች ጋር ለማነፃፀር ያግዛል፤
- የማህበረሰቡ አባላት በተረኮቻቸው ሃይማኖታቸውን፣ ታሪካቸውን፣ ባህላቸውንና በአጠቃላይ ማንነታቸውን እንዴት እንደሚገነቡና እንደሚገልፁ ጥናቱ ስለሚያሳይ ይህን ጥናት ለሚያነብ አካል ቅማንቶች ሃይማኖታቸውን፣ ታሪካቸውን፣ ባህላቸውንና በአጠቃላይ ማንነታቸውን በተረኮቻቸው እንዴት እንደሚገልፁ ግንዛቤን ይፈጥራል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በቅማንት ማህበረሰብ ዝርው የቃል ተረክ ትንተና ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህም የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች የቅማንት ማህበረሰብ አባላት ብቻ ይሆናሉ፡፡ ምንም እንኳን የቅማንት ማህበረሰብ አባላት በተለያዩ ቦታዎች ሊገኙ የሚችሉ ቢሆኑም የዚህ ጥናት መረጃ የተሠበሠበው ከጭልጋና ከትክል ድንጋይአካባቢዎች ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በሌላ አካባቢ የሚኖሩት የማህበረሰቡ ተወላጆች የተቀላቀሉበትን ማህበረሰብ ማንነት ሊጋሩ በመቻላቸው ነው፡፡

የጥናቱ ፍሬ ነገር የሆነው ዝርው የቃል ተረክ በተለያየ አቅጣጫ የሚጠና ቢሆንም በዚህ ጥናት ግን ዝርው የቃል ተረኮቹ ማንነትን ከመገንባትና ከመግለፅ አንፃር የሚያበረክቷቸው ተግባራት ብቻ ይጠናሉ፡፡

## 1.6 የመረጃ አሠባሰብ፣ የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ አቀባዮች ንሞና

### 1.6.1 የመረጃ አሠባሰብና የአጠናን ዘዴ

የዚህን ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ሰፊ የድምፅ ቀረፃ፣ ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ (informal interview) እና ምልከታ (observation) ተከናውኗል፡፡የመረጃ አቀባዮቹ ተረኮቹን ሲተርኩ

በመቅረፀ ድምጽ ተቀርፀዋል። ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያዬም ይሄው ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በድምፅ ቀረፃው ወቅት በሚተርኳቸው ተረኮች ዙሪያ ለሚፈጠሩብኝ ጥያቄዎችና ማብራሪያ ለሚያስፈልጓቸው ጉዳዮች ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ ተጠቅሚያለሁ። ሌላው ምልከታ ነው። በፎክሎር ጥናት ውስጥ ክዋኔ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር እንደሆነ (Finnegan, 2005:87) ይገልፃሉ። አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በተለያየ ክዋኔ ውስጥ የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል። በመሆኑም የአንድን ፎክሎራዊ ቅርፅ ትክክለኛ ትርጓሜ ለማግኘት ክዋኔውን ማጤን ተገቢ ነው። ለዚህ ደግሞ ምልከታ አይነተኛ መሣሪያ ነው።

ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን ተግባራዊ አቀራረብን ተጠቅሜያለሁ። ይህን አቀራረብ አስመልክቶ በምዕራፍ ሁለት ላይ በስፋት ተገልጧል።

### 1.6.2 የመረጃ አቀባዮች ንሞና

የናሙና አመራረጡ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የማህበረሰቡን ባህል፣ ሃይማኖትና አጠቃላይ ሁኔታዎች ያውቃሉ ተብለው የተጠቆሙ ሰዎችን በመምረጥ ተካሂዷል። ከዚህም በተጨማሪ የፆታና የእድሜ ልዩነት የተለያየ መረጃን ሊያመጣ ይችላል በሚል ስጋት ከሁለቱም ፆታዎች በተለያየ የእድሜ ክልል ያሉ መረጃ አቀባዮች በጥቆማ ተመልምለዋል።

ከመረጃ አቀባዮቹ ውስጥ አስራ ስድስቱ ቁልፍ የመረጃ ሠጪዎች ሲሆኑ አራቱ ደግሞ አጋዥ መረጃዎችን ያቀበሉ ናቸው። ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ለጥናቱ የሚያስፈልጉ በርካታ መረጃዎችን የሠጡኝ ናቸው። ቁልፍ የተሠኙትም ለዚህ ነው። የተቀሩት ግን አንዳንድ ክፍተቶችን ለመሙላትና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የረዱኝ ናቸው።

ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች በጭልጋና በላይ አርማጭሆ ወረዳዎች በሚገኙ አራት ቀበሌዎች (አይከል፣ ተበር ሚካኤል፣ ትክል ድንጋይና ከርከር/ማንጌ) ብቻ የሚገኙ ሲሆን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ግን ስለቅማንት ማህበረሰብ የጠለቀ እውቀት እንዳላቸው የተጠቆሙኝን የማህበረሰቡ ተወላጅ የሆኑ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የቅማንት ማህበረሰብ ማንነቱ ይታወቅልኝና ራስ አገዝ በመሆን እንደ አንድ ብሔረሰብ ዕውቅና ይሠጠኝ ብሎ ያነሳውን ጥያቄ በበላይነት የሚመሩና በጐንደር የሚኖሩ አጋር የመረጃ አቀባዮች ናቸው። እነዚህ የመረጃ አቀባዮች ቁልፍ የመረጃ

ሠጪ ያልሆኑበት ምክንያት የጥናቱ ወሰን በሆነው በጭልጋም ሆነ በትክል ድንጋይ እየኖሩ ያሉ ሳይሆን መኖሪያቸው በጐንደር ከተማ በመሆኑ ነው፡፡

## 1.7 ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

### 1.7.1 ቅድመ ዝግጅት

ወደ መስክ በመሄድ መረጃ ለመሰብሰብ ከመነሳቴ በፊት ጥሩ መረጃ ሰብስቤ እመጣ ዘንድ የሚያስችለኝን የእውቀት ስንቅ ለማዘጋጀት በማህበረሰቡ ዙሪያ የተፃፉ የተለያዩ የጥናት ዘገባዎችን፣ የታሪክ መፃህፍትን፣ መፅሄቶችንና የመሳሰሉትን ቤተመፃህፍት በመግባትና ከተለያዩ ስፍራዎች በመፈለግ አንብቤያለሁ፡፡ በዘርው የቃል ተረኮች ዙሪያም ከተሠናዱ ምርምሮችና መፃህፍት የተወሰኑትን አንብቤያለሁ፡፡ በምርምር ዘገባዎች ረገድ በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሠናዱትን አንብቤያለሁ፤ አጠናቅሬያለሁም፡፡

ከዕውቀት ዝግጅቴ ባሻገርም ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች ከሚገኙባቸው ስፍራዎች ገዝቻለሁ፤ ተውሻለሁም፡፡

### 1.7.2 የመስክ ክንውን

ቅድመ ዝግጅቴን ካጠናቀኩ በኂላበመጋቢት ሁለት 2004 ዓ.ም ወደ ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ መዲና፣ ጐንደር ጉዞዬን ጀመርኩ፡፡ ለጉዞ የመረጥኩት መኪና ሠላም አውቶብስ ስለነበር በዚያው ዕለት ከአመሻሹ 11፡45 ሰዓት ጐንደር ከተማ ደረስኩ፡፡ ጐንደር ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምር ወንድም ስለነበረኝ አውቶብስ ተራ ጠብቆኝ ተያይዘን ወደቤቱ አመራን፡፡ በምን ርዕስ ጉዳይ ላይ እንደምሠራና መረጃውን ከየት አካባቢ ልሰበስብ እንደምችል ማምሻችንን ለወንድሜ አጫወትኩት፡፡ ወንድሜ የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ የሆኑ የስራ ባልደረቦቹ ጋር ስልክ ደውሎ በማግስቱ እንገናኝ ዘንድ ቀጠሮ አስያዘልኝ፡፡

በማግስቱ ሰኞ 3/7/2004 ዓ.ም የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ከሆኑ ሁለት የስራ ባልደረቦቹ ጋር ተገናኘሁ፡፡ ከነሱም ጋር የተለያዩ ነገሮችን ተወያየን፡፡ በተለይ ማህበረሰቡ ቢጠየቅ ወይም ቢያነሱበት የማይፈልጋቸውን ጉዳዮች ጠየኳቸው፡፡ እነሱ ግን ምንም ችግር እንደሌለና ለጥናቱ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ያሻኝን ጥያቄ መጠየቅ እንደምችል ነገሩኝ፡፡

ማክሰኞ 4/7/2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 12:30 ሰዓት ከወንድሜ ጋር ወደ ጭልጋ (አይከል ከተማ) ተጓዝን፡፡ ለዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የሆነችኝ ያልኳት ልጅ ቤተሰቦች ጋር ሄድን፡፡ ስንደርስም እቤት ውስጥ ያገኘናት እሷን ብቻ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ የፈለኩት አባቷን ነው፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ራሳቸውም የመረጃ ምንጭ ይሆኑኛል ሲቀጥልም ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር ያገናኙኛል ብዬ ነበር፡፡ ነገር ግን ልጅቱ/ሃይማኖት/ አባቷ ቅማንት እንዳልሆኑና ስለ ቅማንትም ምንም ሊነግሩኝ እንደማይችሉ ነገረችኝ፡፡

ከዚያም ጉዟችንን ከአይከል ከተማ ወጣ ብላ ወደምትገኘው የወንበር ሙሉነህ መንደር ተበር ሚካኤል አደረግን፡፡ እዚያ እንደደረስንም ቤታቸውን ጠይቀን ወደ አጥር ግቢያቸው እንደተቃረብን ውድማ ዳር ያለች የብሳና ዛፍ ጥላ ስር ቁጭ ብለው የሚያጠኑ ሁለት ልጆችን አገኘን፡፡ እድሜያቸው በግምት ከ14-16 ዓመት ይሆናል፡፡ አባ ወንበር ሙሉነህ መርሻን ፈልገን የመጣን መሆናችንን ነገርናቸው፡፡ እነሱም አባ ወንበሩ ፀበል ለመፀበል ልጃቸውን ቄስ አማረን ይዘው ወደ አንዘመርኩም ፀበል የሄዱ መሆናቸውንና ሣምንት ሊቆዩ እንደሚችሉ ነገሩንና ወደ አይከል ከተማ ተመለስን፡፡

በዚሁ ዕለት ከረፋዱ 4:00 ሰዓት ሲሆን የጭልጋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ ክልሉ ያስጠናቸውን አንዳንድ ጥናቶች ተመለከትኩ፡፡ የጭልጋ ወረዳን ካርታም ወሰድኩ፡፡ ከወንድሜ ጋር ከተማ ውስጥ ስንዘዋወር ወንድሜ አስተምሮት የነበረ አንድ መምህር አገኘን፡፡ ከዚያም የመጣሁበትን አላማ አስረዳሁት፡፡ እሱም ቅዳሜ ተመልሼ ብመጣ ገበያ ላይ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት እንደምችልና በዕለቱም እሱም እንደሚረዳኝ ቃል ገብቶልኝ ከሰዓት በኋላ ወደ ጉንደር ተመለስን፡፡

የቅማንት ማህበረሰብ በብዛት ሠፍሮ የሚገኝበት ሌላው ወረዳ ላይ አርማጭሆ እንደሆነ ስላነበብኩና ስለሰማሁ ረቡዕ 5/7/2004 ዓ.ም በጠዋት ወደ ትክል ድንጋይ ከወንድሜ ጋር ተጓዝኩ፡፡ እዚያም የወንድሜ ጓደኛ አባት፣ አቶ አበራ ታከለ ስለነበሩ ወደዚያው አመራን፡፡ እሳቸው የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ናቸው፡፡ ምሳችንን እየበላን ብዙ ወግ አወጉን፡፡ እኔም ለምን እንደመጣሁ ነገርኳቸው፡፡ እሳቸውም ከሰዎች ጋር ሊያገናኙን ይዘውን ወጡ፡፡ መጀመሪያ የሄድነው ወ/ሮ ማታ ቸኮል ጋር ነበር፡፡ ከኝህ ሴት ጋርም በርካታ ነገሮችን ተጨዋወትን፡፡ከጭውውታቸውም አምስት ተረኮችን አገኘሁ፡፡ ከዚያም አመስግነን ወጣንና ወደ

አቶ ካሳ በለጠ ጋር ሄድን። እሳቸውም እቤት ስላልነበሩ ወደ አቶ አስራት ቢለው ጋር ሄድን። ሻይ ተፈልቶልን እየጠጣን ወጋችንን ቀጠልን። የመጣሁበትን አላማ አስረድቼ አንዳንድ መረጃዎችን እንዲነግሩኝ ጠየኳቸው። ከሳቸው ጋርም በግምት ሁለት ሰአት ያህል ተጨዋውተን ወጣን። በመጨረሻም አቶ አበራ ቅዳሜ ተመልሼ ብመጣ ብዙ ሰዎችን እንደሚያገናኙኝ ነገሩኝ። እኔም ቅዳሜ ጭልጋ ሰው የቀጠርኩ መሆኑን ገልጬ ለእሁድ ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

ሀሙስ አቶ ነጋ ጌጤን ለማነጋገር ጐንደር፣ ፒያሳ የሚባል ሠፈር ሄድኩ። ከሳቸው ጋርም ምን እንደምፈልግ ነግሬያቸው፣ "የምትፈልጋቸውን ነገሮች በጥያቄ መልክ አዘጋጅና አምጣ" ስላሉኝ እንደዚያው ለማድረግ ተስማምቼ ወጣሁ። አምባሣደር ዘመነ ካሰኝ የሚባሉ ሰውም ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡኝ እንደሚችሉ ስለተጠቆምኩ በዚያን እለት በተደጋጋሚ ላገኛቸው ብጥር አልተሳካልኝም።

ሀሙስ ማምሻዬን አቶ ነጋን ልጠይቃቸው የሚገቡኝን ጥያቄዎች ሳዘጋጅ አመሸሁና አርብ 7/7/2004 ዓ.ም ጠዋት 2:30 ሰዓት አቶ ነጋ ጌጤን አገኘኋቸው። እኚህ ሰው በጣም የተረጋጉ፣ ለሰው ትልቅ ክብር ያላቸው፣ ታሪክ አዋቂና መልከመልካም ሰው ናቸው። ንግግራቸው ሳቢ ነው። ከኚህ ሰው ጋር ከ2:30-6:00 ሰዓት ድረስ ብዙ ቁምነገሮችን ተጨዋወትን። ከዚያም ስላገኘኋቸው የተሠማኝን ደስታ ገልጬላቸው ተለያየን።

ቅዳሜ 9/7/2004 ዓ.ም እኔና ወንድሜ በጠዋት ወደጭልጋ ተጓዝን። የወንድሜ ተማሪ የነበረው መምህር አለማየሁ በላይ ጋር ደወልንና አግኝተነው መዞር ጀመርን። እሱም ቀጠሮ አሲይዞልን የነበራቸውን ሰዎች አገናኘን። ከነዚህ ሰዎች ጋር ለአራት ሰአታት ያህል ስንወያይ ከቆየን በኋላ 8:45 ከአይከል ዳርቻ ወደምትገኘው የወንበር ሙሉነህ መንደር ተጓዝን። ነገር ግን ወንበር ሙሉነህም ሆኑ ልጃቸው ቄስ አማረ ከሄዱበት ፀበል አልተመለሱም። በኋላም ተመልሰን ወደ ጐንደር መጣን።

በማግስቱ 10/7/2004 ዓ.ም ጠዋት 1:00 ሰዓት ላይ ትክል ድንጋይ ደረስን።ከዚያም ወደ አቶ አበራ ቤት አመራን። አቶ አበራ ግን በቤት አልነበሩም። ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ነበር። እስኪመለሱ ከተማ ውስጥ እየተዘዋወርን ቆየን። በቤተክርስቲያን ዙሪያ ያሉ የኔብጤዎችን (ለማኞችን) አንዳንድ ነገሮችን አነጋገርን። በዚህ እለት 4:00 ላይ ወደ አቶ አበራ ቤት ተመለስን። አቶ አበራ መምጣታችንን ስለሰሙ ምግብ ሳይበሉ እየጠበቁን ነበር። ስንመጣም

ምግብ ቀረበ መጀመሪያ እንደወጋችን ተግደረደርንና ሲቆጡን መብላት ጀመርን። ተመግበን እንደጨረስን ቀጠሮ ወደ አስያዙልን አምስት ሰዎች ጋር ወሰዱን። እነሱንም ለሶስት ሰአታት ያህል ስናናግር ቆይተን ከሰዓት በኋላ 8:30 ወደ ጐንደር ተመለስን።

ከሰኞ እስከ አርብ (10/7/2004 ዓ.ም - 14/7/2004 ዓ.ም) ድረስ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በፈርጅ በፈርጅ ሠደርኳቸው። ከዚያም ጥያቄ የሆኑብኝን በማስታወሻ አሠፈርኩ።

እሁድ 16/7/2004 ዓ.ም የቅማንት ማህበረሰብ፣ "እንደ አንድ ብሔረሰብ እውቅና ይሠጠን" የሚል ጥያቄ ለአማራ ክልል አቅርበው ስለነበር በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሊወያዩ በአይከል ከተማ እንደተቃጠሩ በመስማቴ በማለዳ አይከል ከተማ ገባሁ። የስብሰባ አዳራሽ ገብቼ ስብሰባውን በመቅረፀ ድምፅ እቀርፅ ዘንድ እንዲፈቀድልኝ የስብሰባውን አስተባባሪዎች አስፈቀድኩ። ስብሰባውም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 6:30 ሰዓት ነበር። ስብሰባው እንዳበቃ ወደ አባ ወንበር ሙሉነህ መርሻ ቤት ሄድኩ። እዚያም የነሱ የበአል ቀን ስለነበር ቅዳሴ ናቸው ተባልኩ። ከዚያም እስከ8:00 ሰአት ጠበቅንና 8:00ላይ ወደ ወንበር ሙሉነህ ቤት ሄድን። ግቢው ውስጥ አራት ውሾች ነበሩ። ውሾቹ እጅግ ሃይለኞች ናቸው። እኔና ወንድሜ ተደናግጠን ከአጥር ላይ እንጨት ስንመዝ "ተዉ" ተባልን። በጣም ስለፈራን ከውጪ ቆምን። ከዚያም የወንበር ሙሉነህ ልጅ መጥቶ ይዞን ገባ።

ከቤታቸው አጠገብ ካለ ነፋሻማ ቦታ ላይ ከከብት ቆዳ (ጠፍር) የተዘጋጁ ወንበሮች ወጡልንና ተቀመጥን። እዚያም ወንበር ሙሉነህና ልጃቸው ቄስ አማረ መጡ። ከነሱ ጋር ከአራት ሰዓት በላይ ስንጫወት ቆየን። ጭውውታችንን ስንጨርስ 12:50 ሰዓት ሆኖ ነበር። ወደ ከተማ ስንሄድ ትራንስፖርት ስላጣን እዚያው አይከል አደርን።

ከ17/7/2004 ዓ.ም - 21/7/2004 ዓ.ም ድረስ በጐንደር ከተማ ውስጥ ያሉ የማህበረሰቡ ተወላጆችን በማፈላለግ አንዳንድ አጋዥ መረጃዎችን ስሰበስብ ቆየሁ።

ቅዳሜ 22/7/2004 ዓ.ም ጠዋት ወደ ጭልጋ በመሄድ በአይከል ከተማ ዙሪያ ካሉ የገጠር ቀበሌዎች ዝንጅብል ለመሸጥ ወደ ገበያ የመጡ የተለያዩ ሰዎችን አገኘሁ። እዚያው ገበያ ውስጥም የተለያዩ ጥያቄዎችን እያነሳሁ ብዙ ተጨዋወትን። ከዚያም ከሰዓት በኋላ ገበያቸውን ገብይተው ወደ ቤታቸው ከመመለሳቸው በፊት ጠላ ወደሚጠጡባቸው ቤቶች እየገባን አብረን

እየጠጣን ስንጫወት ቆየን። ጠላ ቤት የነበረን ጨዋታም በጣም የተፍታታ ስለነበር በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችን እንዳገኝ እረድቶኛል።

በቤተክርስቲያን ዙሪያ ያሉ ተረኮችን መሰብሰብ ፈልጌ ስለነበር የዚያን ቀን እዚያው አድሬ እሁድ 23/7/2004 ዓ.ም በ12:00 ሰዓት ወደ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሄድኩ። እዚያም ቅዳሴ እስኪያበቃ ከኔብጤዎች ጋር ስወያይ ቆይቼ ቅዳሴው ሲያበቃ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ሰበሰብኩ። ከረፋዱ 5:00 ሰዓት ላይም ወደ ጐንደር ከተማ ተጓዝኩ።

በ24/7/2004 ዓ.ም ያገኘኋቸውን መረጃዎች በመልክ በመልካቸው ካደራጀሁ በኋላ መጋቢት 30/2004 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

በጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም ከአማካሪዬ ጋር በመመካከር ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ጭልጋና ከርከር ተመልሼ በመሄድ ተጨማሪ መረጃዎችን ቃርሜያለሁ።

መቶ አለቃ ጥጋቡ የሚባሉ የማህበረሰቡ አባል በአይከል እንደሚገኙና ስለማህበረሰቡ ብዙ ነገር እንደሚያውቁ ስለተጠቆምኩበጥቅምት 17፣ 2005 ዓ.ም ጠዋት 2:00 ሰዐት አይከል ደረስኩ። ጠዋት ስብሰባ ስለነበረባቸው ከስድስት ሰዐት ጀምሮ እስከ አስር ሰአት ተኩል ድረስ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ተወያየን። እኝህ ሰው ብዙ ነገሮችን የሚያውቁና እጅግ ግልጽ ናቸው።

በሳምንቱ እሁድ (24/02/2005) ወደ ከርከር ተጓዝኩ። ከርከር በመኪና እስከግንድ መጣያ ድረስ ከተሄደ በኋላ የአንድ ሰዓት ተኩል የእግር ጉዞ ተሄዶ የሚገኝ ቀበሌ ነው። በዚያ ቀበሌ ባለችና ማንጌ በተሰኘች መንደር ውስጥ አበይ መኮንን የተባሉ የዘጠና አመት እድሜ ያላቸው አዛውንት እንዳሉ ስለተነገረኝ ነበር ወደዚያች መንደር ያቀናሁት። ከአድካሚውና ውጣውረድ ከበዛበት የእግርጉዞ በኋላ ከአባባ አበይ ቤት ስደርስ አዛውንቱን ያገኘኋቸው ቅቤ ተቀብተው ፀሀይ እየሞቁ ነበር። ከኝህ አዛውንት ጋር ከ 2:30 ሰዓት እስከ 5:00 ሰዓት ገደማ ከተጨዋወትኩ በኋላ የአንድ ሰዓት ተኩል የእግር ጉዞዬን መልሼ ተያያዝኩት።

## 1.8 በጥናቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህ ጥናት ተወጥኖ እስኪቋጭ ድረስ አንዳንድ ችግሮች ገጥመውኝ ነበር። ከነዚህም ውስጥ ክለሳ ድርሳናትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሳደርግ የ“IES” ቤተ መፃህፍት ጠዋት ከ2:30 ሰዓት

በፊት አለመከፈትና ከሰዓት በኋላም በ11:00 መዘጋት አንዱ ችግር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ቤተመፃህፍት ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ "ካሌንደር" የሚዘጋቸውን የበአል ቀናት ዝግ በመሆኑ በቤተመፃህፍቱ የሚገኙ መረጃዎችን እንደልብ እንዳላገኝ እንቅፋት ሆኖኝ ነበር፡፡

ይህንንም ችግር ለመቅረፍ በመፍትሔነት የተጠቀምኩት ያልታተሙትን ጥናታዊ ፅሁፎች ፎቶ ኮፒ አድርጎ ማውጣት የማይፈቀድ በመሆኑ በስራ ቀናት እነዚህን ጥናቶች በማንበብ መረጃ የወሰድኩ ሲሆን መፅሀፍቱን ግን ፎቶ ኮፒ በማድረግ ከስራ ሰዓት ውጪ እቤቴ በመሆን መረጃዎችን ለመውሰድ ችያለሁ፡፡

ሌላው ችግር መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሄድኩ ጊዜ መረጃ አቀባዮችን ወዲያው አለማግኘት ነበር፡፡ ይህ ችግር ገጥሞኝ የነበረው ማህበረሰቡን ከዚህ በፊት የማላውቀው በመሆኑ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ለዚህም የወሰድኩት የመፍትሄ እርምጃ ወንድሜ የሚያስተምርበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉን የማህበረሰቡ ተወላጆች መተዋወቅ ነበር፡፡ ከዚያም እነሱ ለተለያዩ (ጭልጋም ሆነ ትክል ድንጋይ ለሚኖሩ) የማህበረሰቡ ተወላጆች የመጣሁበትን አላማ ገልፀው ደብዳቤ ስለፃፉልኝ ሰዎችን እንደ ልብ ማግኘት ችያለሁ፡፡

በችግርነት የሚነሳው ሌላው ጉዳይ በጀት ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ጥናታዊ ስራውን ጀምሮ ለመጨረስ የበጀተው ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ገንዘቡ መረጃ ሰብስቦ ለመምጣት እንኳን የማይበቃ ነበር፡፡ ነገር ግን ከቤተሰቦቼና ከጓደኞቼ በተደረገልኝ ድጎማ ጥናቱ ከዳር ደርሷል፡፡

ወንበር ሙሉነህና ቄስ አማረ የተባሉት የህገልቦና እምነት ተከታዮች መንደር ስሄድ ውሾቻቸው ሊበሉኝ ሲመጡ ለመከላከል አጥራቸውን መዝዤ "በትርክን ጣል በትር አይያዝም፡፡" ሲሉኝ ውሾቹን ፈርቼ ስለነበር ከአጥራቸው ላይ የመዘዝኩትን እንጨት ባለመጣሌ አኩርፈውኝ የነበረ መሆኑ ሌላው ችግር ነበር፡፡ ይህንንም ችግር እኔ ባህሉን ባለማወቄና በመደንገጤ የተነሳ የፈፀምኩት እንደሆነ ገልጬ ይቅርታ በመጠየቄ ፈትቼዋለሁ፡፡

# ምዕራፍሁለት

## የተዛማጅ ጥናቶች እና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

ይህን ክፍል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ነጣጥሎ ማየት ይሻላል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች የሚቃኙ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral prose narrative)፣ ስለማንነት (Identity)፣ እና ስለተግባራዊ አቀራረብ (Functional approach) የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ይደረጋል፡፡

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ተረክን መሠረተ ነገራቸው አድርገው የተሰሩ ጥናቶች ይቃኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የከሁሉም በላይ የሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ ጥናትና የአብረሃም አለሙ "አርቲክል" ተረክና ማንነትን አጣምረው የተሰሩ በመሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ዝምድና አላቸው፡፡ የተቀሩት አስራ አንድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ ጥናቶች ግን በዚህ ክፍል የተጠናቀሩት ተረክ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ነው፡፡

ከእኔ ጥናት ጋር ግንኙነት ኖሮት ያገኘሁት ጥናት ከሁሉም በላይ በ2004 ዓ.ም ያሠናዳችው ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት የተሠራ ሲሆን “የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርአቶች ጥናት” በሚል ርዕስ የተሠየመ ነው፡፡ በውስጡም ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን በአንድ ወገን፣ ባህላዊ ስርአቶቹን ደግሞ በሌላ ወገን ተንትናለች፡፡

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማም የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርአቶች ለማህበረቡ አባላት ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በንዑስ አላማ ስርም በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማህበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የስራ ባህልና አምልኮ እንዴት እንደተገለፁ ለማሳየት መሞከር አንዱ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ ማንነት መገለጫዎች በመሆናቸው ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡

ከሁሉም ተረኮቹ የሚያነሷቸውን ጭብጦች መነሻ በማድረግ ትንተናውን በስምንት ክፍሎች ከፍላ ታስረዳለች፡፡ እነሱም ከማህበረሰቡ ስያሜ ጋር የተያያዙ ተረኮች፣ ከማህበረሰቡ አመጣጥ ጋር የተያያዙ ተረኮች፣ ነገደ ወይጣና ሺህ ጅብሪል፣ ነገደ ወይጦና አቢናዝ፣ ነገደ ወይጦና ባህር ዳር፣ ነገደ ወይጦና የታንኳ እና የወፍጮ ስራ፣ ነገደ ወይጦና እርግማን እንዲሁም ነገደ ወይጦና ውሃ የሚሉ ናቸው፡፡

በጥናቱ ውጤት እንደገለፀቸውም ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የማህበረሰቡን ስያሜ፣ አመጣጥ፣ አምልኮ፣ የስራ ባህልና ድህነታቸውን አስመልክቶ የአካባቢው ማህበረሰብ ለሚያደርስባቸው ተፅዕኖ ወይም መገለል ምላሽ የሚሠጡና የማህበረሰቡ አባላት በማንነታቸው እንዲኮሩና በራሳቸው ፀንተው እንዲኖሩ የሚያደርጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የከሁሉም ጥናት በቀጥታም ባይሆን ተረክ ማንነትን የመገንባትና የመግለፅ ተግባር እንዳለው የሚያትት በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም የኔ ጥናት ቀጥተኛ ጉዳይ በተረክ ማንነት እንዴት እንደሚገነባና እንደሚገለፅ ማሳየት በመሆኑና የምናጠናቸው ማህበረሰቦች የተለያዩ መሆናቸውን ሁለቱን ጥናቶች የተለያዩ ያደርጋቸዋል፡፡

ሌላው ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው የአብረሃም አለሙ አርቲክል ነው፡፡ ይህ አርቲክል “narrating local identity among the southwestern Oromo of Ethiopia: case of Jimma and Gera” የሚል ሲሆን እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ስሌት በ2012 African study monographs በተሰኘ መፅሔት 33(1) ከገፅ 17-47 የሠፈረ ነው፡፡

ጥናቱ ተረክ ማንነትን የመገንባትና የመግለፅ ተግባር እንዳለው የጅማና የጌራን ማህበረሰብ መነሻ በማድረግ ያስረዳል፡፡ የጥናቱን አላማ ሲገልፅ ተረክ እንዴት፣ በምን መሠረትና እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል ራሱን ከሌሎች በማነፀር ማንነቱን እንዴት እንደሚገልፅ ማሳየት ነው ይላል፡፡

እንደ ኦሮሞ ላሉና ታሪካቸውንና ባህላቸውን በስነቃሎቻቸው ለሚያስተላልፉ ማህበረሰቦች ፎክሎር በተይም ቃል ተረክ የማንነታቸው መገንቢያና መግለጫ እንደሆነ አብረሃም ያስረዳል፡፡ በዚህ ፅሁፍ ገፅ 25 ለይ የማንነት ተረክን ሲገልፅም “identity narrative may not

necessarily be in a form of stories in the strict sense of the term they are often presented as conversations or reminiscences past experiences and explanations of the present state of affairs." ይላል። ከጥቅሱ ለመረዳት እንደሚቻለው የማንነት ተረኮች የግድ በትረካ መልክ የተዋቀሩ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። ለዚያም ይመስላል አብረሃም በጥናቱ ውስጥ ከተነተናቸው ተረኮች ውስጥ አጫጭሮችና በንግግር መልክ የቀረቡ የሚበዙበት። በትንተናው የተካተቱት ተረኮች ሴና (seenaa) የሚባሉ ሲሆኑ ማህበረሰቡ እውነት ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ታሪካዊ ተረኮች ሲሆኑ የሚተረኩትም በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ባላቸው አዋቂ ወንዶች ነው።

አብረሃም በማጠቃለያው እንደሚያስረዳው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ማንነት ከሌሎች ማህበረሰቦች አንፃር በማወዳደር የሚገነባና የሚገለፅ ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ በተረክ ነው። የጅማና የጌራ ማህበረሰብም ከተለያዩ ነገሮች አንፃር ራሳቸውን በቃል ተረኮቻቸው እንደሚገልፁ በአርቲክሉ ተጠቁሟል። ከእነዚህ ነገሮች መካከል ዋና ዋናዎቹም የማህበረሰቡ ታሪክ፣ እሴት፣ ግዛትና የዘር ሀረግ እንደሆኑና እነዚህ ነገሮች የጅማና የጌራን ማህበረሰብ ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚለዩት እንደሆኑ አብረሃም ያስረዳል። የጌራ ማህበረሰብ በቃል ተረኮቹ እንደሚያስረዳውም ተዋጊና አምራች ነው። አብረሃም ማንነት በተረክ እንዴት እንደሚገነባና እንደሚገለፅ ማጥናቱ ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው ቢሆንም የምናጠናቸው ማህበረሰቦች ግን ልዩነታችን ናቸው።

ከእነዚህ ጥናቶች በተጨማሪ ተረክ መሠረተ ነገራቸው አድርገው የተሠሩ አስራ አንድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ ጥናቶች ተዳሰዋል። እነዚህ የሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ ጥናቶች ምን ላይ እንደሚያተኩሩና ከዚህኛው ጥናት ጋር ያላቸው ግንኙነት (አንድነትና ልዩነት) ይዳሰሳል።

ከነዚህ ጥናቶች መካከል አንዱ አማረሞላ፣ በ1999 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ነው። የዚህ ጥናት አላማ የሸካቾ ብሄረሰብ ሀገረሰብ ተረቶችን ሰብስቦ መመደብ፣ ቅርፅና ይዘታቸውን ተንትኖ ማሳየትና ሰንዶ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ እንደሆነ በጥናቱ ላይ ተገልጿል። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም የሸክቾ ብሄረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች በምን አይነት መንገድ ሊመደቡ ይችላሉ? የሀገረሰብ ተረቶቹ የአከዋወን ስልት ምን ይመስላል? ተረቶቹ ውስጥ ምን ምን ማህበራዊ፣

ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ታሪካዊና ባህላዊ ጉዳዮች ይንፀባረቃሉ? የሚሉ መሪ ጥያቄዎችን ቀምሯል። በጥናቱ ትንተና ላይ ተረቶቹን አይነታዊና ይዘታዊ ትንተናን በመጠቀም እንደሚመድብ ገልጿል።በአይነታዊ ምደባ ስርም አካባቢያዊ ምደባንና ፎክሎራዊ ምደባን ተጠቅሞ ተረቶቹን በተለያየ መንገድ መድቧል። አካባቢያዊ ምደባን መሰረት አድርጎ ተረቶቹን ኬሞ እና ኢንጌሞ በማለት የመደበ ሲሆን በኬሞ ስር የሚመደቡት ተረቶች ስለብሔረሰቡ የጎሳ መሪዎች ወይም ንጉሶች፣ ስለባህላዊ የእምነት መሪዎች፣ ብሔረሰቡ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ስላደረጋቸው ጦርነቶች ወዘተ. የሚያትቱ ናቸው (34)። በኢንጌሞ ስር የሚካተቱት ተረቶች ደግሞ በብሔረሰቡ እምነትና አስተሳሰብ ስለአንዳንድ ማህበራዊ ግንኙነቶች፣ በአካባቢያቸው ስላሉ ልዩ ልዩ ክስተቶችና ሁኔታዎች የሚያትቱ እንደሆኑ ገልጿል። እዚህ አከፋፈል ላይ የጠራ ድንበር አይታይም። ለምሳሌ በኬሞ ስር ከሚካተቱት ተረቶች መካከል ብሔረሰቡ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ስላደረጋቸው ጦርነቶች የሚያወሩ ተረቶች እንደሚካተቱ ገልጿል። በሌላ በኩል በኢንጌሞ ስር ከሚካተቱት ተረቶች መካከል በአካባቢው ስላሉ ልዩ ልዩ ክስተቶችና ሁኔታዎች የሚያወሩት ይካተታሉ። ጦርነት ደግሞ ከአካባቢያዊ ክስተቶች አንዱ ነው። ስለዚህ ይህ ጉዳይ የሁለቱን ድንበር ለማካለል ያስቸግራል። በዚህም አንዱ በሌላው ውስጥ የሚጣለቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በሌላ አከፋፈል (አማረ እንደሚለው በፎክሎራዊ ምደባ) ደግሞ ተረቶቹን አፈታሪክ፣ ገላጭ/ኬትመጣ/ ተረቶች እና ፋቡላ በማለት በሦሥት ይመድባቸዋል። እራሱ በገጽ 31 ላይ ሲያስረዳ የስነቃሉ ባለቤቶች የሰጡትን ምደባ መጠቀም ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ እየገለጸ፣ማህበረሰቡ የመደበው ምደባ እያለ የ“Okpewho”ን አከፋፈል መጠቀሙና መመደቡ ተገቢነቱ አልታየኝም። Ben-Amos (1982)ም ዝርው ተረኮችን ለመመደብ ጥቅም ላይ ከዋሉት ዘዴዎች መካከል የአካባቢያዊ ምደባ ዘዴና የትንተናዊ ምደባ ዘዴዎች እንደሚገኙ ጠቁመው እነዚህ ሁለት የምደባ ዘዴዎች የየራሳቸው የአመዳደብ ስልትን እንደሚከተሉ ይገልጻሉ። እንደ Ben-Amos (1982) አገላለጽ ዝርው የቃል ተረኮችን የአውሮፓውያኑን አከፋፈል ይዞ ተረት (Folktale)፣ አፈታሪክ (Legend) እናሚት (Myth) ብሎ ከመክፈል ይልቅ አካባቢያዊ ምደባን መጠቀም የተሻለ ነው። ምክንያቱም በዚህ መንገድ መክፈል ወጥነት ስለሌለው ነው። ለአንዱ ማህበረሰብ ሚት የሆነው ለሌላው ተረት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ አንዱን የመክፈያ አቅጣጫ መከተል ይበጅ ነበር።

በማህበረሰቡ ውስጥ ተረት ለመተረት የተለየ ቦታና ሁኔታ ወይም የጊዜ ቀጠሮ እንደሌለ ከጠቆመ በኋላ ተረቶቹን ከይዘት አንፃር በስድስት ዋና ዋና ጭብጦች መድቧቸዋል። እነሱም ብልህነት፣ መጥፎ ባህሪያት፣ ፍትሀዊነት፣ ጓደኝነት፣ ትዕግስተኝነት፣ እና ጣውንትነት ናቸው። አብዛኛዎቹ ተረቶችም ትምህርታዊ መልዕክት የሚተላለፍባቸው ሆነው መገኘታቸውንም ገልጿል።

ሌላው ስራ፣ "በየምብ ሔረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት 'ምስል' ትንተና" በሚል ርዕስ ለማ ንጋቱ በ1999 ዓ.ም ያዘጋጀው ነው። የዚህ ጥናት ዋና አላማም በየም ልዩ ወረዳ የሚተረኩ ፆታ ተኮር ተረቶችን ሰብስቦ በተረቶቹ ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደተገለጹ መተንተን ነው። ከዚህ ዋና አላማ ስርም ሶስት ንዑሳን ዓላማዎች ተካተዋል። አንደኛው ፆታ ተኮር ተረቶችን በዘርፍ መመደብ፣ ሁለተኛው ተረቶች ፆታዊ ምስልን የሚያንፀባርቁባቸውን መንገዶች መለየት እና ሶስተኛው ደግሞ ፆታ ተኮር ተረቶችን ከነአውዳቸው በስርአት አደራጅቶ መሰነድ ናቸው።

የዚህ ጥናት የንድፈሃሳብ ቅኝት ራሱን ችሎ በአንድ ምእራፍ የተቀመጠ ሳይሆን በምእራፍ 3 እና 4 ከማሕበረሰቡ ተረቶች ክዋኔና ምደባ ጋር እየተቀላቀለ የቀረበ ነው።

በድምዳሜውም ሴቶች ከአርባ ሁለት ተረቶች ውስጥ በሃያ አንዱ፣ ወንዶች ደግሞ ከሰላሳ ስምንት ተረቶች ውስጥ በሃያ አራቱ በአወንታ የተሳሉ ሲሆን በተቀሩት ደግሞ በአሉታዊ መልክ እንደተሳሉ ገልጿል። በአፈታሪክና በገላጭ ተረቶች እምነትን ተገን በማድረግ የወንዶች ንጽህናና የበላይነት፣ የሴቶች ደግሞ ጎዳፋነትና የበታችነት እንደተገለፀ አመልክቶ ለዚህ የመፍትሄ ሀሳብ ይጠቁማል። የመፍትሄ ሀሳቡም "...ስለዚህ በብሔረሰቡ ውስጥ በስነፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ማህበራትና ድርጅቶች በሴቶች ላይ ስነልቦናዊ ጫና የሚያሳድሩ ተረቶችን በመለየት ሃይማኖታዊ መሰረት እንደሌላቸው ቢያጋልጡ የሚፈጥሩትን ጫና ሊቀንስ ይችላል" የሚል ነው። ነገር ግን በትንተና ወቅት ተረቶቹ ሃይማኖታዊ መሰረት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን አላሳየም። እንዲህ ያለውን የመፍትሄ ሃሳብ ለማስቀመጥ አስቀድሞ እነዚህ ተረቶች ሃይማኖታዊ መሰረት ያላቸውና የሌላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

ተረቶቹ በብሄረሰቡ አጠራር በሁለት ተከፍለዋል (ተመድበዋል)። አንደኛው "ቶቾ" ሲሆን ሌላው ደግሞ "ኤሻ" ነው። ቶቾ፣ እውነት ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውና ስለብሔረሰቡ አመጣጥና ስላለፈባቸው ታሪካዊ ሂደቶች የሚተርኩ ሲሆኑ ኤሻ ደግሞ የፈጠራ እንደሆኑ የሚታመንባቸው በመሆናቸው በአብዛኛው ለተዝናኖት የሚተረኩ እንደሆኑ ገልጿል።

በዚህ ጥናት ላይ የተጠየቀ ችግር አስተውያለሁ። ለምሳሌ በገጽ 27 ላይ "ወጣቱ ትውልድ ባህሉን የመናቅ አዝማሚያ ስላለው ተረት አይተርትም" ይላል። ትንሽ ወረድ ብሎ ደግሞ "...እኔም በመስክ ቆይታዬ ተረት የሚተረትበትን አጋጣሚ አለማግኘቴ 'ተረት የመተረት ባህሉ ቀርቷል' የሚለውን የመረጃ አቀባዮቼን ሃሳብ እንድጋራ ቢያደርገኝም ከሁለቱም ጾታዎች መረጃ አቀባዮችን ያለችግር ማግኘቴ በሁለቱም ጾታዎች የመተረት ባህሉ እንደነበረ ለመገንዘብ አስችሎኛል" ይላል።ገጽ 37 ላይ ደግሞ "...እነዚህን እሴቶች በቃል ጠብቆ ለማቆየት ወይም ለማያውቃቸው እንግዳ ለማስረዳት የብሄረሰቡ አባላት ወጣት አዛውንት ሳይሉ ይተርካሉ።" ይላል። እነዚህን አገላለጾች ስንመለከት በአንድ በኩል ወጣቱ አይተርትም ይላል፤በሌላ በኩል ደግሞ ይተርታል ይላል።ስለዚህ ይህ አገላለጽ የሚጣረሱ ሃሳቦችን የያዘ ይመስለኛል።

ሌላው ጥናት የምንዳ ገብሬ (2000 ዓ.ም) ሲሆን፣ "የጌዴኦ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው" የሚል ነው። የዚህ ጥናት ዓላማዎች በህብረተሰቡ ልማዳዊ ስርአቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው መካከል ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መርምሮ ለማመልከት በተወሰኑት ላይ ዝርዝር ያለ ዳሰሳ ማካሄድ፣ የጌዲኦ ዝርው ቃል ተረኮች ከሚያበረክቷቸው ማህበራዊ ግልጋሎቶች አንጻር ሲመረመሩ ይዘቶቻቸው በምን በምን ላይ እንደሚያተኩሩ ማሳየት፣ የተረኮቻቸውን ኅሳዊ ምደባና አካካቢያዊ ስያሜዎቻቸውን ለይቶ ማውጣት፣ እንዲሁም ስለዝርው ቃል ተረኮች ምንነት በመስኩ ምሁራን የተሰጡ ገለፃዎችን ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማስተያየት ክዋኔያቸውን፣ አወቃቀራቸውን፣ ተመሳስሎና ልዩነታቸውን ለይቶ ማመልከት የሚሉ ናቸው።

መረጃውን የሰበሰበው በ1999 ዓ.ም ዲላ ዩኒቨርስቲ ከሚማሩ የክረምት ተማሪዎች ሲሆን ከመካከላቸውም ለቡድን ውይይት የሚሆኑትን መረጃ አቀባዮች የለየበትንም መስፈርት ሲገልጽ "...የአካባቢው ተወላጅነት፣ልማዱንና ስርአቱን ማወቅ፣የትምህርት ደረጃቸው ከፍ ያለ መሆን..." እንደሆነ ገልጿል። መረጃውን ከክዋኔ አውዱና ከማህበራዊ አውዱ ውጪ የሰበሰበው በመሆኑ

ምናልባት ትክክለኛውን መረጃ ላያገኝ ይችላል። ለቡድን ውይይት የሚሆኑትን መረጃ አቀባዮች ሲመለምልም የትምህርት ደረጃን እንደ አንድ መስፈርት መጠቀሙ አስፈላጊነቱ አልታየኝም። ምክንያቱም የአንድን ማህበረሰብ ተረት ለማወቅ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር መስፈርት አይሆንም። ያልተማረው ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ተረት ይተርታል።

የጌዴኦ ዘርው ቃል ተረኮች የልማዳዊ ስርዓቶቹ መግለጫ፣ ማጠናከሪያና ቀጣይነታቸው እንዲጠበቅ መልሰውም መትከያዎች እንደሆኑ ገልጿል። Finnegan (1970:329-330)ን በመጥቀስ ተረኮች የተጠቀሱትን ማህበራዊ ጉዳዮች ከማስተናገድ ውጪ ሌላ ፋይዳ እንደሌላቸው ይገልጻል። ነገር ግን ዘርው ቃል ተረኮች ልማዳዊ ስርአቶችን ከመግለጽ፣ ከማጠናከርና ቀጣይነታቸው እንዲጠበቅ መትከያዎች ከመሆን ባሻገር የማንነት መገለጫዎችም ናቸው።

የተረቶቹን አወቃቀር፣ አቀራረብ፣ የታዳሚን እድሜና መቼትን መነሻ በማድረግ ዘርው ቃል ተረኮቹን "መማሳ" እና "ጢንጎ" በሚል በሁለት ከፍሏቸዋል።

መማሳ ሽማግሌዎች የሚተርቱት፣ የሚተረትበት ስፍራ ደግሞ ስብሰባ፣ እርቅና ዳኝነት የሆነ፣ የሚተረትበት ጊዜ ግን ያልተገደበ እንደሆነና ጢንጎ ደግሞ በመኖሪያ ቤቶች፣ በየዛፍ ጥላ ስር፣ በየደጃፉ ላይ በእረኝነት ቦታና በሃዘን ቦታዎች የሚነገሩ፣ ተራኪዎቹ በእድሜ የተገደቡ፣ የሚቀርቡበት ጊዜም ከስራ ሰዓት ውጪ እንደሆነ ገልጿል። የመጀመሪያው ጉዳይ ስብሰባ፣ እርቅና ዳኝነት ስፍራ ሳይሆኑ ሁኔታዎች ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች የሚከወኑባቸው ስፍራዎች ደግሞ አንድም መኖሪያ ቤት፣ ወይም የዛፍ ጥላ ስር አለበለዚያም ደጃፎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ መማሳ ከጢንጎ የሚለይ አልሆነም።

ጢንጎን ሲያብራራም ለመክፈያነት ከተጠቀመባቸው መስፈርቶች ውጪ "ገጸባህሪያቱ ሰውና እንስሳት፣ ሰውና አራዊት ናቸው" ይላል። ከተራው ነገር ብንነሳ አራዊት የእንስሳት አንዱ ምድብነው። ስለዚህ ሰውና እንስሳት፣ ሰውና አራዊት የሚለው አገላለጽ የተገባ አይመስለኝም። ዋናው ጉዳይ ግን የገጸባህሪያትን ሁኔታ ለመክፈያ መስፈርትነት ሳይጠቀም በሁዋላ ደግሞ የጢንጎን ባህሪ ብቻ ሲያብራራ ማንሳቱ ከመማሳ ለመለየት አይጠቅምም። ምክንያቱም የመማሳ ገጸባህሪያት እንዲህ ናቸው ተብሎ ባልተተነተነበት ሁኔታ ሁለቱን (መማሳንና ጢንጎን) በገጸባህሪያት ለመለየት ስለማይቻል ነው።

በገጽ 72 ላይ የጢንጎና መማሳን ልዩነት በሰንጠረዥ ሲያስረዳ የጢንጎ ተራኪዎች በማንኛውም የእድሜ ክልል የሚገኙ እንደሆኑ አስፍሯል፡፡ ይህ ደግሞ አስቀድሞ በገጽ 68 ላይ “የጢንጎ ተራኪዎች በእድሜ የተገደቡ ሆነው...” ከሚለው ጋር ይጋጫል፡፡ ይህም በጥናቱ ላይ የተጠየቀ ችግር ሊኖር እንደሚችል ያመላክታል፡፡

በቀጣይነት የተመለከትኩት ጥናታዊ ስራ የማንያስለው አባተ ባየህን (1999 ዓ.ም) ነው፡፡ የዚህ ስራ ርዕስ፣ “የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው” የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የቤንች ብሔረሰብ አባቶች የእኛ ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን የቃላዊ ዝርው ተረኮች ዘሮች ለይቶ መግለፅ ነው፡፡ ከዚህ ዋና አላማ ስርም የዝርው ተረኮቹን ጭብጥ በመተንተን፣ ማህበራዊ ፋይዳቸውን መግለፅ እና የቤንችን ብሔረሰብ አባላት ዝርው ተረኮች መቼና የት እንደሚተረኩና በብዛት እጥቅም ላይ የሚውለውን የዝርው ተረኮች ዘር መግለፅ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን ይዟል፡፡ ጥናቱ ሶስት ጥያቄዎችን ለመመለስ እንደሚጠናም ተጠቁሟል፡፡ ይኸውም ትረካ ለቤንቾች ምንድን ነው? በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ዝርው ተረኮች ሲቀርቡ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? እና የብሄረሰቡ አባላት ዝርው ተረኮቻቸው በአሁኑ ወቅት በምን ሁኔታ እንደሚገኙ ይታወቁ ይሆን? የሚሉ ናቸው፡፡ ምናልባት እነዚህ የምርምር ጥያቄዎች የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ቅስም ያላቸው አይመስሉም፡፡ የምርምር ጥያቄዎች የሚነሱት ከአላማ ላይ ነው፡፡ የሚከናወነውም ምርምር እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ነው፡፡ ስለዚህ የምርምሩ ጥያቄዎች ከአላማው ጋር ቁርኝት ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡ በዚህ ጥናት ግን ይህን አልተመለከትኩም፡፡

ማንያስለው በጥናቱ ደረስኩበት እንደሚለውም ቤንቾች ዝርው ተረኮቻቸውን ከክወና አውዳቸው፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከተረኩ እውነተኛነትና ከትረካዎቹ አላማ አንፃር “ኤሸሸ” እና “ቤንችቶስ” በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ኤሸሸ የፈጠራ ታሪክ ሆኖ ክወናውም በምሽት እንደሆነና በአዋቂዎች ለልጆች የሚተረክ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ዓላማውም ለማስደሰትና ስነምግባርን ለማስተማር ተብሎ እንደሆነ ጠቁሟል፡፡ ቤንችቶስ ደግሞ እውነተኛ ታሪኮች የሚቀርቡበት ሲሆን በአንድ የታሪክ አጋጣሚ በአካባቢው ተነስተው የነበሩት ታዋቂ/ታሪካዊ/ ሰዎችን የሚመለከቱ አፈታሪኮችን፣ የብሔረሰቡን እምነት፣ የአምልኮ ስርአትና አሰራሮች የሚመለከቱ

በገጽ 72 ላይ የጢንንና መማሳን ልዩነት በሰንጠረዥ ሲያስረዳ የጢንን ተራኪዎች በማንኛውም የእድሜ ክልል የሚገኙ እንደሆኑ አስፍሯል፡፡ ይህ ደግሞ አስቀድሞ በገጽ 68 ላይ "የጢንን ተራኪዎች በእድሜ የተገደቡ ሆነው…" ከሚለው ጋር ይጋጫል፡፡ ይህም በጥናቱ ላይ የተጠየቀ ችግር ሊኖር እንደሚችል ያመላክታል፡፡

በቀጣይነት የተመለከትኩት ጥናታዊ ስራ የማንያለው አባተ ባየህን (1999 ዓ.ም) ነው፡፡ የዚህ ስራ ርዕስ፣ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው" የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የቤንች ብሔረሰብ አባቶች የእኛ ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን የቃላዊ ዝርው ተረኮች ዘሮች ለይቶ መግለፅ ነው፡፡ ከዚህ ዋና አላማ ስርም የዝርው ተረኮቹን ጭብጥ በመተንተን፣ ማህበራዊ ፋይዳቸውን መግለፅ እና የቤንችን ብሔረሰብ አባላት ዝርው ተረኮች መቼና የት እንደሚተረኩና በብዛት እጥቅም ላይ የሚውለውን የዝርው ተረኮች ዘር መግለፅ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን ይዟል፡፡ ጥናቱ ሶስት ጥያቄዎችን ለመመለስ እንደሚጠናም ተጠቁሟል፡፡ ይኸውም ትረካ ለቤንቾች ምንድን ነው? በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ዝርው ተረኮች ሲቀርቡ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? እና የብሄረሰቡ አባላት ዝርው ተረኮቻቸው በአሁኑ ወቅት በምን ሁኔታ እንደሚገኙ ይታወቁ ይሆን? የሚሉ ናቸው፡፡ ምናልባት እነዚህ የምርምር ጥያቄዎች የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ቅስም ያላቸው አይመስሉም፡፡ የምርምር ጥያቄዎች የሚነሱት ከአላማ ላይ ነው፡፡ የሚከናወነውም ምርምር እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ነው፡፡ ስለዚህ የምርምሩ ጥያቄዎች ከአላማው ጋር ቁርኝት ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡ በዚህ ጥናት ግን ይህን አልተመለከትኩም፡፡

ማንያለው በጥናቱ ደረስኩበት እንደሚለውም ቤንቾች ዝርው ተረኮቻቸውን ከክወና አውዳቸው፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከተረኩ እውነተኛነትና ከትረካዎቹ አላማ አንፃር "ኤሸሸ" እና "ቤንችቶስ" በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ኤሸሸ የፈጠራ ታሪክ ሆኖ ክወናውም በምሽት እንደሆነና በአዋቂዎች ለልጆች የሚተረክ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ዓላማውም ለማስደሰትና ስነምግባርን ለማስተማር ተብሎ እንደሆነ ጠቁሟል፡፡ ቤንችቶስ ደግሞ እውነተኛ ታሪኮች የሚቀርቡበት ሲሆን በአንድ የታሪክ አጋጣሚ በአካባቢው ተነስተው የነበሩት ታዋቂ/ታሪካዊ/ ሰዎችን የሚመለከቱ አፈ.ታሪኮችን፣ የብሔረሰቡን እምነት፣ የአምልኮ ስርአትና አሰራሮች የሚመለከቱ

እንደሆኑ አሳይቷል። ለምደባው ወጥ መስፈርት ማስቀመጡና በመስፈርቶቹም እስከመጨረሻው መገልገሉ ከጥናቱ ጥንካሬዎች መካከል አንዱ ነው።

ሌላው ጥናት አብዱልቃድር ሃጂ (1982)፣ "Some cultural elements as reflected in Somalia folktale" በሚል ርእስ ያዘጋጀው ነው። የዚህ ጥናት ተቀዳሚ ዓላማ በተረቶቹ ላይ ተመስርቶ የሶማሌን ብሔረሰብ ባህላዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮች ማሳየት ነው። ለዚህም ማሳያ ስማኒያ ሁለት ተረቶችን ሰብስቦ በተረቶቹ ውስጥ ጎልቶ የታየውን ጭብጥ መነሻ በማድረግ በስምንት መድቧቸዋል። ይዘቶቹም ብልህነትና ጥበበኝነትን፣ ፍትህን፣ ሀይማኖትና ስነምግባርን፣ ጋብቻን፣ ሴቶችና ቅናትን የሚመለከቱ እንደሆኑ ገልጿል።

አብዱልቃድር መረጃውን የሰበሰበው በጅጅጋ ከሚገኝ የስደተኞች ካምፕ ውስጥ ብቻ በመሆኑ ምናልባ ትማህበራዊ አውዱን ስለማያገኘው የሁሉንም የሱማሌ ክልል የተመለከተ ጥናት ነው ላይባ ልይችላል።

ተስፋዬ ገ/ማ በ1990፣ "A study of major themes in Jabalwi folktales" በሚል ርዕስ ያሰናዳው ጥናት ደግሞ ትኩረቱ በጀብላዊ ሀገረሰብ ተረኮች ጭብጥ ትንተና አማካይነት የጀብላዊ ብሔረሰብን ማንነትና የአኗኗር ልማዳቸውን እንዲሁም ርዕዮተ ዓለማቸውን (ማህበረሰቡ አለምን የሚያይበትን አተያይ) ማሳየት ነው። የተረኮቹን ጭብጥ በመመርመር የጀብላዊ ብሔረሰብ ስለዓለም ያለውን አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ልማድ፣ ወግ፣ ተስፋ፣ ምኞት ወዘተ. መገንዘብ እንደቻለ ገልጿል። የሰበሰባቸውን ሰባ ሁለት ተረቶችም በሀያ አምስት ዋና ዋና ጭብጦች መድቧል። ጭብጦቹም የነገሮች አመጣጥ፣ ሰዋዊ እኩይ ምግባራት፣ እርኩስ መናፍስት በማለት መድቦ በስራቸው ስለብቀላ፣ ስለትዕግስት፣ ስለቅናት፣ ስለስስታምነት፣ ስለምቀኝነት፣ ስለሞኝነትና ደደብነት፣ ስለስንፍና፣ ስለጨካኝነት ስለሀይማኖት፣ ስለፍርሃት፣ ስለታማኝነት፣ ስለአንድነት፣ ስለፍትህ፣ ስለእውነት እንደሚገልፁ አሳይቷል። አጥኚው መረጃዎችን ከመረጃ አቀባዮች መሻት ውጪ ለመሰብሰብ መከጀሉ (1990፡12) ከምርምር ስነምግባር ውጪ እንዳይሆን ያሰጋል። ምክንያቱም መረጃን ለመሰብሰብ ስንነሳ የመረጃ አቀባዮችን መረጃ ለመስጠት ያለ ፍላጎት መጠየቅና ማረጋገጥ ከምርምር ስነምግባሮች መካከል አንዱ በመሆኑ ነው።

መላክነህ መንግስቱ (1990) “The major themes and motifs of southern Agaw Folktales” በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ጥናት ዋና ትኩረት በጭብጥና በመባያ ጉዳዮች (motifs) ላይ የተመሰረተ ትንተና ማቅረብ ነው፡፡ የጥናቱ ዝርዝር አላማዎችም የደቡባዊ አገው ሀገረሰብ ተረቶች ያላቸውን ስነፅሁፋዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መመርመር፣ ተረቶቹ በብሔረሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና መወሰን፣ የህዝቡን ስነልቦናዊ፣ ስነምግባራዊና ኪናዊ አመለካከትና እምነት ማሳየት የሚሉ ናቸው፡፡ የሰበሰባቸውን ስድሳ ተረቶች የቶምሰንን “motif index” በመጠቀም በ12 ምድብ ቦድኖ ተንትኗል፡፡ በጥናቱ ድምዳሜም ተረቶቹ ወጣቶች ለማስተማር ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጡ ገልጿል፡፡ በዚህ ፋይዳቸውም የወጣቶችን አካላዊና አዕምሮአዊ ብቃት በማሳደግ የህበረተሰቡን ጥሩ ስነምግባራት በማስቀጠል ወጣቶቹ የመቻቻል ባህላቸው እንዲጎለብት የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡ በጥናቱ ዘገባ (report) ገፅ 45 ላይም ተረቶቹን በተለያዩ ምድቦች የመክፈሉን ስራ አስቸጋሪነት ገልጿል፡፡

ሌላው የተመለከትኩት ጥናት ሳህሉ ኪዳኔን በ1996፣ “Borana Oromo prose narrative, A contextual study” በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ስራ ነው፡፡ ሳህሉ የቦረናን ዝርው የቃል ተረኮች ከማህበረ-ባህላዊ አውዳቸው ተነስቶ ያጠና ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማም የማህበረሰቡን ተረኮች ሰብስቦ አውዱን መነሻ በማድረግ በአይነት መመደብ ነው፡፡ በዚህም የሰበሰባቸውን ተረኮች በሶስት መድቧቸዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንደኛው “Duri duri” ሲሆን የልጆች ተረት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ “Mamaksa” ሲሆን ይህ ምድብ ደግሞ የአዋቂ ተረቶችን የሚያቅፍ ነው፡፡ ሶስተኛው ምድብ “Arga geti” ነው፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱት ደግሞ ሚቶችና አፈታሪኮች ናቸው፡፡ እነዚህ ምደባዎች ሀገረሰባዊ (Indigenous classification) እንደሆኑና በማህበረሰቡ የተ መደቡና የተ ሰየሙ መሆናቸ ውን እና እያንዳንዳቸ ው የተ ለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዳሏቸው ገልጿል፡፡ ይህ ጥናት አውዳዊ የአጠናን ዘዴን፣ አካባቢያዊ ምደባና ትንተናን እንዲሁም አካባቢያዊ ስያሜዎችን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡

የልጆች የተባሉት ከ7-15 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ሰዎች የሚከወኑት ናቸው፡፡ ይህ ተረክ ሲጀምርም፣ “ከብዙ አመት በፊት ነው አሉ” ብሎ ነው፡፡ የጎልማሶች ተረኮች የህብረተሰቡን እሴቶችና እምነቶች የያዙ ናቸው፡፡ በዚህ ስር ያሉት ተረኮች ወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል መልካሙን ከክፉው እንዲለይ የህብረተሰቡን ጥበቦች፣ ባህላዊ እውነታዎችና መሰል ጉዳዮች

እንዲያውቅ በማሰብ እነዚህን ጉዳዮች የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በሶስተኛው ምድብ ውስጥ ያሉት ሚቶችና አፈታሪኮች ደግሞ የህብረተሰቡን ታሪክና ልማድ (History and tradition) ይዘዋልብሏል፡፡

ሌላው ጥናት ደግሞ ይሄነው ጀምበር በ1996፣ "A generic classification of Amharic oral prose narrative of west Gojam" በሚል ርእስ ያሰናዳው ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምዕራብ ጎጃም አካባቢ የሚነገሩ የአማርኛ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሰብስቦ መመደብ ነው፡፡ ለምደባ ስራውም እንደመስፈርትነት የተጠቀመው የክዋኔ አውድን፣ ጭብጥን፣ የገፀባህሪያት አሳሳልን፣ የታሪክ አወቃቀርንና የአቀራረብ ስልትን ነው፡፡ የሰበሰባቸውን ተረኮችም ተረት፣ አፈ-ታሪክ እና የዘር ሀረግ ቆጠራ (genealogy) በማለት በሶስት ምድብ ከፍሏቸዋል፡፡ የተረቶቹ ክዋኔ በየትኛውም የእድሜ ክልል ባሉ ሴቶችና ወንዶች ሲሆን እንደሚችል የገለፀ ሲሆን አፈታሪኮችና ዘር ቆጠራዎች ግን በአዋቂዎች እንደሚከወኑ ገልጿል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ኖሮት የተገኘው ሌላው ስራ ባይለየኝ ጣሰው በ1999 "Anyuaa oral prose narrative-Ethnic genres and social function"በሚል ርእስ ያዘጋጀው ነው፡፡ የጥናቱ አላማዎች የአኙዋክ ብሄረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የማህበረሰቡን አመዳደብ መሰረት በማድረግ መለየትና የተረኮቹን ማህበራዊ ሚና ማሳየት ናቸው፡፡

ዝርው ተረኮቹን በአይነት ለመመደብም የአካባቢያዊ ምደባ ስልትን (indigenous way of categorization) ተጠቅሟል፡፡ በዚህም የተረኮቹን ይዘትና የተራኪውን እድሜ መስፈርት አድርጎ እውነተኛ ታሪክ (the Leere)፣ ተረቶች (the Wae) እና ምሳሌያዊ ታሪኮች (the Angade) በማለት በሶስት መድቧቸዋል፡፡ the Leere፣ ስለሞቱት ጀግኖችና ስለታሪካዊ ክንውኖች የሚተርኩ ናቸው፡፡ the Wae ደግሞ ልዩ ልዩ የሰው ባህሪያትን የሚያሳዩ ሆነው በቀልድ፣ በማስደሰትና በማዝናናት የተሞሉ ተረቶች ናቸው፡፡ the Angade፣ ያለፉ ሁነቶችን፣ የእምነት ስርአቶችንና ማህበረሰቡ አለምን የሚያይበትን አተያይ ያሳያሉ፡፡ የተረኮቹን ማህበራዊ ፋይዳ ሲገልፅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መምከሪያና ማስተማሪያ ናቸው ብሏል፡፡

ሌላው ጥናት አብርሃም አለሙ በ2000፣"Jimma Oromo oral prose narrative-Preliminary descriptive analysis" በሚል ርእስ ያሰናዳው ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ የጅማ ኦሮሞን

ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች መነሻ አድርጎ ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን መለየትና መግለፅ ነው፡፡ ይህን ዋና አላማ አንግቦም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች የትኞቹ እንደሆኑ ማሳየት፣ ማህበረሰቡ ተረኮቹን እንዴትና በምን መስፈርት እንደሚመድባቸው መመርመር፣ የተረኮቹን ውስጣዊ ባህሪያት ማጤን፣ ተረኮቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች መለየት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን አካቷል፡፡ ተረኮቹንም "Seenaa Taarika"፣ "Oduu duri" እና "Qoosaa" በማለት በሶስት መድቧቸዋል፡፡ ለዚህ አመዳደብ መስፈርቱም የተረኮቹ እውነተኛነትና ፈጠራዊነት እንዲሁም የሚተረኩበት ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጿል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ የሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ ጥናቶች በዝርው የቃል ተረክ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ከኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን በቅማንት ማህበረሰብ ላይ ያልተጠኑ በመሆናቸው፣ አላማቸው በተረክ ማንነት እንዴት እንደሚገለጽ ማሳየት ባለመሆኑና እያንዳንዳቸው የተረክ ምደባ ጉዳያቸው ሲሆን የኔ ጥናት ግን በተረክ ምደባ ላይ አለማተኮሩ፣ የቅማንት ማህበረሰብን ማጥናቱና ትኩረቱ በተረክ ማንነት እንዴት እንደሚገለጽ ማሳየት በመሆኑ ይለያያሉ፡፡

እነዚህ ጥናቶች ከፎክሎር ምድቦች (genres) መካከል አንዱ በሆነው ስነቃል ስር ባለው ዝርው የቃል ተረክ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ለፎክሎር ጥናት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ በተለይ አብዛኞቹ ጥናቶች እስከዛሬ በብዛት ያልተጠናው የማህበረሰብ ክፍል ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ተጠኚውን ማህበረሰብ ለሌላው ማህበረሰብ በማስተዋወቅ ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የጎላ ነው፡፡

## 2.2 የንድፈ ሀሳቦችቅኝት

ፎክሎር የብዙ ነገሮች የወል መጠሪያ ነው፡፡ በዚህም በውስጡ በርካታ ሰዋዊ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ Martha (2005፡12) ሲገልጹ፣ "Folklore is present in many kinds of informal communication, whether verbal/oral and written texts, customary/behavior, rituals or material/physical objects. It involves values, traditions, ways of thinking and behaving. It is about art. It is about people and the way people learn." በማለት ነው፡፡ ስለዚህ ፎክሎር ኢመደበኛ በሆነ መንገድ አለምን የምናውቅበት እውቀት ጭምር ነው፡፡ እኛነታችንን፣ ማህበረሰባችንን፣ እምነታችንን፣ ባህላችንን እና ልማዶቻችንን በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በልማድ፣ በድርጊት፣ በባህሪ እና በቁስ የምንገልጽበት ፈጠራ ነው፡፡

ስለዚህ ይህንን ትልቅ ጉዳይ እንዳለ ማጥናት አስቸጋሪ በመሆኑ ፎክሎርን በመከፋፈል ማጥናት እንደሚገባ በርካታ ምሁራን (Dorson 1972፡3,Toelken 1996፡183, Martha 2005፡12) ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን በእያንዳንዱ አመዳደብ ውስጥ ያለምንም ውዥንብር ፎክሎርን ፍንትው ባለ አኳኋን መክፈል አይቻልም፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንዱ አከፋፈል ውስጥ ብቻ አንዱ የፎክሎር ምድብ (genre) በሌላው የፎክሎር ምድብ (genre) ውስጥ መቀላቀሉ አይቀርም፡፡ የሆነው ሆኖ እንደነ "Dorson" በአራት፣ እንደነ Martha ደግሞ በ3 ክፍሎ ማጥናት የተለመደ ነው፡፡Martha (2005፡12) ቃላዊ ጥበባት (verbal art)፣ ቁሳዊ ባህል (Material culture) እና ማህበረሰባዊ ልማድ (folk customs) ብለው ሲከፍሉት፣ Dorson ( 1972፡ 3) ደግሞ ከላይ በተገለፁት ሶስቱ ዘርፎች ላይ ማህበራዊ ትውን ጥበባትን (Performing folk arts) በመጨመር ሦስት የነበረውን ምድብ ወደ አራት ከፍ ያደርጉታል፡፡

የፎክሎር አንድ ምድብ በሆነው ስነቃል ውስጥ የሚካተተው ቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral prose narrative) የዚህ ጥናት ትኩረት ይሆናል፡፡

### 2.2.1 ቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral prose narrative)

#### 2.2.1.1 የቃላዊ ዝርው ተረክ ምንነት

የቃላዊ ዝርው ተረክ ጥናት ሲነሳ Jacob Grimm እና Wilhelm Grimm የሚባሉ ጀመርመናዊ ወንድማማቾች አብረው ይነሳሉ፡፡ እነዚህ ወንድማማቾች ቃላዊ ዝርው ተረክን በማጥናት ፈር ቀዳጆች እንደሆኑ Dorson (1972፡1) ያስረዳሉ፡፡ በእነዚህ ወንድማማቾች መጠናት የጀመረው ቃላዊ ዝርው ተረክ እስካሁንም ድረስ በተለያየ አኳኋን ይጠናል፡፡

ቃላዊ ዝርው ተረክ የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ለዚህም ነው Fludernik (2009፡1)፣ "Narrative is all around us, it is associated above all with the act narrative and is to be found wherever someone tells us about something." የሚሉት፡፡ ከዚህ አገላለፅ መረዳት እንደሚቻለው ተረክ ማንም ሰው በማንኛውም ስፍራ ስለማንኛውም ነገር የሚተርከው ነው፡፡

ሌሎች ደግሞ (Fina 2003፡11, Brockmeyer 2000, Ochs and Capps 2001፡2) ተረክ ነገሮችን በጊዜ ቅደም ተከተል የሚተርክ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

የተረክን ምንነት አስመልክቶ Lwis እና Sandra (2001፡16) ሲገልፁ "Narrative is a discourse with a clear sequential order that place events in a meaningful way for definite odense and thus gives in sight about the world and peoples experience of it" በማለት ነው። ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ተረክ ነገሮችና ሁነቶች በተለጣጥቆ (በቅደምተከተል) የሚተረኩበት ሀቲት ነው። ተረክን ስናጠና ትኩረት የምናደርግባቸው ነጥቦች አሉ። እነሱም የተረኩ መልዕክት፣ ተረኩ እንዲፈጠር ወይም እንዲተረክ የሚያደርጉ ሰበቦች እንዲሁም ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሠጡት ትርጉም ናቸው (Degh, 1972: 54)።

ለBascom (1965፡3) ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረክ ሚቶችን (Myths)፣ አፈ-ታሪኮችን (Legends) እና ተረቶችን (Folktales) አቅፎ የሚይዝ የስነቃል አንድ ክፍል ነው። በሌላ በኩል Oring ቃላዊ ዝርው ተረክ በሁነቶችና በድርጊቶች የተዋቀረና የአንድን ማህበረሰብ ባህል ለማስተላለፍ የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ ይገልጻሉ (1986:122)። ስለዚህ ቃላዊ ዝርው ተረክ በቋንቋ የሚገለጽ፣ በቃል የሚተላለፍ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል የተዋቀረ ታሪክ ያለው፣ በታሪኩ ውስጥ ያለውን ድርጊት የሚፈጽሙ ገጸባህሪያት ያሉት የድርጊቶችና ሁነቶች ትረካ ነው። በዚህም አንድ ማህበረሰብ ባህሉን፣ ወጉንና ልማዱን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍበት አይነተኛ መሳሪያ ነው።

### 2.2.1.2 የቃላዊ ዝርው ተረክ ተግባር

ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ጥቅም የጎላ ነው። Bascom (1954) የፎክሎርን ተግባር ሲያብራሩ በአራት በመመደብ ነው። እነሱም አስተምሮታዊ ተግባር፣ የማጠናከርና የመትከል ተግባር፣ የመቆጣጠርና የመግታት ተግባር እና የባህልን ጠቀሜታ የመግለጽ ተግባር ናቸው።

ፈቃደ (1984፡13) የቃል ተረክን ተግባር ሲገልጹ "የዛሬው ትውልድ የቆመበትን መሰረት ለማወቅ፣ ትናንትን ማወቅም ዛሬን ለማወቅና የነገውንም መንገድ ለማቀድ ስለሚበጅ አፋዊ ኪነተ ቃል እና አፋዊ ታሪክ አንድን ህዝብ የማወቂያ እና የዚያን ህዝብ መለወጫ መንገድ መፈለጊያ መሳሪያ ሊሆን ይችላል።" በማለት ነው። ከዚህ አገላለፅ መገንዘብ እንደሚቻለው ተረክ ያለፈን ጊዜ ተመክሮ አሁን እያለነው ላለው ህይወት የምናውልበትና መጪውንም የምንተነብይበት ዘዴ ነው። ምክንያቱም ያለፈው ጊዜ ሲተረክ ያሁኑን ስለሚያነጽር ያለፈውንና

ያሁኑን ይዞ መጪውን መተንበይ ስለሚቻል ነው። ከዚህም ባሻገር የአንድ ማህበረሰብ ማንነት የሚንፀባረቅበት መስታወት ነው።

የቃል ተረክ በተለይ ፅሁፍ ለሌላቸው ማህበረሰቦች ታሪካቸውን ሰንደው የሚያስቀምጡበት መሳሪያ ነው (Fludernik 2009:1)። ስለዚህ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ ተከስተው የነበሩ ማናቸውም አይነት ታሪኮች (የጦርነት፣ የረሀብ፣ የጥጋብ፣ የስደት፣ የሃይማኖት፣ የፍቅር...) ለመጪው ትውልድ ይደርሱ ዘንድ ተጭነው የሚጓዙበት መርከብ ነው።

2.2.2 ማንነት (Identity)

Hall (2000:16) ማንነትን ሲገልፁ "identification referring to a construction and a process never completed that requires discursive work" በማለት ነው። እዚህ አገላለፅ ውስጥ ሊጤኑ የሚገባቸው ሁለት ጉዳዮች አሉ። አንደኛው ማንነት የሚገነባ የመሆኑ ጉዳይ ነው። የአንድ ማህበረሰብ ማንነት ማህበረሰቡ ሲፈጠር አብሮ የሚፈጠር ሳይሆን ማህበረሰቡ በቋንቋ የሚገነባው ጉዳይ ነው። ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ማንነት ሂደት የመሆኑ ጉዳይ ነው። የአንድ ማህበረሰብ ማንነት በአንድ አኳኋን ረግቶ የሚቀመጥ ሳይሆን ሁሌም በሂደትና በለውጥ ውስጥ ያለ ነው።

Mathisen (1993: 37) እንደሚያስረዱት ባህላዊ ማንነት ሁለት ነገሮችን አጣምሮ የሚይዝ ነው። አንደኛው አንድ ነገር በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ በአንፃራዊነት ለረጅም ጊዜ የመቆየት ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሌሎች ማህበረሰቦች የተለዩ መሆንን የመግለፅ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ የሆኑ ጉዳዮች በማህበረሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ሊሆኑ ይገባል። ከዚህም ጎን ለጎን በዙሪያው ካሉ ሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ያሉ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የአኗኗርና የማናቸውም አይነት ልማዶች ልዩነት መፍጠሪያዎችም ናቸው።

Erikson (1968: 50) ማንነትን ሲገልጹ "identity is based on two simultaneous observation: the perception of selfsameness and continuity of one's existence in time and space and the perception of the fact that others recognize one's sameness and continuity." በማለት ነው። ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ማንነት

ሲነሳ ሁለት የማይነጣጠሉ ነገሮች አብረው ይነሳሉ፡፡ እነሱም አንድነት/ተመሳስሎ (Sameness) እና ቀጣይነት (continuity) ናቸው፡፡ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት እንዲህ ነው ለማለት በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ የጋራ የሆነ መገለጫ ባህሪ ሊኖርይገባል፡፡ ይህ ባህሪ ደግሞ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በአንጻራዊነት ለረጅም ጊዜ የቆየ ሊሆን ይገባል፡፡

እኚህ ሰው፣ Erikson ማንነት የተመሳስሎ ጉዳይ (sameness) እንደሆነ ሲገልጹ፣ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ተመሳስሎ/አንድነት ለዚያው ማህበረሰብ ማንነት ሲሆን ይህ ተመሳስሎ/አንድነት ማህበረሰቡን ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚለየው ነው፡፡

2.2.3 ማንነትና ተረክ (Identity and narrative)

ማንነት ሰዎች "ማን ነን" ወይም "ምንድን ነን" ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመሥጠት የሚሞክሩበት ሲሆን ይህ መልስ የሚፈጠረውም ሆነ የሚገነባው በተረክ ነው (Lwis and Sandra 2001)፡፡

የፎክሎር ጥናት ከምደ ባና ከ ይዘት ትንተ ና ብቻ ተ ላቆ የተ ረኮችን ትርጉም በመተ ንተን የማህበረሰቡን ማንነት ለማሳየት መሞከር ከጀመረ ውሎ አድሯል (Mathisen 1993: 35)፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ማንነቱን የሚገነባውም ሆነ የሚገልፀው በቋንቋ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ Krosktity (2000:111) ሲያስረዱ "Identity is the linguistic construction of membership in one or more social group or categories" ይላሉ፡፡ ስለዚህ ማንነት በቋንቋ የሚገነባና የሚገለፅ ራስን የመግለፅ ጉዳይ ነው፡፡ በቋንቋ ከሚገለፁ ነገሮች መካከል ደግሞ አንዱ ተረክ ነው፡፡ ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ተረክ በማጤን የተረኩ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ ማንነት መገንዘብ ይቻላል፡፡

Dundes (1986:132) እንደሚገልፁት ፎክሎር ስለአንድ ማህበረሰብ ማንነት ማወቅ ለሚሹ ተመራማሪዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡ ይህን ግላዌ Mathisen (1993:35) ሲያጠናክሩ ፎክሎር የጋራ ማንነት መገለጫ እንደሆነ በመግለፅ ነው፡፡ የፎክሎር አንድ ምድብ በሆነው ስነቃል ውስጥ የሚካተተው ዝርው የቃል ተረክም እንደፎክሎርነቱ የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ የሆነው ማንነት መከሠቻ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

Sims (1963:168) እንደሚያስረዱት ተረኮች የማህበረሰቡን አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህን ተረኮች በማጤን የማህበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ የአለም አተያይ (ርዕዮተአለም)፣ ፍልስፍናና መሠል የማንነት መገለጫዎች ማወቅ ይቻላል። ስለዚህ ተረክና ማንነት በእጅጉ ቁርኝት ያላቸውና አንዱ ለሌላው ህልውና ምክንያቶች ናቸው። ማንነት የሚፀነሰው፣ የሚወለደውም ሆነ የሚያድገው በተረክ ነው። በሌላ በኩል ተረክ ይኖር ዘንድ የማህበረሰቡ ማንነትን የመግለፅ ጉጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው።

ማንነትና ተረክ በእጅጉ ቁርኝት ያላቸው ናቸው። Gover ይህን ጉዳይ ሲያስረዱ "Narrative and identity are not separable entities but, instead, serve to mutually constitute one another" በማለት ነው። ማንነት ይፈጠርና ይገነባ ዘንድ ተረክ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ መገንዘብ ይቻላል። ማንኛውም ማህበረሰብ "እኛ እንዲህ ነን" ብሎ ማንነቱን የሚገነባው በተረኮቹ ነው።

Kerby (1991:3) የተረክና የማንነትን መስተጋብር ሲገልፁ፣"Narratives are a primary embodiment of our understanding of the world, of experience, and ultimately of ourselves." ይላሉ። ተረክ ማንነትን የምንገነባበት ዋና መሣሪያ ከመሆኑም ባሻገር አንድ ማህበረሰብ ማንነቱን ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ድልድይ ነው። Fina (2003:22) ይህን ጉዳይ ሲያጠናክሩ "story telling is a type of discourse practice that involves the reflection, negotiation and constitution of identities." በማለት ነው። ስለዚህ ተረክ የማንነት መፍጠሪያ፣ መገንቢያና ማንፀባረቂያ ነው።

### 2.2.4 ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional approach)

2.2.4 ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional approach)

በፎክሎር ጥናት ውስጥ በርካታ አቀራረቦች አሉ። ከእነዚህ አቀራረቦች መካከል ተግባራዊ (functional) የተባለው አቀራረብ በዚህ ክፍል ይብራራል። ይህ ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው አንድ የፎክሎር አይነት (genre) በማህበረሰቡ ውስጥ ያለን ተግባር መመርመር ላይ ነው (Sims, 2005:175)። አንድ የፎክሎር ተመራማሪ በዚህ ዘዴ ጥናት የሚያከናውን ከሆነ የፎክሎሩ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ በፈጠረው ፎክሎር ምን መልዕክት

እንደሚያስተላልፍበትና ፎክሎሩ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተግባር ለማወቅ ይጥራል (Oring, 1986:68)።

እንደ Bascom (1965:290-294) ፎክሎር አራት ተግባራት አሉት። ከነዚህም የመጀመሪያው አስተምሮታዊ ተግባር ነው (1965፡293)። ማንኛውም ማህበረሰብ ትውልዱን በፎክሎር ያስተምራል። መጭውን ትውልድ ስለአለምና በውስጧ ስላሉ ማናቸውም ነገሮች የሚያስተምርበት መን ገድ ነው። በሁለተ ኛነት የሚያስቀምጡ ት የፎክሎር ተ ግባር ደግሞ ማምለጫ መሆንን ነው (1965፡290)። ፎክሎር አንድ ማህበረሰብ አሰልቺ ከሆነው አለም የሚያመልጥበት መንገድ ነው። ከዚህም ባሻገር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ ካሉ አንዳንድ አሰልቺ ስርአቶች የሚያመልጡበት ዘዴ ነው። በሶስተኛነት የሚያስቀምጡት የፎክሎር ተግባር ማጠናከርና መትከል ነው (1965፡294)። አንድ ማህበረሰብ በባህሉ ውስጥ ይሁነኝ ብሎ የሚቀበለውን ስርአት እንዲቀጥል የሚያደርገው በዚሁ በፎክሎር ነው። በዚህም ቀጣይነት እንዲኖረው የሚፈልገውን ልማድ ለቀጣይ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ዘዴ ነው። በአራተኛ ላይ ያሰፈሩት ተግባር ደግሞ ራሱን ባህልን የመገምገሚያ መሳሪያ መሆንን ነው (1965፡292)። ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በተለይም ስነ ቃል የማህበረሰቡን ባህል በመገምገም እንዲቀጥል የማይፈልገውን ልማድ ነቅሶ ያስወግዳል። ቃላዊ ዝርው ተረክም እንደ የፎክሎር ዘርፍነቱ እነዚህ ሁሉ ፋይዳዎች አሉት።

ከዚህ በተጨማሪ ተረክ ማንነትን የመፍጠር፣ የመገንባትና የማንፀባረቅ (የመግለፅ) ተግባር አለው። የአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ማንነት የሚፀነሰው፣ የሚገነባውም ሆነ የሚገለፀው በተረክ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## የቅማንት ማህበረሰብ[1] ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ቅማንት ማህበረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ ገለፃ ይደረጋል፡፡ በተለይም ስለማህበረሰቡ ጥንተ አመጣጥ፣ ስለማህበረሰቡ ቋንቋ እና ሀይማኖት፣ ስለማህበረሰቡ አስተዳደራዊ ሁኔታ እንዲሁም ስለማህበረሰቡ መተዳደሪያ (ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ) በመጠኑ ይዳሰሳል፡፡

### 3.1 የቅማንት ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ

ስለ ቅማንት ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ ከመወጋቱ በፊት ማህበረሰቡ "ቅማንት" የሚለውን ስያሜ እንዴት እንዳገኘው ማንሣት ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ ስያሜ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሦስት ናቸው፡፡

አንደኛው "ከመአንተ" ከሚል የግዕዝ ቃል የመጣ ነው የሚል ሲሆን የቅማንት አባትና እናት (አይነርና እንተላ) በከርከር ጫካ ሲኖሩ አንድ ሰው አያቸውና "አንተ ማን ነህ?" ቢላቸው በግዕዝኛ "ከመአንተ" አሉ-እንዳንተ ሰው ለማለት፡፡

ሁለተኛው አተያይ ደግሞ ከመጀመሪያው ጋር አንድ አይነት ሆኖ የቃሉ መሠረት ግዕዝ ነው የሚለውን አይቀበልም፡፡ ምክንያቱም የቅማንት ቋንቋ ከግዕዝ ቋንቋ የቀደመ በመሆኑ ቃሉን ከግዕዝ አልወሰደውም (ነጋ፣ 1993፡2)፡፡ በቅማንተኛ "ክመንቲ" ማለት እንዳንተው ሰው ማለት ነው፡፡ ማህበረሰቡ "ክመንቲ" ሲባል ቋንቋው ደግሞ ክመንትነይ ይባል ነበር፡፡[2] ዘላለም (2003) ስለ ቋንቋቸው ሲፅፍም "kemantney" ማለቱ ከዚያ የሰበሰበው መረጃ ወደዚህ ስያሜ እንዲያዘነብል አድርጎት ሊሆን ይችላል፡፡

---

[1]የማህበረሰቡ ተወላጆች (ለምሳሌ ነጋ ጌጤ) ማህበረሰብ የሚለውን አይወዱትም፡፡ ምክንያቱም የህዝቡ ብዛትና ታሪካዊ ሁኔታ መንግስት ብሔረሰብ ብሎ የሚያዋቅርበትን መስፈርት ከማሟላትም በላይ ስለሆነ ቢያንስ ብሄረሰብ ነን ይላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት እስከተካሄደበት ድረስ መንግሥት የብሔረሰብነት እውቅና ስላልሠጣቸው ማህበረሰብ የሚለውን ቃል መጠቀም ግድ ሆኗል፡፡

[2]አዲሱ የሚባል መረጃ ሰጪ እንደነገረኝ

ሦስተኛው አመለካከት ደግሞ ቅማንት የሚለው ቃል በቅርብ ጊዜ የአማራው ብሔረሰብ የቅማንትን ማህበረሰብ የሚጠራበት ስያሜ ነው፡፡ በቅማንት ቋንቋ ውስጥ ከናካቴው [ቅ] የሚባል ድምፅ የለም (ነጋ፣1993፡2)፡፡ ማህበረሰቡ ይህን ስም ከማግኘቱ በፊት "ክመእንት" ይባል ነበር፡፡ ትርጉሙም አንተ-ካም ማለት ነው (ነጋ 1993፡2)፡፡ በዚሁ መፅሀፍ እንደተገለፀው የቅማንቶች የዘር ምንጭ የኖህ ልጅ ካም ነው፡፡ ካም ደግሞ ኩሽን፣ ምዝራይብንና ከነዓንን ወለደ፡፡ ስለዚህ የካም ዘሮች ስለሆኑ ይህ ስያሜ እንደተሠጣቸውና የቃሉ መሠረትም ቅማንትኛ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ስለ ቅማንት ህዝብ ጥንተ አመጣጥ የተለያዩ ነገሮች ሲባሉ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ መላምቶች አንዳንዶቹ ተራ አሉባልታ የሚመስሉ ነገር ግን ከታሪኩ ተናጋሪ አንፃር የማንነት ልዩነት ለማምጣት ታስቦ የሚነገሩ ናቸው፡፡ የዚህን ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ በተመለከተ ያሉትን አመለካከቶች ጠቅለል አድርጐ በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው ከእንጨት የመጡ የእንጨት ፍሬዎች ናቸው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከከነዓን ምድር ተሰደው የመጡ ናቸው የሚል ነው፡፡ ሦስተኛው አስተሳሰብ ደግሞ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩና ከየትም ያልመጡ ናቸው የሚል ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

በአካባቢያቸው ያለው የአማራ ማህበረሰብ እስካሁንም ድረስ ከእንጨት እንደመጡና የቅማንት የዘር ሀረግ መነሻ እንጨት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ የአማራው ማህበረሰብ እንዲህ የሚልበትን ምክንያት የሚያስረዳበት አፈ-ታሪክ አለው፡፡

> *ድሮ የአማራው ህዝብ የቅማንትን ህዝብ ለማጥቃት ያሉበት ጫካ ድረስ ይሄዳል፡፡ ይህን የተረዳው የቅማንት ህዝብ በሚኖርበት ጫካ ውስጥ ያለውን ዛፍ ሁሉ በቁመቱ ልክ እየፈለፈለ በውስጡ ይሸሽግ ነበር፡፡ በኋላም የአማራው ህዝብ ሲፈልግ ያጣውና ሲመለስ ሲል ቅማንቱ ከተሸሸገበት ፍልፍል ዛፍ ውስጥ በመውጣት የአማራውን ህዝብ ያጠቃዋል፡፡ ያኔ ያመለጡት ቅማንቱን ከእንጨት ውስጥ ሲወጣ አይተውታልና የእንጨት ልጅ ነው አሉት፡፡ (አዲሱ 2004፣ጎንደር፤አቶ አበራ 2004፣ትክል ድንጋይ)*

በማለት አማራው ለምን የእንጨት ዘር እንደሚላቸው ያስረዳሉ፡፡

አብዛኛው የጐንደር ህዝብ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ በመሆኑ የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች አዳምና ሔዋን እንደሆኑ፣ አሁን በአለም ላይ ያለው ሰው ሁሉ መሠረታቸው

አዳምና ሔዋን እንደሆኑ ያምናል። በዚህም አማራው የቅማንትን ማህበረሰብ ከእንጨት የተገኘ፣ የእንጨት ፍሬ ማለቱ ነገሩን ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል።

ሌላው ስለቅማንት ህዝብ ጥንተ አመጣጥ የሚነገረው ደግሞ ከከነዓን ምድር የመጣ መሆኑ ነው። አለቃ ታዬ (1920፡9-11) የቅማንትን ህዝብ ጥንተ አመጣጥ ሲያስረዱ የቅማንቶች አባት አይነር ሚስቱን እንተላን ይዞ ከከነዓን ምድር ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣና ሰው ሣያየው በከርከር ዱር በርሃ ፍራፍሬ እየለቀመና አያደነ መኖር እንደጀመረ ነው። አለቃ ታዬ በዚሁ መፅሀፍ እንደገለፁት የቅማንት ህዝብ በሰሜን ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሰፋሪ ነው። ይህን ጉዳይ ሲያስረዱ እንዲህ በማለት ነው።

> *የቅማንቶች መኖሪያ በከርከር፣ በጭልጋ፣ በጋላገር፣ በቦባ፣ በኮሶጌ፣ በጀኒፈንቀራ፣ በዙሪያቸውም ባሉ አገሮች ነው። ይህ ሁሉ አገርስ አፄ ፋሲል የጐንደርን ከተማ ሳይቆረቁሩ በፊት አስቀድሞ የክርስቲያን ህዝብ አልነበረበትምን፣ ወይስ አፄ ፋሲል ክርስቲያኑን ነቅለው አገሩን ለቅማንት ሠጡትን ብለን ለመጠየቅ ግድ ነው። ለዚህ ጥያቄ አናውቅም ተማለት በቀር ምላሽ አይገኝለትም። እኛ ግን እነሆን አሁን የተቆጠሩትን የቅማንት አገሮች ጥንት ከመሠረት አገራቸው እንደነበረ በኋላ ግን በዘመነ ክርስትና የክርስቲያን ነገስታት ቅማንትን የክርስቲያን ዜጋ አድርገው በላያቸው ስሪ እንደሠሩባቸው ባገራቸውም መሀከል ጉልተኛ ሆኖ ክርስቲያን እንደገባባቸውም ባገራቸውም ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት እንደተሠሩባቸው እናውቃለንና ብዙ ታሪክ ፃፎች እንደሚሉ የቅማንቶች አባት አይነር በፊት እንደመጣ አገሩንም ይዞ እንደነበረ ነገራችንን በዚህ እናፀናለን (አለቃ ታዬ 1920፣10-11)።*

ከዚህ ፅሁፍ መረዳት እንደሚቻለው በሰሜን ኢትዮጵያ በተጠቀሱት ስፍራዎች ቀድመው ይኖሩ የነበሩት ቅማንቶች ናቸው። ነገር ግን የእነዚህ የቅማንቶች አባት ከከንዓን የመጣ ነው።

ሶስተኛው ስለቅማንት ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ ያለው አስተሳሰብ ደግሞ ከጥንት ጀምሮ እዚሁ የበቀለ እንጂ ከየትም የመጣ አይደለም የሚለው ነው። ይህ ሃሳብ በአብዛኛው የቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ይህን የሚሉበትን የተለያዩ ምክንያቶች ያስቀምጣሉ። ኢትዮጵያ የሠው ዘር መገኛ እንደሆነች እነ ድንቅነሽና አርዲን አስረጅ በማድረግ ከገለፁ በኋላ እኛ ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን በመሆናችን እዚሁ የተፈጠርን እንጂ ከየትም የመጣን አይደለንም[3] ይላሉ። ሌላው ደግሞ የቋንቋ ጉዳይ ነው። የእስራኤላውያን ቋንቋ

---

[3]አዲሱ ታረቀኝ የተባለው መረጃ ሰጪ እንደሚያብራራው

ኢብራይስጥ ነው፣ ኢብራይስጥ ደግሞ የሴም ቋንቋ ዝርያ ነው። የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋ ደግሞ የኩሽ ነው። ስለዚህ ከእስራኤል ቢመጡ ኖሮ የኩሽ ቋንቋን ሳይሆን የሴም ቋንቋን ይናገሩ ነበር።[4] ይህን ጉዳይ ተክለፃድቅ መኩሪያም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ኑብያ-አክሱም-ዛጉዬ እስከ አፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት በሚለው መፅሃፋቸው ገጽ 392 ላይ አለቃ ታዬ የቅማንትን ዘር ሲያስረዱ ከእስራኤል መነሳታቸውን ባለመቀበል ይሞግታሉ። በመፅሀፉ እንደተገለፀውም "በዚህ አይነት አለቃ ታዬ የአገውን ዘር ከዳዊት ከእስራኤል ልጅ የወረደ ማድረጋቸው ነው። ይኸም ቢሆን የአገው ዘር ኩሽ መሆኑ ቀርቶ ሴማዊ ሲሆን ነው። የዳዊት የልጅ ልጅ ዘር ከሆነም ከዳግማዊ ሚኒሊክ ጋር ወጥቶ የአገውና የላስታ ንጉስ ተብሎ ከነገሠ ከፈላሻ ልዩነት የለውም። ልማዱም ሃይማኖቱም ከፈላሻዎች ሊለይ አይችልም ነበር።"ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የአገው ዘር የሆነው የቅማንት ማህበረሰብ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ የመጣ እንዳልሆነ ነው።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በሰሜን ኢትዮጵያ መጀመሪያ የታየው የሠው ዘር የቅማንት ማህበረሰብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህን ጉዳይ Gamst (1969፣1) ሲያስረዱ የመጀመሪያዎቹ የሠሜንና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ሠፋሪ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ፣ የአገው ህዝብ አካል የሆነው የቅማንት ማህበረሰብ ነው ይላሉ። እኚህ ሰው በዚሁ መፅሀፍ ገጽ 19 ላይም እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ስሌት በ900 ዓ.ም አካባቢ የሠሜን ህዝብ በከፊል ተከዜን ተሻግሮ አገዎችን እየገፋ መስፈር መቀጠሉንና ይህ ህዝብ ደግሞ አማራ እንደሆነ እንዲሁም ተከዜን ሳይሻገሩ እዚያው የቀሩት ኢትዮጵያውያን ደግሞ የአሁኖቹ የትግሬ ህዝብ ቅድመ-ቅድመ አያቶች እንደሆኑ ያስረዳሉ። በዚህም ቅማንት ሠፍሮ ይኖርበት በነበረው ምድር ላይ የአማራው ህዝብ በኋላ መጥቶ እንደተቀላቀለበት መገንዘብ ይቻላል።

## 3.2 የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋና ሃይማኖት

### 3.2.1 የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋ

ዘላለም(2003)Hetzro (1969)ን ጠቅሶ እንደሚያስረዳው የአገው ቋንቋ በሰሜን ምስራቅና በሰሜን ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍል በስፋት ይነገር ነበር። ከአገው ቋንቋዎች መካከል አንዱ የሆነው ቅማንትኛ ቋንቋም የቅማንት ህዝብ መግባቢያ ነበር። ምንም እንኳን ቋንቋው አሁን ባለበት ሁኔታ እየተዳከመ የመጣ ቢሆንም የቅማንትኛ ቋንቋ በአሁኑ ጊዜ በጭልጋ ዝቅተኛ

[4] አዲሱ ታረቀኝ የተባው መረጃ ሠጪ እንደሚገልፀው

ቦታዎች (lowland) ውስጥ ባሉ መንደሮች ያለ እንደሆነ Zelealem (2003:31) ይገልፃል፡፡ ያም ቢሆን አዋቂዎች ቋንቋውን ያውቁታል እንጂ ለተግባቦት አላማ ይገለገሉበታል ማለት እንዳልሆነ በዚሁ መፅሀፍ ተጠቅሷል፡፡

እንደ 1994 የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ቅማንተኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ($L_1$) የሚናገሩት 1,625 ሰዎች ሲሆኑ 3,450 ሰዎች ደግሞ በሁለተኛ ቋንቋነት ($L_2$) ይግባቡበታል፡፡ ይህ ቁጥር 172,291 ከሆነው የቅማንት ህዝብ አንፃር ሲታይ ህዝቡ በዙሪያው ካለው አማራ ጋር ባለው የረጅም ጊዜ ግንኙነት ተፅዕኖ ቋንቋው እየጠፋ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

Zelealem (2003) እንደሚያስረዳው ለቅማንትኛ ቋንቋ መዳከም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ በርካታ ተፈጥሮአዊና ታሪካዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህም ምክንያቶች አንዱ የጭልጋና የጎንደር አቀማመጥ ነው፡፡ በ17ኛው እና 18ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ ነገስታት የመናገሻ ከተማቸውን ጎንደር ማድረጋቸው በቅማንትኛ ቋንቋና ባህል ላይ ተፅዕኖ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ጎንደር ከ1630ዎቹ-1850ዎቹ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ እንደነበረች ዘላለም Sasse 1992b:73ን በመጥቀስ ያስረዳል፡፡ በዚህም በከተማዋ ዙሪያ ገባ ያሉት ቅማንቶች የአማርኛ ቋንቋ ተፅዕኖ እንዲወድቅባቸው ሆኑ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል በሚካሄደው ንግድ አማራው ወደ መተማ ለመጓዝ የጭልጋን ምድር አልፎ ይሄድ ስለነበር ሁለቱ ህዝቦች እንዲገናኙ እድል ፈጥሯል (Zelealem 2003:33-35)፡፡ በኋላም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከጎንደር መተማ ያለውን መንገድ ሲያሰሩ አንድም በመንገዱ ስራ ወቅት በኋላም መንገዱ ካለቀ በኋላ በጉዞ ወቅት (Transport) ሁለቱ ህዝቦች በመገናኘታቸው አማርኛን መልመድ ጀመሩ፡፡

ሌላው ምክንያት የክርስትና እምነት መስፋፋትና የዘመናዊ ትምህርት መጀመር እንደሆነ Zelealem (2003:37) ያስረዳል፡፡ ስልጣኔ በተለይም ትምህርት (መንፈሳዊውም አለማዊውም) በቅማንት ምድር መጀመሩ ለቅማንትኛ ቋንቋ መዳከም አንዱ ምክንያት ነው፡፡

በጭልጋ ዘመናዊ ትምህርት የተስፋፋው በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በርካታ የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተከፈቱ ቢሆንም በየትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የመማር ማስተማሩ ስራ የሚከናወነው በአማርኛ ቋንቋ

ነው፡፡ ይህ ደግሞ በቅማንት ህዝብ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ እንዲስፋፋና የቅማንትኛ ቋንቋ እንዲዳከም በር ከፍቷል (Zelealem 2003:38)፡፡

በይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት (1270-1285) መጀመሪያ የቤተክርስቲያን ግንባታ በኢትዮጵያ እንደተጀመረ Huntingford et al (1954) ያስረዳሉ፡፡ የክርስትና እምነት መስፋፋት ደግሞ የቅማንት ወጣት ወንዶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በዲያቆንነትና በቄስነት እንዲሳተፉ አድርጓቸዋል (Zelealem 2003:39)፡፡ በዚህም አስቀድሞ የነበራቸውን ቋንቋ እንዲተዉ ሆነዋል፡፡

ለቅማንት ቋንቋ መዳከም እንደ ምክንያት የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ፖለቲካዊ ተሳትፎ (political involvement) ነው፡፡ ዘላለም Halevy (1887)ን ጠቅሶ እንደሚያስረዳው በዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመን ትልልቅ ባለስልጣኖችና የጦር አመራሮች የነበሩት የቅማንት ማህበረሰቦች ናቸው፡፡ ይህን ጉዳይ Quirin (1977) ሲያጠናክሩ ቴዎድሮስን በሽፍትነት ወቅት ተቀላቅለው የነበሩት የቅማንት ማህበረሰቦች በኋላ ወደ ጦር አለቅነትና አስተዳደራዊ ማዕረግ እንደተሸጋገሩ በመግለፅ ነው፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ የቴዎድሮስ የጦር መሪ የነበረው የጮንጮቄ ተወላጅ ገልሙ ነበር፡፡ በዚህ መንገድ ወደ ፖለቲካዊ ጉራ መቀላቀላቸው በቤተመንግስት አካባቢ የሚነገረውን የአማርኛን ቋንቋ እንዲለምዱና እንዲገለገሉበት አድርጓቸዋል፡፡

ሌላው በምክንያትነት የሚነሳው መሠረታዊ ጉዳይ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ላዕከማርያም የሚባሉ ቄስ ወደ ቅማንት ህዝብ በመላክ ህዝቡ የኦርቶዶክስ እምነትን ይቀበል ዘንድ እንዲጠመቅ ማድረጋቸው ነው፡፡[5]

በእነዚህና መሠል ምክንያቶች የቅማንትኛ ቋንቋ በመዳከም ላይ ነው፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ አብዛኛው ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነው፡፡

---

[5]ተስፋዬ፣ ወንበር ሙሉነህ መርሻ፣ ቄስ አማረ ሙሉነህ፣ ነጋ ጌጤና አዲሱ ታረቀኝ የተባሉ መረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝና በ Zelealem 2003 እንደተገለፀው፡፡

6 ቅማንቶች አለምን ሁሉ የፈጠረ ነው ብለው የሚያምኑት በሰማይ ያለ አምላካቸው ነው፡፡

### 3.2.2 የቅማንት ማህበረሰብ ሀይማኖት

Gamst (1967) እንደሚያስረዱት በሠሜን ማዕከላዊ ኢትዮጵያ የእስልምና ሀይማኖት ከመምጣቱ በፊት በቅደም ተከተል የተከሠቱ ሦሥት አይነት ሀይማኖቶች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ በጣም ጥንታዊ የሆነው የጥንት አገዎች በተለያየ መልክ ያመልኩት የነበረውና እስከ ቅርብ ጊዜም የአሁኖቹ የአገው ህዝቦች ያምኑበት የነበረው አረማዊ-አገው እየተባለ የሚታወቀው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከሁለት ሺ. አመት በፊት በሠሜን ኢትዮጵያ የተሠራጨው የእብራውያን ሀይማኖት (ኦሪት) ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ (ከአንድ ሺ. ስድስት መቶ አመት በፊት) የተስፋፋው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ነው፡፡ በዚሁ መፅሀፍ እንደተገለፀው የቅማንት ህዝብ ሀይማኖት በአብዛኛው አረማዊ-አገው እንደሆነና በተጨማሪም የእብራዊ (ኦሪት) ሀይማኖት እምነት በውስጡ ያቀፈና አንዳንድ የክርስቲያን እምነቶችን ያካተተ ነው፡፡

የቅማንት ህዝብ በአንድ እግዚአብሔር እንደሚያምን Gamst (1967) ይገልፃሉ፡፡ እንደ ቅማንት ህዝብ ሀይማኖት (ሀገልቦና)ምዝገና[6]ከሠማየ ሠማያት ወርዶ ከድንግል በመብረቅ የወለደው አይደረኪ. የሚባል ኃይለኛ ሰው አለ፡፡[7] አለቃ ታዬ ስለ አይነር እና እንተላ የዘር ሀረግ ሲያስረዱ አይነር ከሚስቱ ከእንተላ ዘጠኝ ወንዶችና አምስት ሴቶች ልጆች እንደወለደና ከነዚህም መካከል አንዱ አይደረኪ. እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም አይደረኪን ቅማንቶች ከእናትና አባት የተገኘ ሳይሆን ከሰማይ የወረደ ነው እንደሚሉና ይህ "ተራ ተረት" እንደሆነ ፅፈዋል፡፡ ይህን ጉዳይ በማንነት ተረክ ትንተና ላይ የምመለስበት በመሆኑ ከዚህ በላይ አልሄድበት፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለወንድ ከማርያም እንደተወለደ አለቃ ታዬ በመፅሀፋቸው በተደጋጋሚ በሚጠቅሱት መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ሰፍሯል፡፡ በዚያን ዘመንም እየሱስን የዮሴፍ ልጅ እንደሆነ የሚያምኑም ነበሩ፡፡ ለእምነቱ ተከታይ ግን ይህ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ የሌላን ህዝብ እምነት ተረት ማለት ተገቢ. አይደለም፡፡ ቅማንቶችም ቢ.ሆኑ አይደረኪ. አባት የለውም እንጂ. እናት የለውም አይሉም፡፡

የቅማንት ህዝብ ሀይማኖት እጅግ ሚስጥራዊ እንደሆነ የተለያዩ ሰዎች ይገልፃሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን አብዛኛው የቅማንት ህዝብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ሆኗል፡፡ ዘላለም Halevy (1877)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዳው የቅማንት ህዝብ ወደ ክርስትና

---

[7]ቄስ አማረ ሙሉነህ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደነገሩኝ

እምነት የተቀየረው በፋሲለደስ ዘመን (1632-1667) ነው፡፡ Bruce የተባሉ ተጓዥ የአባይን ምንጭ ለማግኘት ባደረጉት ጉዞ ወቅት የታዘቡትን በፃፉበት መፅሀፍ እንደገለፁት የቅማንት ህዝብ በ1660ዎቹ በአፄ ፋሲል ዘመን በክርስትና ሀይማኖት የተጠመቁ ቢሆኑም ክርስትናን አጥብቀው አልያዙም፡፡ ይልቁንም ክርስቲያኑን እንደ እርኩስ ይቆጥሩት ነበር (Bruce 1790: 4፣275)፡፡ ስለዚህ በፋሲለደስ ዘመነ መንግስት የክርስትና እምነትን እንዲቀበሉ ቢደረጉም አብዛኞቹ እምነቱን ተቀብለው አላሰረፁትም ነበር፡፡

በኋላ ግን በ1950ዎቹ መጀመሪያ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ቄስ ላዕከማርያምን ልከው እንዲጠመቁ በማድረጋቸው አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትናን ተከታይ እንደሆነ የማህበረሰቡ አባላት ያስረዳሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ከ500 የማይበልጡ የእምነቱ ተከታዮች አሉ (Gamst 1967) ፡፡ የሀገ ልቦና እምነት ተከታዮች ለፀሎት ተግባር በሚገለገሉባቸው ድግናዎች[8] ዙሪያ በመሰብሰብ ዝናብ ሲጠፋ ወይም ከመጠን በላይ ሲዘንብ ይፀልያሉ፡፡ ሀይማኖታዊ ስርአቱ የሚከናወነው በቅማንትኛ ቋንቋ ሲሆን የራሱ ዜማና ስርአትም አለው፡፡ ቋንቋው በፅሁፍ ላይ ያልዋለ በመሆኑ ሀይማኖታዊ ስርአቱ የሚከወነው በቃል ብቻ ነው፡፡

ፀሎቱ ሲካሄድ ወንበሩ[9] በአጭር ወንበር መሠል ነገር ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ቄሶች ከፊት ለፊታቸው እየተወዛወዙ ይቀድሳሉ፡፡ ሴቶች ቆሎና ቂጣ ያዘጋጃሉ፡፡ አንድ ኪሎ የሚሆን ማር ከመሀል ይቀመጣል፡፡ ለመሠዋዕትነት የቀረቡ በግና ዶሮዎች በቄሶች ይሠዋሉ፡፡ ከዚያም የበጎቹ ምላስና የዶሮዎቹ አንድ አንድ እግር (የቀኝ) በእሳት ተጠብሶ ቄሶቹ ይቋደሱታል፡፡ ቆሎ፣ ቂጣና የተቀረው ስጋ ተጠብሶ በፀሎቱ ላይ የነበረው ምዕመን ሁሉ ይቃመሠዋል(ይርጋ 1994፡9)፡፡

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ደብረዘይት ብለው በሚያከብሩት የፋሲካ ፆም አጋማሽ ወቅት የቅማንት እምነት (ሀገልቦና) ተከታዮች ደግሞ ሽምኩላ (ከረመይኪኩና) የሚባል በአልን ያከብራሉ፡፡ በዚህ እለት ጀንበር ስታዘቀዝቅም በምድር ላይ በየትም አገር የሚበቅል ዘር ሁሉ

[8]ድግና ማለት ለፀሎት ተግባር የሚገለገሉበት ደን ነው፡፡
[9]ወንበር የሀይማኖቱ መሪ ማለት ነው፡፡

በሰፌድ ላይ ይቀላቀልና ወንበሩ አንድ ፊር[10] ታርሶላቸው ዘሩን በመዝራት በአለም ላይ ሁሉ እህል ተዘርቶ ይበቅል ዘንድ ይመርቃሉ፡፡ በህገልቦና እምነት መሠረት ወንበር አያርስም፡፡

## 3.3 የቅማንት ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ሁኔታ

የቅማንትን ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ሁኔታ በተመለከተ Gamst (1967) በሦሥት ደረጃ ከፍለው ያስቀምጡታል፡፡ ከታች ያለው ደረጃ የአዛውንቶች ሸንጎ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠር ማንኛውም አይነት ችግር መጀመሪያ ለመፈታት የሚሞከረው እዚህ ቦታ ላይ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ያለው የከፍተኛና ዝቅተኛ ቀሳውስት ጉባኤ ነው፡፡ በመጀመሪያው እርከን ላይ ሊፈታ ያልቻለ ችግር በዚህኛው እርከን ሊፈታ ይሞከራል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ያለው ደግሞ የህይማኖትና የፖለቲካ የበላይ የሆነው ወንበር ነው፡፡ ከላይ ባሉት ሁለት ደረጃዎች መፍትሔ ያላገኘ ጉዳይ የመጨረሻ እልባት የሚያገኘው እዚህኛው እርከን ላይ ነው፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ወንበሮች በተለያየ ቦታ ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ በጭልጋ፣ በከርከር፣ በትክል ድንጋይና ወዘተ፡፡ ከከርከር ውጪ ባሉት ወንበሮች የተሠጡ ውሳኔዎች በይግባኝ ወደ ከርከሩ ወንበር ሊመጡ ይችላሉ፡፡ የከርከሩ ውሳኔ ግን ይግባኝ የለውም፡፡[11]

አብዛኛው የቅማንት ህዝብ (በተለይ በገጠር ያለው) ይህን የአስተዳደር ስርአት ከመንግሥት የአስተዳደራዊ ስርአት ጐን ለጐን ይገለገልበታል፡፡

## 3.4 የቅማንት ማህበረሰብ መተዳደሪያ (ምጣኔ ሃብታዊ ሁኔታ)

በ1994 ዓ.ም በኢትዮጵያ በተደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት የቅማንት ህዝብ ቁጥር 172,291 ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 6,705 በከተማ ሲኖሩ የተቀሩት 165,586 ሰዎች ደግሞ በገጠር ይኖራሉ፡፡ በገጠር የሚኖረው ህዝብ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን በከተማ የሚኖረው ደግሞ በንግድና በመንግስት ሰራተኛነት ይተዳደራል፡፡

---

[10]በእርሻ ላይ ያለ  በማረሻ የተቆፈረ መስመር ነው፡፡ አራሹ ማረሻውን መሬት ተክሎ እያረሰ ከጥግ እስከ ጥግ ሲሄድ አንድ ፊር አረሰ ይባላል፡፡
[11]ወንበር መሉነህ መርሻ እንዳወጉኝ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ስለማንነት የሚነገሩ ዝርው የቃል ተረኮች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ከማህበረሰቡ የተሰበሰቡ ዝርው የቃል ተረኮች ትንታኔ ይሠጥባቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ተረኮቹ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያነሱ ቢሆኑም በዚህ ክፍል ትኩረት ተሠጥቶ ትንታኔ የሚሠጥባቸው ተረኮች ስለማህበረሰቡ ማንነት የሚያወሩት ናቸው፡፡ እንደ ተግባራዊ አቀራረብ አራማጆች ተረክ የተለያዩ ተግባራት አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ ማንነትን የመገንባትና የመግለፅ ተግባር አንዱ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍም ትኩረት የሚሰጠው ለዚሁ ተግባር ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት በስፋት እንደተገለፀው ተረክና ማንነት የሚነጣጠሉ ጉዳዮች አይደሉም፡፡ የማንነት መፈጠሪያው፣ መገልመሻውም ሆነ መገለጫው ተረክ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራንን (Gover, Miller, Potts, Fung, Hoogstra, Fina…) በመጥቀስ በቀደመው ክፍል ተገልጿል፡፡

ማህበረሰቡ ተረኮቹን ቦድኖ የማይወይም በመሆኑ በአካባቢያዊ ምደባ (indigenous classification) ለመክፈል አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ከማህበረሰቡ ከተሠበሠቡት ተረኮች ውስጥ ማንነትን መሠረት ነገራቸው ያደረጉትን ለብቻ በመለየት ትንታኔ ለመስጠት ይሞከራል፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ማንነት ሲገለፅ ያ ማህበረሰብ ከአጐራባቾቹ ማህበረሰቦች ጋር ያለው የቋንቋ፣ የሃይማኖትና መሰል ባህላዊ ልዩነቶች ናቸው፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ግን ከአጐራባቹ ከአማራ ማህበረሰብ ጋር የቋንቋ ልዩነት ስለሌለው የማህበረሰቡን ማንነት ሃይማኖታዊ ማንነት፣ በአላትና የጋብቻ ሁኔታ ብሎ ቦድኖ ማየቱ የተሻለ ነው፡፡

### 4.1 የቅማንት ማህበረሰብ ሀይማኖታዊ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ

የአንድ ማህበረሰብ ማንነት ከሚገለፅባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ሀይማኖት ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ሀይማኖት በአካባቢው ካሉ ሌሎች ማህበረሰቦች ሀይማኖት የተለየ ከሆነ የማህበረሰቡ ግላዊ አሻራ ነውና የማንነቱ መገለጫ መሆኑ አይቀርም፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ሀይማኖትም (ሀገልቦና/ሀገአበው) በዙሪያው ካሉ ሌሎች ሀይማኖቶች (ከእስልምናና ከኦርቶዶክስ ክርስትና) የተለየ ነው፡፡ ይህን ልዩነትም ማህበረሰቡ በተረኮቹ ያስረዳል፡፡

በተረኮቻቸውም ውስጥ ስለ አምላካቸው፣ ስለሃይማኖቱ ቃላዊነት (ፅሁፍ አልባነት)፣ ስለዕምነቱ መሪዎች (ወንበርና ቄስ)፣ ስለዕምነቱ ጥንታዊነትና ሀገር በቀልነት፣ በእምነቱ ለምግብነት ስለተከለከሉ እንስሳትና መሠል ጉዳዮችን ያስረዳሉ፡፡

በቀደመው ዘመን የቅማንት ማህበረሰብ ሁሉ የሀገልቦና እምነት ተከታይ ነበር (ያሬድ 1999፡318)፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች የማህበረሰቡ አብዛኛው ክፍል የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ሆኗል፡፡ ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የሀገልቦና እምነት ተከታዮች አሉ፡፡ የክርስትና እምነትን ተቀበሉ የተባሉትም ቢሆኑ ከቀደመው እምነታቸው (ከሀገልቦና) ሙሉ በሙሉ የተላቀቁ አይደሉም፡፡ በሀገልቦና ሀይማኖታዊ ክንውኖች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ዝናብ ለማምጣትም ሆነ ከልክ ያለፈ ዝናብን መጠን ለመቀነስ በሚደረግ ፀሎት ላይ በተለያየ መንገድ ይሳተፋሉ፡፡ ለፀሎቱ ማሣረጊያ የሚሆንን መስዋዕት ከማቅረብ አንስቶ በፀሎቱ ላይ እስከመታደም ድረስ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሀይማኖትን አስመልክቶ የተሠበሠቡትን ተረኮች ይዘታቸውን መነሻ በማድረግ የሀገልቦና እምነት መሪዎች፣ የሀገልቦና አምላክ፣ ሀገልቦናና ቃላዊነት፣ የፀሎት ስፍራ፣ የሀገልቦና ጥንታዊነትና ሀገር በቀልነት እና በሀገልቦና እምነት ለመብላት የተከለከሉ ነገሮች በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

### 4.1.1 የሀገልቦና እምነት መሪዎች

የሀገልቦና እምነትን በበላይነት የሚመራው ወንበር ይባላል፡፡ ይህ ወንበር ሀይማኖቱን ብቻ ሣይሆን አስተዳደራዊ ሁኔታውንም (ዳኝነቱን) የሚመራ ነው፡፡ በሀይማኖታዊ ክንውኖች ላይም ግንባር ቀደም ተዋናይ ነው፡፡ ከዚያም የከመዘና ቄስ የሚባል አለ፡፡ ሁለተኛው ቄስ ደግሞ ይተንቲ ይባላል፡፡ ስለዚህ እምነቱን በበላይነት የሚመራው ወንበሩ ሲሆን እነዚህ ሁለት ካህናት ደግሞ ከወንበሩ በበታች ሀይማኖታዊ ስርአቶችንየሚያከናውኑ ናቸው፡፡

እነዚህ የሀይማኖቱ ቁንጮዎች ዝም ተብሎ በዘፈቀደ የሚሾሙ አይደሉም፡፡ ወንበርና የከመዘና ቄስ ለመሆን የክብር የዘር ሀረግ ሊኖር ሲገባ ለወንበርነት ደግሞ ከክብር ዘር በተጨማሪ የህዝብ

ይሁንታና ምርጫ ያስፈልጋል። የይተንቲው ቁስ ይተንቲ ከተባለው ዘር የወጣ ነው። ይህን ጉዳይ በተረኮቻቸው እንደሚከተለው አድርገው ያስረዳሉ።

> *የቅማንት ዘር ክብርና ይተንቲ ከሚባሉ ሁለት ትልልቅ ዝርዮች የሚነሳ ነው። ይህ እንዴት መጣ አትለኝም? ከኩሽ ተወልዶ ወደ አንድ ግንድ የመጣው ክብርዋ ይባላል። ክብርዋ ሦስት ሚስቶችን አገባና ዘጠኝ ልጆችን ወለደ። ከአንዷ ሴት የተወለዱት ገዱህ፣ ሽመኑህና ባቱህ የተባሉት የክብርዋ ልጆች የክብርን የዘር ክብር ይዘው ወረዱ ሁለቱ ሴቶች የወለዷቸው ስድስቱ ሠዎች ደግሞ የይተንቲን ዘር ይዘው ወረዱ። ስለዚህ ክፍፍሉ የተነሳው ከእናት እንጂ ሰውየው አንድ ነው።*
>
> *የክብር ዘር የሹመት ዘር ነው። ወንበሩም መውጣት የሚችለው ከክብር ዘር ነው። ቁሱም ቢሆን የከመዘና ቁስና የይተንቲ ቁስ ተብሎ የተከፈለ ነው። የከመዘናው ቁስ የክብር ዘር ሲሆን ያው የይተንቲው ቁስ የይተንቲ ዘር ነው። የይተንቲ ቁስ አይባርክም። እርድም ሆነ ሌላ የሚባርክ የከመዘና ቁስ ነው። ወንበሩ ከክብር ዘር ይሁን እንጂ የሚመረጠው ግን በህዝብ ነው። ፀባዩ ምኑ ይታይና ህዝቡ እሱ ይምራን ያለ እንደሆነ ብቻ ወንበር ይሆናል (መቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ 2005፣ ጭልጋ/አይከል)።*

ስለዚህ የህገልቦና ወንበርና የከመዘና ቁስ ለመሆን የክብር የዘር ሀረግ ሊኖር ይገባል። የክብርና የይተንቲ የዘር አቆጣጠርን በጋብቻ የዘር ቆጠራቸው ላይ በስፋት የማነሳው ስለሆነ ከዚህ በላይ አልሄድበትም።

ሆኖም ግን አንደኛው የዘር ሀረግ የሹመት ዘር በመሆኑ ሁለተኛው ዘር አይቃወምም እንዴ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ ስለማይቀር ይህን ጥያቄ እዚህ መልሶ መሄድ ተገቢ ነው። የክብር የዘር ሀረግ መጋባት የሚችለው ከይተንቲ ሲሆን የይተንቲውም መጋባት የሚችለው ከክብር ነው። ከዚያ ውጪ የክብር ወንድ የክብሯን ሴት ወይም የይተንቲው ወንድ የይተንቲዋን ሴት አያገባም። የክብር ወንድ ማግባት የሚችለው የይተንቲዋን ሴት ነው። የይተንቲውም ወንድ ቢሆን ማግባት የሚችለው የክብሯን ሴት ነው። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ዝርዮች ተጋብተው የሚወለደው ልጅ የአባቱን የዘር ሀረግ ይከተላል። ስለዚህ የክብር ወንድ የይተንቲዋን ሴት ሲያገባ የሚወለደው ልጅ የዘር ሀረጉ ክብር ይሆናል። የይተንቲው ወንድ የክብሯን ሴት አግብቶም የሚወለደው ልጅ የአባቱን የይተንቲ ዘር ይሆናል። ስለዚህ ወደሹመት ከማይመጣው ዘር የተገኘች ሴት ልጆቿ የአባታቸውን የዘር ሀገር በመከተላቸው ወደ ሹመት መምጣታቸው ነው። በሌላ በኩል የሹመት ዘር ያላት የክብር ሴት የምታገባው የይተንቲን ወንድ በመሆኑና ልጆቹም የሱን የዘር ሀገር ስለሚከተሉ በልጆቻቸው ካልሆነ ወደ ሹመት አይመጡም። እንዲህ

ያለ መካካስካለ ደግሞ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉት ሁለት የዘር ሀረጎች በሹመት የተነሳ እሰጣገባ ውስጥ አይገቡም፡፡

የዘጠና አመት አዛውንት የሆኑት አቶ አበይ መኮንን ደግሞ ወንበርና የከመዘና ቄስ መሆን የሚችል ሰው ከክብር ዘር መሆን እንዳለበት የሚያስረዱት በሌላ ተረክ ነው፡፡

> *አደረኪ (አይደረኪ) በሦስት ሲወልደን አንዲቱ ሰሜንኛ፣ አንዲቱ ጐጃሜ ሌላይቱ ደግሞ ሸልካዋልካይ ከነዚህ ከሦስቱ ነው፡፡ ከነዚህ የሚወለዱት ክብር ናቸው፡፡ ሸልከዋልካይ ተሻምታ ዶሮ አርዳ ያን አብልታ "ይመርቁኝ" አለች፡፡ "ምን ልመርቅሽ?" ቢሏት "ክርክር ወንበርነትን ይመርቁኝ" አለች፡፡ ከዚያ ሰጧት፤ ተቀበለች፡፡ ደግሞ ጐጃሜይቱ አርዳ አብልታ አጠጥታ "ይመርቁኝ" አለች፡፡ "ምን ልመርቅሽ የክርክርን ወንበርነት ሸልካዋልካይ ወስዳለች" አሏት፡፡ "እርስዎ የፈለጉትን ይስጡኝ" ስትል ከዚህ (ከክርክር) ተመርቀው ጭልጋ ወንበርነትን ወሰዱ፡፡ እንደገና ሠሜነኛይቱ ዝም ብላ ቆይታ በኂላ አርዳ፣ ጋግራ አብልታ፣ "ይመርቁኝ" አለች፡፡ "አይ እንግዲህ አንቺ አልፎብሻል ያንቺ ጆኒፈንቀራ ከመዝና ቄስ ሆነው ይያልቱ" ተብላ ቀረች (አበይ መኮንን 2005፡ ክርክር/ማንጌ)፡፡*

በቅማንቶች ትልቁ ወንበር የከርከሩ ነው፡፡ የጭልጋው ወንበር ወንበር የመሆን ማዕረጉን የሚይዘው ከርከር መጥቶ ተመርቆ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ወንበሮች ምንም እንኳን የክብር ዘር ቢሆኑም በመካከላቸው የተወሰነ የዘር ልዩነት (ወደታች በተወረደ ቁጥር የተፈጠረ) እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህን ጉዳይ ያሬድ፣ <u>"የጐንደር ታሪክ"</u> በሚል መፅሀፉ ገጽ 320 ላይ እንዲህ ብሎ ይገልፀዋል፡፡ "የጭልጋው ወንበር በዘራቸው ቅስና ካላቸው የባቱ፣ የገዱና የሺመኑ ዘሮች የሚሾሙ ሲሆን የከርከሩ ደግሞ የሚመረጠው/የሚሾመው ናዚ፣ እንጀዚና የዛና ከሚባሉት ዘሮች ነው፡፡" ስለዚህ ምናልባት ባቱ፣ ገዱና ሺመኑ በተረኩ ጐጃሜይቱ ተብላ ከተገለፀችው የሚወለዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ናዚ፣ እንጀዚና የዛና የተባሉት ደግሞ የሸልከዋልካይ ልጆች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ከክብር ዘር ሦስተኛዎቹ የሠሜነኛይቱ ልጆች ደግሞ የከመዘና ቄስ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

በጭልጋም ሆነ በከርከር (ከርከር ይህን ጥናት ባካሄድኩበት ወቅት ወንበር የለም) ወንበር በመሆን የሚሾሙት የክብር ዘር ያላቸው ሲሆኑ ከክህነትም የመባረክና መሠል ስልጣናት ያሉት ትልቁ ቄስ (ከመዘናው) የክብር ዘር ነው፡፡ ይህን የከመዘና ቄስ ከበታች ሆኖ የሚያግዘው ከይተንቲ ዘር የሚገኘው የይተንቲ ቄስ ነው፡፡

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ቃል ተረክ ማህበረሰቡ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚለይበትን ሁኔታ የሚገልፅልበት ብቻ ሳይሆን በራሱ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን ማሳያና ተከባብሮ የመኖሪያ መንገድም ነው፡፡ ቃል ተረክ በእነዚህ ሁለት የዘር ሀረጐች መካከል መቻቻል እንዲኖርና የስልጣን ሽኩቻ እንዳይነሳ ያግዛል፡፡

4.1.2 የህገ ልቦና አምላክ

የህገልቦና እምነት ተከታዮች አምላክ ምዝገና ይባላል፡፡ ምዝገና በኦርቶዶክስ ክርስትና ሚት እግዚአብሔር እንደሚባለው ያለ ነው፡፡ ቅማንቶች ምዝገና አለምን ሁሉ የፈጠረ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ አለምንና በውስጧ ያሉትንም ነገሮች ሁሉ የፈጠራቸው ሀሙስ እንደሆነም ያምናሉ፡፡ ለዚያም ነው የቅማንቶች ዋና የቅዳሴ ቀናቸው ሀሙስ የሆነው፡፡ ወር በገባ ያለው የመጀመሪያ ሀሙስ ምዝገና ተብሎ የሚቀደሰውም ለዚያ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ሌላው በህገልቦና እምነት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሠጠው አደራ (አንዳንዶቹ አይደረኪ የሚሉት) ነው፡፡ አደራ (አይደረኪ) ለቅማንት ማህበረሰብ (ለህገልቦና እምነት ተከታዩ) የእያንዳንዱ ትዕዛዛትና ህግጋት መሠረት ነው፡፡ አንድን ሀይማኖታዊ ወይም ማህበራዊ ክንዋኔ ሲፈፅሙ "ለምንድን ነው ይህን የምታደርጉት?" ተብለው ሲጠየቁ "አባታችን አደራ/አይደረኪ አዞናል" ነው የሚሉት፡፡

የአይደረኪን ወይም የአደራን አወላለድ፣ አስተዳደግ፣ አኗኗርና አሟሟት በተረካቸው እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *አማሮች እየሱስ ክርስቶስ እንደሚሉት ሁሉ የኛ አባት ደግሞ አይደረኪ ነው፡፡ እነሱ "አምስት ሺ አምስት መቶ አመት ከገዛ በኋላ መልሶ ተፀንሶ ተወለደ" ነው የሚሉ፡፡ እኛ ግን ወለደ ነው የምንል፡፡ እነሱ "ከሠማየ ሠማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ" ይላሉ እኛ ግን ከሠማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ሴት ወልዶ ነው የምንል፡፡ የአይደረኪ አወላለድም እንዲህ ነው፡፡ አንዲት መናገርና መስማት የማትችል ልጅ ነበረች፡፡ እድሜዋም አስራ አምስት ነበር፡፡ አንድ ቀን የዚህች ልጅ ወላጆች ምናምን ለመግዛት ገበያ ይሄዳሉ፡፡ ያኔ ግበሩሀ[12] መጥቶ እንደምን ዋልሽ ቢላት የማትሰማ የነበረችው ሰምታ ምዝገና ይመስገን ብላ ተናገረች፡፡ እንግዲህ እግዜር ያሳይህ በምን ቋንቋውን ለመደች ይባላል?! እናትና አባቷም ሲመጡ እንደምን ዋላችሁ ብላ*

[12]በኦርቶዶክስ ሚት ገብርኤል የሚባለውን አይነት መልአክ ነው፡፡ ይህ መልአክ በቅማንት አብሳሪ መልአክ እንደሆነ ይታሰባል፡፡

አስደነገጠቻቸው፡፡ እነሱም እንዴት ተናገርሽ ቢሏት የሆነውን ነገረቻቸው፡፡ ከዚያ ግበሩህ ተመልሶ መጣና ይዣት ልሄድ ብሎ ቤተሰቦቿን ፈቃድ ጠየቀ፡፡ እነርሱም የሆነውን ሰላዩ ቅዱስ እንደሆነ አውቀዋልና እሺ አሉት፡፡ ከዚያም ይዟት ሲሄድ ወንዝ ላይ ሲደርሱ ትቷት ተሰወረ፡፡ ያኔ ምዝገና በመብረቅ ነጕድጓድ ብልጭ አደረገባትና ፀነሰች፡፡ አማሮች "ጌታችን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተፀነሠ" ይላሉ፡፡ ወዲህ ደግሞ "እሳት ነው" ይላሉ፡፡ እሳት ዘጠኝ ወር እንዴት በማህፀን ይተኛል? የኛ በተፀነሰ በሰባተኛው ቀን ሴቲቱ ልትችለው አልቻለችምና ወደቀች፡፡ ያኔ ጃከረንታ[13]፣ "ፍጡርህ እንዴት ያለ ነው ሴቲቱ እኮ ልትቀደድ ሆነ፤ አልቻለችውም እንዴት ይሁን?" ቢለው፣ "አይ አውርጂው በላት አውርዳው ትረፍ" አለውና በሰባተኛው ቀን ተወለደ፡፡
እንደተወለደም ጥጋቡ አልቻል አለ፡፡ እጅግ ሀይለኛም ስለነበረ ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ ለአርባ ቀናት ታሠረ፡፡ በአርባኛው ቀንም ተፈታ፡፡ ከዚያም በወጣትነቱ በጨዋታም ይሁን በሌላ ሌላ ሰው ሊተካከለው አልቻለም፡፡
አንድ ቀን ጋላ (የገና ጨዋታ) ሲጫወት ሩሯን (ኳሷን) የሚለጋትም የሚቀልባትም እሱ ሆነ፡፡ እንደው ለሌላው ሰው አላቀምስ አለ፡፡ ከዚያ አንዱ ሀይለኛ፣

"አባትክን ማን አውቆ፣

ጕርፍ ያመጣህ ዝቆ፤

አባትክን ንገረኝ፣

ለስድብ ቸገረኝ" ይላል፡፡

ምክንያቱም በመብረቅ ነገር የተፈጠረ ልጅ ነው፤ አባቱ አይታወቅም፡፡ እሱም ዝም ይላል፡፡ በኋላ ግን በጣም እየደጋገመ ሲሰድበው፣ "ምነው ትሠድበኛለህ አትስደበኝ እንጂ" ይላል፡፡ ከዚያ ያ ኀይለኛ፣ "ምን ሠደብኩህ እስኪ ንገረኝ የማን ልጅ ነህ? እኔ የከሊ ልጅ ነኝ፡፡ እሱም የከሊ ልጅ ነው፡፡ እስኪ ንገረኝ ያንተ አባት ማን ነው?" ይለዋል፡፡ በዚህም ይጣላሉ፡፡ ኀይለኛውም፣ "እንግዲህ ልመታህ ነኝ፡፡" ይላል፡፡ ከዚያ አይደረኪ፣ "በል እንግዲህ እንግጠም ያጠቃ ያጥቃ፡፡ አንተም ብትገለኝ እኔም ብገልህ ደም እንዳይነሳ ፀጡ በእኔና ባንተ ብቻ ይቅር" አለው፡፡ ያም ተስማማና ግይድ[14] ገቡ፡፡ ከዚያም አይደረኪ አነሳና በብብራ አሳር ቢመታው ሰውነቱን ቀዶ ወደ ምድር ሀያ ክንድ ገባ፡፡ ከዚያ ኀይለኛው ወዲያው ሞተ፡፡ ከዚያ የሟች ወንድሞች አኮረፉና አይደረኪን አገለሉት፡፡

አንድ ቀን የሟች ወንድም ሚስት ያጭና ሴቷን ሊያመጡ የመንደሩ ጕረምሶች ሁሉ ወደ ሴቲቱ መንደር ሄደው ኖሯል፡፡ አይደረኪም፣ "ዛሬ የዚህ መንደር ሰው ሁሉ ምን ገባ መንደሩ ጭልል ብሏልሳ?" ብሎ ሲጠይቅ፣ "ኧረ አንተን ደመኛ አድርገውህ ነው እንጂ ያ የገደልከው ወንድም ዛሬ ሊዳር ነው የመንደሩ ሰው ሁሉ እሱን አጅቦ ሴቲቱን ሊያመጣ ሄዷል፡፡" ይሉታል፡፡ ከዚያ ያው ይታየዋል ይገሰግስና ሰተት ብሎ አግቢዋ ቤት ይሄዳል፡፡ ሙሽራይቱም ገና ከጕጆ ወደ ሙሽራው ጋር አልወጣችም ነበር፡፡ እዚያ

[13]የምዝገና ታዛዥ የመላእክት አለቃ እንደሆነ የእምነቱ ተከታዮች ያስረዳሉ፡፡
[14]ግይድ ውል፣ ቃል ኪዳን፣ መሃላ እንደማለት ነው፡፡

እንደደረሰም ወዳለችበት ይገባና ጥላውን ጣል ያደርግባታል ከዚያ ትፈቅደዋለች፡፡

ከዚያ አማቺቱ ላይም ጥላውን ጣል ያደርግባታል፡፡ እሷም ለልጁ ትፈቅደዋለች፡፡ ከዚያ ይዟት ሊሄድ ሲል ቤተሰቦቿን እንዲህ ብሎ ሙግት ያስተምራቸዋል፡፡ "በሉ አሁን ሚስታችንን ሲሏችሁ 'እሷ ጐበዝ አይታ ሄዳለች፡፡ ያባት እዳ ለልጅ እንጂ የልጅ እዳ ላባትና እናት አይሆንም፤ እኛ አንጠየቅም፡፡ ሴት ወለድን እሷም ቆንጆችና ጐበዝ ወደዳት በዚህም አግድማ ሄደች፡፡ እኛን ምን አድርጉ ትሉናላችሁ?!' በሉ" ብሎ "ይገልድጉ ጉሽ" ይላል በቅማንትኛ "አንተ ግድግዳ ልቀቅ" ሲል የጐጆው ግድግዳ ይለቅና በዚያ ሾልኮ ይዟት ይሄዳል፡፡ ከዚያ ተነስተው፣ "ሚስታችንን ስጡን" ቢሉ፣ "ይህች ሴት የለችም፡፡" ይላሉ፡፡ "ከምን ሄደች ከምን ሄደች?" ይባባላሉ፡፡ ከዚያ ቤተሰቦቿም እንዳስተማራቸው ይመልሳሉ፡፡ ምን ያድርጉ? እነዚያም "ሰርግ ብዬ" እያሉ ከቆዩበት ቆይተው ቢመጡ አንዱ አሽሟጣጭ፣ "አይጐበዝ! እሱ ብቻውን ተወልዶ በቀረ! እሱ ትናንት ይዟት የገባውን ሰርግ ብዬ እያልክ ስትናፍፍ" ይላል፡፡ ይህን ሲሰሙ አይደረኪ ጋር ሰተት ብለው ይመጡና፣ "ምን ብለህ ሚስታችንን ይዘሀት መጣህ?" ቢሉት፣ "እኔ ሚስት ታጩ አታጩ አላውቅም የናንተ ሚስት ከሆነችማ ውሰዷት" ይላል፡፡ ቅማንቶች ግንባራቸውን ይቀደዳሉ የሚባልበት ምክንያት ያኔ "ኪዱስ" ብሎ ግንባሯን ቀዶ ስለባረካት ነው ይባላል፡፡ ከዚያ ገብተው ሲያይዋት ባርኳታል፤ "አይይ... ባርኳት የለ! እንግዲህ ምን እናደርጋታለን?!" ይሉና ይመለሳሉ፡፡ ከዚያ፣ "ይሄ ሰውዬ ከዚህ ቀደም ወንድማችንን ገደለ አሁን ደግሞ ሚስታችንን ቀማ ምን ይሻለናል?" ብለው ተመካከሩና፣ "ዘመቻ ይሁን ብለን እናሳውጅና እዚያ ዘመቻ ላይ እሱም ስለሚመጣ እንግደለው፡፡" ብለው ተማከሩና ለዳኛውም ነግረው ዘመቻ ታዘዘ፡፡ በዘመቻው ላይም ማንም ሰው እንዳይቀር ታወጀ፡፡ እሱ የዘመቻው ለት እቤቱ ተቀመጠ፡፡ ዘመቻው ለምን እንደሆነ አውቋልና፡፡ ከዚያ እናቱ፣ "ዘመቻ ተብሏል ውጣ እንጂ" ብላዋለች፤ "እናቱ ትዝመት አባቱ"[15] ይላል፡፡ "ተው እንጂ ልጄ ወይ ወንድም የለህ፣ እህት የለህ፤ ወገን የለህ፣ ጓደኛ የለህ፤ ብቻህን የተፈጠርክ ሰው ተው እንጂ" አለችው፡፡ "እኔ ሦስት ጊዜ ኪዱስ ብል፣ ሰባት ጊዜ ረግጬ የምወጣው ርካብ ያለው ፈረስ ተደጃፌ መጥቶ ይቆማል፤ ከጭንጫው ላይ ውሃ የማፈልቅ፣ ከባህሩ ላይ እሳት የማነድ ወንድ እኮ ነኝ፡፡ ሦስት ጊዜ ኪዱስ ብል ሦስት ጀንፎ ያለው ጦር ከጄ መጥቶ ይገባል፡፡ እና ከእኔ ጋር ነው እነሱ እኩል የሚሆኑት?!" ብሎ ተበሳጭቶ ሲነሳ እናቱ፣ "እረ ተው ልጄ ተው እባክህ" ትለዋለች፡፡ ንጋት ይነሳና፣ "ኪዱስ... ኪዱስ... ኪዱስ..." ብሎ በሚናገርበት ጊዜ ሰባት ርካብ ረግጦ የሚወጣው ፈረስ ከደጃፉ መጥቶ ቀጥ! ሦስት ጀንፎ ያለው ጦር ከጁ መጥቶ ጥልቅ! ያኔ ተበሳጭቶ ሲነሳ የከረንታ ፈጣሪውን፣ "ልጅህን አስቁመው እንጂ ሊጨርሳቸው እኮ ነው፡፡ ተነሳኮ ቆረጠ ከፈረሱ ላይ እየወጣ ነው ታዲያ ማን ይተርፈዋል ምድርን እኮ ወና ሊያደርጋት ነው፡፡" ሲለው ምዝገናም፣ "ሂድና ና ብለህ ጥቀሰው፡፡" ይለዋል፡፡ ከዚያም ይጠራዋል፡፡

[15]የምን ዘመቻ ነው? እኔ አልዘምትም፤ ዘመቻው አይመለከተኝም እንደማለት ነው፡፡

*ሲጠራውም አራቱን ርካብ ጨርሶ አምስተኛውን ረግጦ ነበር፡፡ ከዚያ ወደ ሰማይ ያርጋሉ፡፡ ምዝገና ጋር ሲደርስም፣ "እንዴት ነው?" ብሎ ጠየቀው፡፡ "አይ አባቴ እኔ ለመኖር አልተመቸኝም እየተጣላሁ፣ እየተደባደብኩ፣ እየተዳማሁ ነው ያለሁት፡፡" አለው፡፡ "አይ አንተም አታጉልብት በጉልበት እኮ አይሆንም ስራ አይሠራም በጉልበት፡፡ የምትፈልግ ከሆነ ወይ ግዛትህን ለብቻ በባህር ከልዬ ልስጥህ" አለው፡፡ "መስዬ ተመሳስዬ ልኑር፡፡" አለ፡፡ "አይ ካልክማ ከዚህ በኋላ እንዲህ ብለህ በኋይልህ ልትጠቀም እንዳትሞክር ጦርም በጅህ እንዳይገባ፡፡ በተበደልክ ጊዜ ፊትህን ወደ ፀሃይ መውጫ አድርገህ 'ኪዱስ...' ብለህ ንገረኝ፡፡ እኔ ያኔ ጨቅላ እርር ብሎ ሲያለቅስ እናቱ 'ልጄ ወደቀን' ብላ እንደምትደነግጠው ደንግጬ እሠማሀለሁ፣ እረኛ ከብቶቹን እየጠበቀ ቢጣራ፣ አባቱ 'ከብት ወደቀ፣ ከብት ተዋጋ' ብሎ ደንግጦ እንደሚሠማው እሠማሀለሁ፣ ቃሌ ይሁን፡፡ አንተ ግን መደብደብ መቸንከር ነው እንጂ ያለብህ በሃይልህ አይሁን አግጄሀለሁ" ብሎ መልሶ ወደ ምድር ሰደደው፡፡*

*ከዚያ ወደ ምድር መጥቶ እየተሠደበ፣ እየተደበደበ፣ እየታሠረ፣ እየተፈታ ኖረ፡፡ ቦር የሚባል አለ በዚህ በደብረሳሙኤል ወዲያ ሆኖ ኳሪቾ ቢል ቋራ አሉት፡፡ ኳሪቾ ማለት በቅማንተኒ ፀሃይ ሃገር ማለት ነው፡፡ እዚያ ገብስ ዘርተው ነበርና ልጁን፣ "ሂድና ምርቱን ሰብስብ፡፡" ቢለው፣ "ይህን ሁሉ በረሃ እንዴት ብዬ ነው?" ብሎ መለሠለት፡፡ አይደረኪ ደግሞ ቃል ተገብቶለት ሲመጣ የተነገረው ምልክት ነበር፣ "የወለድከው ልጅህ መልስ በሠጠህ ጊዜ አንተ ወደኔ ትመጣለህ፡፡" ብሎት ነበርና ሊጠራ እንደሆነ አወቀ፡፡ ከዚያም ደብድበው ገደሉትና ወደ መንደራቸው ተመለሱ፡፡ መቼም ሴት ነገረኛ ነው፣ "ደብድበን ገደልነው" ሲሏቸው፣ "አይ እንደሱ ያለውን ጀግናማ አትችሉትም ከሆነስ ችብችቦውን (ክንድና ክንዱን) ቆርጣችሁ ባመጣችሁት ነበር" ሲሏቸው እንዳሏቸው ለማድረግ ቢሄዱ አይደረኪ የለም አርጓል፡፡*

በዚህ ተረክ ውስጥ አደራ (አይደረኪ) ይፈፅማቸው የነበራቸው ነገሮች በአጠቃላይ እስከአሁንም ድረስ የህገልቦና እምነት ተከታዮች (በተለይም የሀይማኖቱ መሪዎች) የሚፈፅሟቸው ናቸው። ለምሳሌ ወንበሮችና ቄሶች ምንም አይነት የጦር መሣሪያን አይዙም። ለዚህም ምክንያታቸው አይደረኪ (አደራ) ወደምዝገና እንደሄደ ምዝገና "አንድም ነገርን በጉልበትህ ለማድረግ እንዳትሞክር፣ ጦርም በእጅህ እንዳይገባ እኔን ብቻ 'ኪዱስ' ብለህ ጥራኝ" ብሎታል የሚል ነው። የህገልቦና ካህናትና ወንበሮች ምንም አይነት ነገር ቢደርስባቸው ኪዱስ ብለው ከመለመን ውጪ በጉልበታቸው ለማድረግ የሚሞክሩት አንዳችም ነገር የለም። ይህን ጉዳይ በሚከተለውም ተረክ አጠናክረው ይገልፃሉ።

*ላይ አርማጮሆ ቦለቃ የሚባል ሀገር ቄስ ሸዋይ የሚባሉ የቅማንት ቄስ ነበሩ፡፡ ፈጣሪን በጣም የሚያምኑና የሚለምኑ ነበሩ፡፡ አውሬ ቢመጣ ምን ቢመጣ ከተቀመጡበት ወይ ከቆሙበት ንቅንቅ አይሉም፡፡ "ፈጣሪ አዞ ከሆነ ያሻውን*

*ያድርግ በኔ መሸሽ አልድንም::" የሚሉ ነበሩ:: አንድ ቀን አንድ ነብር የግራጫ እሾህ በጥፊ ሲግታ እሾሁ በሡንጣው (በመዳፉ) ይገባበትና ቢል ቢል አልወጣልህ ይለዋል:: በጥርሱም ቢግጥ እምቢ ይለዋል:: ከዚያ በጣም አብጦበት መላወስም ተሳነው:: ከዚያም እንደተጨነቀ ቄስ ሸዋይ ካሉበት መጣ:: እሳቸውም ከአፋፍ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ነበር:: መቼም የሰው ግንባር ተፈሪ ነው ፊቱን ዞሮ ቁጭ አለ:: ከዚያም አንዴ ሲዞር ወደሳቸው ይመጣ ዘንድ ጠቀሱት:: (ተራኪው እጃቸውን ና በሚል ምልክት ያወራጫሉ::) ከዚያም ነብሩ መጣና እጁን ጭናቸው ላይ አስቀመጠ:: እጁን ቢያዩት ግምኛ ተጐድቷል:: በጥርሱም በምኑም አገኝ አገኝ ሲል ጫጭሮታል:: ከዚያ ባንድ ገፅ መቆንጠጫ ባንድ ገፅ ደግሞ ወረንጦ የምትባል እቃ አለች እሷን ሚስታቸውን አምጭልኝ ብለው ሰርስረው በመቆንጠጫዋ ስበው አውጥተው ያበጠውን አፍረጥርጠው ቅቤ ቀብተው ሂድ ሲሉት ሦስት ጊዜ ሠግዶ "ነውር" አለ ይባላል:: በሂደ በሠባተኛ ቀኑም አንድ አውራ ድኩላ መትቶ ይዞ መጣ አሉ:: ከዚያን በኋላም በተደጋጋሚ እያመጣ ሦስት አመት ገበረ ይባላል (ቄስ አማረ፣ 2004 ጭልጋ)::*

እንግዲህ የህገልቦና እምነት መሪዎች ምንም መጣ ምንም በጉልበታቸው ለመከላከል አይሞክሩም። ነብር ሰውን ከሚያስፈሩት አውሬዎች መካከል አንዱ ነው። ነገር ግን ቄስ ሸዋይ ሊሸሹት ወይም ሊከላከሉት አለበለዚያም ሊያጠቁት ሲሞክሩ አይታዩም። ይልቅስ ከስቃዩ ሲገላግሉት እናስተውላለን። ይህ ደግሞ የመነጨው አይደረኪ በምድር እየተጣላ በተቸገረበት ጊዜ ምዝገና፣ "ከዚህ በኋላ በሀይልህ ምንም ነገር ልታደርግ አታስብ እኔን ጥራኝ" ስላለው ነው። ለዚያም ነው ቄስ ሸዋይ፣ "ፈጣሪ አዞ ከሆነ ያሻውን ያድርግ በኔ መሸሽ አልድንም" የሚሉት። አደራ (አይደረኪ) ወደምዝገና ሄዶ፣ "በጉልበትህ እንዳታድር" እስከተባለበት ጊዜ ድረስ ለሃይለኛነቱ ወደር አልነበረውም። በእርግጥ ያ የጉልበት ሀይል ከዚያ በኋላም ቢሆን በሌላ ሀይል ይተካል እንጂ አይጠፋም። እንደህገልቦና እምነት ተከታዮች በእነሱ ላይ ሲፈፀም የሚችል አንድም ጉዳት የለም። ይህ እንዲሆን ፈጣሪያቸው ለአይደረኪ (ለአደራ) ቃል ገብቶለታል። "ምንም ነገር ቢደርስብህ እኔን ጥራኝ እኔም ፈጥኜ እደርስልሀለሁ" ብሎታል። ይህ ጉዳይ ተፈፃሚ ሲሆን በሌሎች ተረኮቻቸውም ላይ ይታያል።

*አንዴ አንድ የጐንደር ንጉስ የቅማንትን ህዝብ ለማጥፋት ያሴራል:: በዚህም እንደነገ ዘመቻው እንዲሆን ይወሰናል:: ወታደሮቹ በቅማንት ህዝብ ላይ ከመዝመታቸው በፊት ይበረቱ ዘንድ የሚመገቡት ምግብና የሚጠጡት ጠላና ጠጅ ሲሰናዳላቸው ታደረ:: ከዚያም ጠዋት የተዘጋጀውን በልተውና ጠጥተው ለመሄድ ሞሰቡን እንክፈትህ ቢሉት አልከፈትም አለ:: ወጡም፣ ጠላውም፣ ጠጁም... ሁሉም አልከፈትም አለ:: በኋላ፣ "አማሮች ይፀልዩ" ተባለና መጡ:: ሲፀልዩ ቢውሉ የተከደነው ሁሉ ሊከፈት ቀርቶ ንቅንቅም አላለ:: "እስቲ እስላሞች ይምጡ" ተባለ:: እነሱም በምነታቸው ቢፀልዩ ሊከፈት አልቻለም:: "እስኪ እነዚህ ቅማንቶች የተባሉት ይምጡና ይሞክሩት" ተባለ:: እንደነሱ*

*ሲፀልዩ አልዋሉም፡፡ ያው እንደ አባታችን ኪዱስ .. ኪዱስ.. ኪዱስ.. ብቻ አሉ፡፡ ምርጉ ሁሉ ተከፈተ፡፡ ነገር ግን መጠጡ ደም ምግቡ ትል ሆኖ ተገኘ፡፡ ከዚያም፣ "ምን የመከራችሁት ነገር ነበር? ይህንንስ ምግብ ለምን አይነት ክፋት አሰባችሁት ነበር? እውነቱን ንገሩን ጌታ የሚወደው እውነትን ነው፡፡" አሉ፡፡ ከዚያም ለምን እንዳዘጋጁት ይነግሯቸዋል፡፡ ቅማንቶችም፣ "እኛ ምን በደልናችሁ ምንስ አጠፉን የፈጣሪ ተገዢ ነን፤ የፈጣሪ ለማኝ ነን፤ የፈጣሪ ፀሏች ነን ምን አደረግን እኛን የምታጠፉን?" ሲሉ ያ መንግስት ተፀፅቶ ተዋቸው አሉ፡፡ (ቄስ አማረ 2004 ቃል.ጋ)*

በዚህ ተረክ እንደተገለፀው የህገልቦና እምነት ተከታዮች መሣሪያ ታጥቀው ከጠላቶቻቸው ባይዋጉም ፈጣሪያቸው ከማንኛውም የጠላት ውጊያ እንደሚጠብቃቸው ያምናሉ፡፡ በተረካቸው እንደገለፁት የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ለረጅም ጊዜ ፀልየው ያልተሳካላቸውን ጉዳይ እነሱ ሦስት ጊዜ "ኪዱስ" ብቻ ብለው ይፈፅሙታል፡፡ በዚህም የእነሱ እምነት ከሌሎች እምነቶች የጠነከረ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

የተዘጋጀው መብልና መጠጥ ደምና ትል ሆኖ መገኘቱም ማንም እኛን ሊያጠቃን ቢያስብ በሠማይ ያለው አምላካችን ነገሮችን ሁሉ የሚደበላልቅበትና ሀሳቡን የማያሳካለት በመሆኑ ባይሞክረው ይሻላል ሲሉ ነው፡፡ መብል መጠጡ የተዘጋጀው ለወታደሩ ብርታት ይሆን ዘንድ ነው፡፡ ይህ ብርታት ግን ደምና ትል በመሆኑ ይበረታል ተብሎ የታሰበው ወታደር የማይበላውና የማይጠጣው ሆኗል፡፡ በዚህም የቅማንትን ማህበረሰብ ሊያስጠቃው የሚችለውን ሀይል አያገኝም፡፡ ስለዚህ ማንም በእኛ ላይ ቢነሳ እኛን ለማጥቃት የሚያስችል ቅስም ሊኖረው አይችልም እንደሚሉ ከተረኮቻቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ሌላው የክብር ዘር የይተንቲዋን ዘር ሲያገባት በግንባሯ ላይ ሠርዷ ጋር በአይኖቿ ሽፋሽፍት መካከል ትነሽ ይሠነጥባታል፡፡ አይደረኪ (አደራ) ከሌላ ነጥሎ ያገባትን ሴት እቤቱ እንዳመጣት የእሱ ለመሆኗ ማረጋገጫ ያደረገው ግንባሯን ሰንጥቦ ነው፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ ባላንጣዎቹ በመጡ ጊዜ ሊወስዷት ይችሉ ነበር፡፡ "የእናንተ ሚስት መሆኗን በምን አወቅሁ? እንግዲያውስ ውሰዷት" ባላቸው ጊዜ ሊወስዷት ሲገቡ ግንባሯን ተሠንጥቦ አዩዋት፡፡ ትተዋት የሄዱበት ምክንያትም ይሄው ነበር፤ "ባርኳት የሱ አድርጓት የለ" በሚል፡፡ ስለዚህ የይተንቲን ሴት የሚያገባው የክብር ዘር ሴቲቱን ግንባሯ ላይ መሠንጠቡ ከዚህ በኋላ የኔ ሚስት ናት ማለቱ ነው፡፡

በአጠቃላይ በህገልቦና እምነት ውስጥ ፈጣሪ ነው ተብሎ የሚታመነው ምዝገና ሲሆን እሱ ከአስራ አምስት አመት ድንግል ሴት በመብረቅ እንደወለደው የሚያምኑት አደራ (አይደረኪ) ደግሞ የሀይማኖታዊ ክንውናቸው ሁሉ አስተማሪ ነው። በዚህ እምነት ውስጥ የፈጣሪ ታዛዥና የመላዕክት አለቃ ጃከረንታ ሲባል ግበሩህ የሚባል አብሳሪ መልአክ እንዳለም ያምናሉ።

### 4.1.3 ህገልቦናና ቃላዊነት

ህገልቦና በሚባለው የቅማንቶች እምነት እያንዳንዱ ስርአት (ቅዳሴው፣ ፀሎቱ፣ ምስጋናው...) የሚከናወነው በቃል ነው። በዚህ እምነት ውስጥ ፅሁፍ የሚባል ነገር ዋጋ የሌለው መናኛ ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ ህገልቦናን ፅሁፍ ካላቸው ከክርስትናና ከእስልምና እምነት የተለየ ያደርገዋል። የእምነቱ ተከታዮች የሀይማኖታቸውን ፅሁፍ አልባነት ምስጢር የሚያስረዱበት የቃል ተረክ አላቸው።

> *ድሮ ነው አሉ አማራ[16]፣ እስላምና ቅማንት የሚተዳደሩበትን ህግ ለመቀበል ወደምዝገና ሄዱ። እሱም ለአማራው፣ "በል ይሄ ህግህ ደንብህ ይሁን በዚህ እደር" ብሎ መፅሀፍ ቅዱስ ሰጠው። ለእስላሙም፣ "በዚህ እደር" ብሎ ቁራን ሠጠው። ቅማንቱ፣ "ለኔስ?" ቢለው፣ "አንተ አስተዋይና የማይዘነጋ ልቦና ስላለህ ህግን በልብህ አኖራለሁ በሱ ህግም ትተዳደራለህ" አለው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቅማንት ማህበረሰብ በተፃፈ ነገር ሳይሆን በልቡ ባለው ህግ ይተዳደር ጀመር (አዲሱ ታረቀኝ 2004 ፣ ጐንደር)።*

ፅሁፍ የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ሀይማኖት፣ ታሪክ፣ እውቀትና የመሳሰሉት ሳይዘነጉ ከዘመን ዘመንና ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገሩበት አይነተኛ ድልድይ ነው። በዚህም ፅሁፍ ዝንጋኤን የሚከላከል ጋሻ ነው ሊባል ይችላል። ነገር ግን የህገልቦና እምነት ተከታይ የሆኑት የቅማንት ማህበረሰብ አባላት "እኛ ታሪካችንን፣ ሀይማኖታችንንና ማንኛውንም እውቀታችንን የማንዘነጋ በመሆናችን በሀይማኖታዊ ስርአቶቻችን ውስጥ ምንም አይነት ፅሁፍን መገልገል አይጠበቅብንም" ይላሉ።

በአንዳንድ ተረኮቻቸው እንደሚገልፁት ደግሞ ፅሁፍ አመጣጡ በክህደት ነው።

> *አማሮችም ሁሉም ድሮ እምነታችን አንድ ነበር። ሁላችንም የነአብረሃምና የነይስሀቅን አምላክ እያመለክን እንኖር ነበር። ኋላ ግን ሙሴ "ብቻዬን ሆኜ ፈጣሪ ፅላት ላይ ፅፎ ሠጠኝ" አለና ፅሁፈትን ይዞ መጣ። እንግዲህ ሙሴ የማናወቀውን አዲስ ነገር ይዞብን መጣ። መጀመሪያም ቢሆን ክህደትና ውሸት*

---

[16]አማራ የሚለው የማህበረሰብ መጠሪያ ብቻ ሳይሆን የኦርቶዶክስ ክርስትና የሚለውንም የሚወክል ነው።

*ነበረበትና የኛ አባቶች አላመኑትም፡፡ አንዴ አባታችን አደራ ላይ በሀሰት መስክሮበታል፡፡ እንደውም እኮ ኋላ አደራ ጥፋ ብሎ ብን አድርጐ አጥፍቶት መቃብሩ እንኳን አልተገኘም (አየልኝ ተሠማ፣ 2005 ጭልጋ/አርሁና ጊዮርጊስ)፡፡*

ሙሴን እውነተኛ መሪ አይደለም የሚሉት ቅማንቶች ሙሴ ከእግዚአብሔር ተፅፎ ተሠጠኝ የሚለውን የፅላት ላይ ፅሁፍ አጥብቀው ይቃወማሉ፡፡ እንደውም ሙሴ በአደራ ላይ በሀሠት የመሠከረ ሀሰተኛ ነው ይሉታል፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው ምናልባትም ውሸቱን የራሱን ፈጠራ ፅፎ አምጥቷል ብለው ያምናሉ፡፡ የህገልቦና እምነት ተከታዩ ሙሴን ይጠሉታል፡፡ አንድን ውሸታም ሲሣደቡ እንኳን "አንተ ሙሴ" ይላሉ፡፡ "ሙሴ መቃብር" ሲሉም ድራሽህ ይጥፋ እንደማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሙሴ በፅሁፍ ውሸትን አምጥቷል ብለው ስለሚያምኑ፣ "ፈጣሪያችን በልባችን አኑሯል" የሚሉትን በቃል ያለ እምነታቸውን ብቻ ይከተላሉ፡፡

4.1.4 የፀሎት ስፍራ

ቅማንቶች የፀሎት ስነስርአትን የሚፈፅሙበት ስፍራ ድግና ወይም ዱቢት ይባላል፡፡ መስዋዕት የሚያቀርቡት ደግሞ በተራራ ላይ ነው፡፡ በተራራ ላይ መሠዋትን ከአብርሃም እንደወሰዱት በተረኮቻቸው ይገልፃሉ፡፡

ቅማንቶች ፀሎትና ቅዳሴ የሚፈፅሙባቸው ድግናዎች በደን የተሸፈኑ ናቸው፡፡ እንደህገልቦና እምነት ተከታዮች አገላለፅ እነዚህ ስፍራዎች ደን ስላለባቸው ብቻ ድግና ወይም ዱቢት አይሆኑም፡፡ እነዚህ ስፍራዎች ቅዱሳን አባቶቻችን ያረፉባቸው የመቃብር ስፍራዎች ናቸው ይላሉ፡፡

አንዳንዶቹ መረጃ ሠጪዎች እንደሚገልፁትም አንዳንድ ድግናዎቻቸውን የክርስትና እምነት ተከታዮች በመንጠቅ ቤተክርስቲያን ሠርተውባቸዋል፡፡ አሁንም ድረስ ተከብረው የሚኖሩ ድግናዎች እንዳሉ ግን አስተውያለሁ፡፡

አንዳንድ ድግናዎቻቸውን ደግሞ በምዝገና ፈቃድ ለታላላቅ መሪዎቻቸው መታሰቢያ እንዲሆን አማራው ባለማወቅ ትልልቅ መታሠቢያ በመስራት እንደሚያኖራቸው በተረኮቻቸው ይገልፃሉ፡፡ ይህን ጉዳይ መቶ አለቃ ጥጋብና አቶ ነጋ ጌጤ ሲያስረዱ የኖህን የመቃብር ስፍራ በመጥቀስ ነው፡፡ አቶ ነጋ የፋሲል ግንብ የተሰራው በኖህ የመቃብር ስፍራ ላይ የነበረ ድግና ተመንጥሮ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ መቶ አለቃ ጥጋቡም የአቶ ነጋን ተረክ በመጋራት ያ የሆነበትን ምክንያት

አክለው ሲያስረዱ ምዝገና ለኖህ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የፋሲል ግንብ እንዲገነባ እንዳደረገ በመግለፅ ነው፡፡ ግንበኞቹም ቢሆኑ የቅማንት ማህበረሰብ ናቸው ይላሉ፡፡

የህገልቦና እምነት ተከታዮች የፀሎት፣ የቅዳሴና የመሠዋዕት ተግባራትን የሚፈፅሙባቸው ስፍራዎች የማይታረሱና ከብት የማይገባባቸው ናቸው፡፡ ሰውም ቢሆን ስርአተ ቅዳሴ ሲፈፀም ወይም ሲፀለይ አለበለዚያም መሠዋዕት ለማቅረብ ካልሆነ አይገባባቸውም፡፡ እነዚህ ስፍራዎች ንፁህና የተከበሩ እንደሆኑ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡







ከድግናዎቻቸው መካከል ጥቂቱ

### 4.1.5 የህገልቦና ጥንታዊነትና ሀገር በቀልነት

የህገልቦና እምነትን የሚከተሉት ቅማንቶች በቃል ተረኮቻቸው እንደሚያስረዱት የህገልቦና እምነት ጥንታዊና ሀገር በቀል ነው። ከኦርቶዶክስ ክርስትና ጋር መለያየት የጀመርነው ሙሴ ታቦተ ህጉን ተቀበልኩ እንዳለ ነው የሚሉት ቅማንቶች እነሱ የአስቀድሞውን እምነት ይዘው እንደቀጠሉና ሙሴ ግን አዲስ ነገር አገኘሁ በሚል አዲስ እምነትን (ሀይማኖትን) እንዳመጣ በተረኮቻቸው ይገልፃሉ።

ምንም እንኳን የቅማንት ማህበረሰብ የቀደመ እምነት ህገልቦና ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን የእምነቱ ተከታዮች እየተመናመኑ እንደሆነ Gamst (1967) ያስረዳሉ። በዚሁ መፅሀፍ እንደተጠቀሰውም እምነቱ ጥንታዊ እንደሆነና የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ከህገልቦና አንፃር በቅርብ ነው። ቅማንቶች "ቀዳሚው እምነት የናንተ ሆኖ ሳለ በቅርብ የመጡት ሃይማኖቶች ከእለት ወደ እለት ሲስፋፉ የእናንተ እምነት መዳከም ምክንያቱ ምንድን ነው?" ተብለው ሲጠየቁ፣ "ብዙ ዘመን ከኖረ ጌሾና ወይራ ትናንት የተተከለ ባህር ዛፍ በቁመት መብለጡ አይቀርም። ግን ጌሾም ጌሾ፣ ወይራም ወይራ፣ ባህር ዛፍም ባህር ዛፍ ነው" ይላሉ (ቄስ አማረ ሙሉነህ 2004፣ ጭልጋ)።

ጌሾና ወይራ በጥንካሬያቸው የሚታወቁና በአካባቢው የሚበቅሉ ሀገር በቀል ዛፎች ናቸው። እነዚህን የዛፍ አይነቶች ቅማንቶች የሀይማኖታቸው ወካይ ሲያደርጓቸው ሀይማኖታቸውን ጥንታዊ፣ ጠንካራና ሀገር በቀል ነው ሲሉ ነው። ባህር ዛፍን ከእነዚህ ሁለት የዛፍ አይነቶች አንፃር የተመለከትነው እንደሆነ እንደነሱ ጠንካራ አይደለም፤ አገር በቀልም ሳይሆን በምኒሊክ ዘመን ከውጪ የመጣ ነው። ስለዚህ ሌሎችን ሀይማኖቶች በዚህ የዛፍ አይነት ሲወክሉ፣ የእኛን ሀይማኖት ያህል ጥንካሬ የሌላቸውና አገር በቀል ያልሆኑ ናቸው ማለታቸው ነው። ለዚያም ነው በቅርብ የተተከለ ማለታቸው። በቅርብ መተከል በቅርብ ወደ ሀገር ውስጥ መምጣትንና ጥንታዊ መሠረት የሌለው መሆኑን ለመጠቆም የተገለገሉበት ነው።

ስለዚህ ከተረኮቻቸው መገንዘብ እንደሚቻለው የህገልቦና እምነት ጥንታዊና ሀገር በቀል ነው።

### 4.1.6 በህገልቦና እምነት ለመብላት የተከለከሉ ነገሮች

በህገ ልቦና እምነት ሽኮናቸው ድፍን የሆኑ እንስሳት አይበሉም፡፡ ይህ ግን በክርስትና እምነት ተከታዩም ዘንድ የሚከለከል በመሆኑ የቅማንቱ የብቻ መገለጫ አይደለም፡፡ ከዚህ ውጪ ግን የክርስትና እምነት ተከታዩ እየተመገባቸው የህገልቦና እምነት ተከታዮ የማይመገባቸው ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም አሣና ሰስ ሲሆኑ የማይመገቡባቸውን ምክንያቶችም በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡

> *አንድ ጊዜ አንዲት ሴት፣ ልጇ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ይምትባታል፡፡ እሬሳውም ጠፍቶ ይቀራል፡፡ ታዲያ ሴትየይቱ በሀዘን ተቆራምዳ ስትኖር አንድ ቀን ሰዎች አሳ ሲያጠምዱ አንድ በጣም ትልቅ አሳ ይይዛሉ፡፡የአሣሳውን ሬብ[17] ለማውጣት ሆዱን ሲሰነጥቁትም የዚያ የሟቹ ቀለበት ይገኛል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለህገልቦና እምነት ተከታይ አሣ እርም (የተከለከ) ሆነ (ወንበር ሙሉነህ መርሻ፣ 2004 ጭልጋ)፡፡*

እስላም ያረደውን ክርስቲያን፣ ክርስቲያን ያረደውን እስላም አይመገብም፡፡ እስላምና ክርስቲያን ማንም ከባህር አወጣው ማንም ሳይመርጡ የሚመገቡት አሳን ነው፡፡ እስላም ከባህር ያወጣውን አሳ ክርስቲ ያን ይመገበ ዋል፤ ክርስቲ ያን ከባህ ር ያወጣውንም አሣ እስላም ይመገበ ዋል፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ግን ከናካቴው አሳን አለመመገቡ ከነዚህ ከሁለቱ እምነቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ለህገ ልቦና እምነት ተከታዩ ቅማንት አሣ ወገኑን በልቶ የገደለ ባላንጣው ነው፡፡

በህገልቦና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሰስ ስጋ የማይበላበትንም ምክንያት ወንበር ሙሉነህና ቄስ አማረ ሲያስረዱ፡-

> *አይደርኪና ሚስታቸው አንዴ ሲጓዙ ይውሉና ሲመሽ አንድ ዋሻ ውስጥ ለማደር ይገባሉ፡፡ ለካስ ዋሻው ውስጥ ወልዳ ተኝታ የነበረች ሰስ ኖራለች፡፡ እነሱን ስታይ ልጇን ትታ ደንብራ ወጥታ ሣትመለስ ትቀራለች፡፡ በማግስቱም ብትታይ ከየት ተገኝታ?! አንዴ ፈርታ ሸምጣ! ከዚያ ግልገሏን ሰስ እናታችን ጡታቸውን እያጠቡ ለቅጠል እስክትበቃ አሳደጓት በዚህ የተነሳ፣ "የኔ ፍጥረት የሆናችሁ ይህች ሰስ ጡቴን አጥብቼ ያሣደኳት ልጀ ናትና እንዳትነኳት" ብለው አዘዙ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰስ አንበላም*

በማለት ነው፡፡

ስለዚህ ለዚህ ማህበረሰብ ሰስ የእህት ያህል ትቆጠራለች፡፡ የእናታቸውን (የአይደረኪን ሚስት) ጡት ጠብታ ባደገች አንዲት ሰስ የተነሳ መላው ሰስ እህታቸውና ወንዳማቸው ሆነ፡፡ ይህ

---

[17]የውስጥ እቃ ለምሳሌ ጨጓራ፣ አንጀት፣ ጉበት… ተጠቃለው የሚጠሩበት መጠሪያ ነው፡፡

ማህበረሰብ በቀደመው ዘመን በከርከር ዱር ውስጥ ፍሬ እየለቀመና እንስሳት እያደነ የኖረ ቢሆንም የሰስ ስጋን ግን በተጠቀሰው ምክንያት አይመገብም። አገራባቾቹ የክርስትና እምነት ተከታዮች ግን ሽኮናቸው ክፍት የሆኑ እንስሳትን ስለሚመገቡና ሰስም ሽኮናዋ ክፍት ስለሆነ ይመገቧታል። በዚህም የህገልቦና እምነት ከክርስትናው እምነት ይለያል።

የህገልቦና እምነት ካህናት ለመብላት የተፈቀዱትን እንስሳትም ቢሆን የከመዘናው ቄስ ካልባረከ (ካላረደ) በቀር ሌላ ሰው የባረከውን አይመገቡም። ህዝቡም ቢሆን የሌላ እምነት ተከታዮች ያረዱትን አይበላም። አርብና እሮብ የታረደም አይመገቡም ነገር ግን በሌላ ዕለት የታረደውን ስጋ አርብና እሮብም ቢሆን ይመገቡታል።

የቅማንት ማህበረሰብ ሙሉ በሙሉ የህገልቦናን እምነት ይከተል የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ይህን እምነት የሚከተሉ የማህበረሰቡ ክፍሎች አሉ። በዚህ እምነት ውስጥ የሚመለከው ምዝገና ሲሆን እሱ ከአንዲት ድንግል ሴት በመብረቅ የወለደው አደራ/አይደረኪ የሚባል ሌላው አካል ደግሞ ትልቅ ክብር ያለውና የሃይማኖታዊ ስርአታቸው ሁሉ አስተማሪ ነው። የዚህ እምነት ቁንጮ ወንበር ሲሆን ይህ ሰው ከክብር ዘር የሆነና በብዙ ፀባዩ የተመሠከረለት ሊሆን ይገባል። ጃከረንታ የሚባል የመላዕክት አለቃና ግበሩህ የሚባል አብሳሪ መላእክት በዚህ እምነት የሚታወቁ ሲሆን እነዚህ መላዕክት በሰውና በፈጣሪ መካከል ሆነው የሚያገለግሉ እንደሆኑ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ።

## 4.2 የቅማንት ማህበረሰብ የበአላት መከበር ምክንያት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ

ምንም እንኳን የቅማንት ማህበረሰብ ከአጉራባቹና ምናልባትም ተቀላቅሎት ከሚኖረው የአማራ ማህበረሰብ ጋር ባለው ንክኪ የተለያዩ የአማራ በአላትን የሚያከብር ቢሆንም አንዳንድ ግላዊ የሆኑ በአላት አሉት። አብዛኞቹ በአላት የሚውሉበት ቀን የአማራው ማህበረሰብ በአላት ሲሆኑ የበአላቱ የመከበር ምክንያቶች ግን በእጅጉ የተለያዩ ናቸው። ለእያንዳንዱ በአላት የመከበር ምክንያትም ማህበረሰቡ ተረኮች አሉት። ከተረኮቹ መረዳት እንደሚቻለውም በአላቱ የሚከበሩበት ምክንያት አጉራባቹ የአማራው ማህበረሰብ ከሚያከብርበት ምክንያት የተለየ ነው። የቅማንት ማህበረሰብ ከአማራው በተለየ ከሚያከብራቸው በአላት ውስጥ ምዝገናና ግበሩህ፣ ሽምኩላ (ከረመይኪኩና)፣ ዳኒቃ፣ ዘመን መለወጫና ደመራ ዋናዋናዎቹ ናቸው። እነዚህን ጉዳዮች ከተረኮቻቸው አስረጅ በመውሰድ ለማብራራት ይሞከር።

### 4.2.1 ምዝገናና ግበሩህ

እነዚህ ሁለት በአላት የሚከበሩት በየወሩ ነው። የሚከበሩበት ዕለትም ሀሙስ ነው። የሚከበሩበት ቀን ግን ከወር ወር ይለያያል። ምዝገና የሚውለው ወር በገባ ባለው የመጀመሪያ ሀሙስ ሲሆን ግበሩህ ደግሞ ምዝገና የዋለበትን ሀሙስ ለጥቆ (ተከትሎ) የሚመጣውን ሀሙስ ተሻግሮ ባለው ሀሙስ የሚከበር ነው። ለምሳሌ ህዳር አንድ ቀን 2005 የዋለው ቅዳሜ ነው። ስለዚህ ምዝገና ሀሙስ መዋል ስላለበት ህዳር ስድስት ይሆናል። ግበሩህ ደግሞ አንድ ሳምንት ተሻግሮ በሚመጣው ሁለተኛው ሳምንት በህዳር 20 ይከበራል። ከዚያ ታህሳስ አንድ የሚውለው ሰኞ ቀን ነው። ስለዚህ ምዝገና ወር በገባ በመጀመሪያው ሀሙስ ስለሚከበር ታህሳስ አራት ይውላል። ግበሩህም አንድ ሳምንት ዘሎ ታህሳስ 18 ይውላል። ስለዚህ እነዚህ ወርሃዊ በአላት ወር በገባ በሚል የጊዜ ቀመር ተሠልተው ሀሙስ የሚከበሩ ናቸው እንጂ ቋሚ ቀን የላቸውም። በእነዚህ ቀናት የህገልቦና ካህናት ቅዳሴንና ፀሎትን ያከናውናሉ። መሠዋዕትም ያቀርባሉ።

ምዝገና ብለው የሚያከብሩት አለምና በውስጧ ያሉ ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩበት ነው ብለው ነው። በተደጋጋሚ እንደገለፅኩት ምዝገና የፈጣሪያቸው መጠሪያ ነው። ይህ ፈጣሪያቸው አለምንና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረው ሀሙስ ቀን ነው ብለው ያምናሉ። በዚህም የተነሳ ይህ ዕለት ለእነሱ ትልቅ ስፍራ አለው። ይህ ቀን ለቅማንቶች አጐራባቻቸው አማሮች (የክርስትና እምነትን የሚከተሉት) ሰንበት ብለው እንደሚቀድሱትና እንደሚያከብሩት እሁድ ያለ ነው።

ግበሩህ ደግሞ አብሳሪ መልአክ ነው የሚሉት ሲሆን ይህም መልአክ የአደራን/ የአይደርኪን እናት ለመጀመሪያ ጊዜ ያናገረበት ዕለት ሀሙስ ነው። አይደረኪ የተፀነሰውም የዚያን እለት ነው ይላሉ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የተወለደውም ሀሙስ መሆኑ አይቀርም። ምክንያቱም በተፀነሰ በሰባተኛው ቀን ነው የተወለደው ብለው ስለሚያምኑ ያ የሀሙስ ሰባተኛ ቀን ሀሙስ መሆኑ ነው።

### 4.2.2 ሽምኩላ (ከረመይኪኩና)

ይህ በአል የሚከበረው በመጋቢት ወር እሁድ ቀን ነው። አማራው ደብረዘይት ብሎ በሚያከብረው የበአል ቀን ላይ የሚከበረው ይህ በአል የደብረዘይትን ቀን ለምን እንደሚፈልግ ግን ሊያስረዳኝ የቻለ የመረጃ አቀባይ አላገኘሁም። የአማራው ደብረዘይት በየአመቱ በተለያየ ቀን

የሚውል ነው። ታዲያ ሽምኩላ (ከረምይኪኩና) በየአመቱ ለምን የደብረዘይት ዕለት እንደሚውል አልገባኝም። ምናልባት ግን ማህበረሰቡ የራሱ የቀን አቆጣጠር ስለሌለው የአማራውን (የክርስቲያኑን) የቀን አቆጣጠር ተከትሎ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

ከረመይኪኩና አርብ ለቅዳሜ ያለው ቀን፣ ሽምኩላ ደግሞ ቅዳሜ ለእሁድና ሙሉ እሁድን ጨምሮ ያለው ጊዜ ነው። ለዚህ በአል የሚሆነው ድግስ መዘጋጀት የሚጀምረው ከአርብ ነው። ይህ ከአርብ ጀምሮ እስከ እሁድ ድረስ ያለው የዝግጅት ጊዜ እንቿኩላ ይባላል። በዚህ በአል በእያንዳንዱ የቅማንት ቤት ከፍተኛ ድግስ ይደገሳል። ጠላ ይጠመቃል፣ ደም ይፈሰሳል። ማህበረሰቡ ይህን በአል የሚያከብርበትን ምክንያት በሚከተለው ተረክ ያስረዳል።

> *ከረመይኪኩና ወይም ሽምኩላ ትልቅ በአላችን ነው። ከረመይኪኩና የምልህ አርብ ለቅዳሜ ነው። በእሉ ዋናው ሽምኩላ ነው። የምናከብረው ያማሮች ደብረዘይት ቀን ነው። ይህ ቀን ከፍተኛ ድግስ የሚደገስበት፣ ጠላ የሚጠመቅበት፣ ደም የሚፈስበት፣ የእህል አይነት ተዘጋጅቶ የሚቀመስበት ቀን ነው። መቅመስ ብቻም ሳይሆን ዘርም የሚጣልበትና የሚባረክበት ቀን ነው። ሽምኩላ የምዕአት ቀን ነው። ማን የሚመጣበት? የሞቱ ቅዱሳን አባቶች ከልጅ ልጆቻቸው ቤት ያን ቀን መጥተው በመንፈስ ይደርሳሉ። ያባቶቻችን ቆሌ የሚመጣበት ቀን ነው። ያኔ የአባቶቻችን የሙት መናፍስት ሲመጡ ከኛ ከልጅ ልጆቻቸው ቤት ምንም ነገር ማጣት የለባቸውም። ምናምን የሌላው ደሃ እንኳን ቢሆን ተበድሮም ተለቅቶም መደገስ አለበት። ያን ቀን ዶሮ ይታረዳል፤ ደም ይፈሳል፤ ቃተኛ የሚባል ቅቤ ይቀባል፤ ብርዝ ይበረዛል፤ በተለይ የአዲስ እህል ሸንበራ ቂጣ ይደረጋል። ታዲያ ይህን ሁሉ ድግስ ደግሶ ለራስ መብላት ብቻ አይደለም። የአባቶቻችን ቆሌ ይመጣል ብዬህ የለ? ለነዚያ ላባቶቻችን እንዲደርስ ትንሽ ትንሽ ከያይነቱ በጉሮ በኩል ይፈነጠቃል፤ በየጥጉም ላይ ቁጭ ቁጭ ይደረጋል። ከደሙም ይፈሰሳል። ያን ቀን ድግስ ተደግሶ የማይጠጣበት ቤት ከሆነ እነዚያ በምዕአት የመጡት የአባቶቻቸው መንፈሶች ሳይቀምሱ ስለሚሄዱ ያን ቀን እንደምንም መደገስ ግድ ነው። የአባቶቻችን ቆሌ እንዲጠብቀን። እንቿኩላ አርብን ጀምሮ ድግሱ የሚዘጋጅበት ነው። እንደውም አማሮች "ደብረዘይትን ወደ ቅማንቶች ሀገር ብትሄድ ድግሱ በሽበሽ ነው፣ እንደፈለክ ትውላለህ" ይላሉ።*
>
> *የሽምኩላ ቀን ወደማታ የእህል ዘር በአንድ ሠፌድ ይቀርባል። ከዚያ ወንበሩ ይባርኩታል። ወደምስራቅ ቆመው ፀሎት አድርገው ከባረኩት በኋላ አንድ ገበሬ በሬ ይጠምድና ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አንድ ሾር[18] ሲያርስ ወንበሩ ከነዚያ ዘሮች እየተከተሉ ይጥላሉ። የእህሉን አይነት ጠርቼ አልዘልቀውም። በአካባቢው አሉ የተባሉ አዝዕርት ሁሉ ይባረካሉ። እንግዲህ እነዚያ ያባቶቻችን መናፍስት ባሉበት ዘርም ወድቆ ይባረካል ማለት ነው (መቶ አለቃ ጥጋቡ 2005፣ ጭልጋ/አይከል)።*

---

[18]በእርሻ ላይ ያለ መስመር ወይም ፈር ማለት ነው።

ከተረኩ መገንዘብ እንደሚቻለው የሽምኩላ (የከረመይኪኩና) በአል የሚከበረው የአማራው ማህበረሰብ ደብረዘይት ብሎ በሚያከብረው የፋሲካ ፆም አጋማሽ ላይ ይሁን እንጂ የሚከበርበት ምክንያት ግን የተለየ ነው፡፡ በአካባቢው የሚኖረውና የኦርቶዶክስ ክርስትናን የሚከተለው የአማራው ማህበረሰብ ክፍል የደብረዘይትን በአል የሚያከብረው የአባቶቼ የሙት መንፈስ መጥቶ ይጐበኘናል ብሎ አይደለም፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ይህን በአል የሚያከብርበት ዋነኛ ምክንያት የቀደሙት ቅዱሳን አባት አያቶቻችን የሙት መንፈስ ሊጐበኘንና ሊባርከን ይመጣል በሚል ነው፡፡

የቀደሙት አያቶቻቸው የሙት መንፈስ (በእነሱ አጠራር ቆሌ) በአመት አንድ ጊዜ ወደ ልጆቻቸው የሚወጡት ጕብኙተው ለመሄድ ብቻ አይደለም፡፡ ከመጕብኘት ባሻገር ለቀጣይ የሚዘሩትን የዘር እህል ሳይቀር ለመመረቅና ለመባረክም እንጂ፡፡ ወንበሩ ዘር የመባረክ ስራቸውን የሚያከናውኑት በዚሁ ቀን የሙት መንፈሶቹ (ቆሌዎቹ) ባሉበት ነው፡፡ ምክንያቱም የእነዚህ የቅዱሳን አባቶቻቸው ፀሎት የሠመረ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

አንዳንዶቹ ደግሞ (ለምሳሌ ነጋ ጌጤ) የደብረዘይትን በአል የምናከብረው ፈጣሪ ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት ቀን ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮቼ ይህን ሃሳብ አይቀበሉትም፡፡

4.2.3 የዳኒቃ በአል

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ የሚከበረው ሌላው በአል የዳኒቃ በአል ነው፡፡ ይህን በአል አንዳንዶቹ የቂጣ በአልም ይሉታል፡፡ ይህ በአል የሚከበረው ሀምሌ በገባ በአምስተኛው ቀን ነው፡፡ ይህ በአል በአማራው (የክርስትና እምነትን በሚከተለው) የሰኔ ፆም የሚፈታበት ነው፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ግን ፆም የሚፈታበት አይደለም፡፡ የሰኔ ፆም የሚባልም አይፆሙም፡፡ የእነሱ (የቅማንቶች) ፆም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ እሱን ራሱን የቻለ ስፍራ ስላለው በሚቀጥለው ንዑስ ርዕስ ስር አነሳዋለሁ፡፡

የዳኒቃን በአል የመከበሪያ ምክንያት መቶ አለቃ ጥጋቡ ሲያስረዱ "... ሌላው ትልቁ በአላችን ሀምሌ በገባ በአምስተኛው ቀን የሚከበረው የዳኒቃ በአል ነው፡፡ በዚያን ቀን ቂጣ ይጋገራል፤ ኑግ ይለጠለጣል፡፡ ከዚያም ቂጣና ኑጉን ሰዉም ከብቱም ይቀምሳል፡፡ ለምን ነው እንደዚያ

የምታደርጉ ያልከኝ እንደሆነ ክረምቱን ሰዉንም ከብቱንም ውሃ ሙላት እንዳያገኛቸው ለማድረግ ነው።"

የዚህ በአል የመከበር ምክንያት ፈጣሪያቸው ሰዉንም ሆነ ከብቱን ከክረምት ውሃ ሙላት ይጠብቃቸው ዘንድ ለመለማመን ነው።

4.2.4 የዘመን መለወጫ በአል

የህገልቦና እምነትን የሚከተለው የቅማንት ማህበረሰብ ክፍል ትልቁ የፆም ጊዜ ከነሃሴ አንድ ጀምሮ መስከረም አንድ ድረስ ያለው ነው። የፆማቸውም ምክንያት ከኖህ ጋር በተያያዘ ነው። የዘመን ልውጫውም ቢሆን አዲስ አመትን ከመቀበል በተለየ ነው። ይህን ጉዳይ በተረኮቻቸው እንዲህ ያስረዳሉ።

> *የፆም ቀናችን ነሃሴ አንድ ያነሳ እስከ መስከረም አንድ ያለው ነው። ስንፆምም እንዲህ ዋዛ የለም። ጠዋትን ዘሎ ረፋድ መብላት ወይም በቀን ሁለት ሦስቴ መብላት የለም። እኛ ስንፆም የምንበላው ራታችንን ብቻ ነው። ያም ቢሆን በልክ ነው እንጀ እንብርት እስኪገለበጥ አንወጥቅም። የግድፍትም በዚህ ጊዜ አይበላም። የፆማችን ምክንያት የኖህ ሳንዱቅ[19] ከየፍጥረቱ ሴትና ወንድ ይዛ በጥፋት ውሃው ነሃሴ አንድ የተንሳፈፈች መስከረም አንድ አራራት ተራራ ላይ ምዝገና ሲፈቅድ ኖህ መሬት ወረደ። ያኔም ለጌታ ምስጋና መሬት የሳመበት ቀን ነው። ስለዚህ የመንሳፈፉን ጊዜ ነው መፆም ያለብን። ከዚያ ወዲያማ ነፃ ወጥተናል። አምላክ ቃል ኪዳን ገብቶልን በሰማይ ባንዲራ አሣይቶን ከንግዲህ በውሃ ሠው እንደማይጠፋ ምዝገና ቃል ገብቷል። ስለዚህ መፆም ያለብን ያን የመከራ ጊዜ ኖህ በሣንዱቅ የተንሣፈፈበትን ነው። የኛ ፋሲካችንም መስከረም አንድ ነው። አሁን አማሮች ቅዱስ ዮሐንስ ነው ይላሉ፣ ግን ቅዱስ ዮሐንስ የሚውለው ወር በገባ በሁለተኛው ቀን ነው።*
>
> *መስከረም አንድ ያለፈው ክረምት ማለፉንና የኖህ ሣንዱቅም ወደ ስፍራዋ መድረሷን ምክንያት በማድረግ ይከበራል። ከነሃሴ ሃያ አምስት ጀምሮም ሌሊቱን ሙሉ ጅራፍ እየተጮኸ ይከበራል። ችንቾሀ ነው የሚባለው ጅራፍ ሜጮሁ። በጅራፍም አሮጌው ጨፍጋጋ ዘመን ውጣ አዲሱ ብሩህ አመት ግባ ይባላል። ያኔ በሚለኮሰው ችቦም ከብቶቹንም አዝመራውንም ለኮስ ለኮስ እናደርጋለን። ቤቱንም ችግር ውጣ፣ መከራ ውጣ፣ እየተባለ ግንቡ በእሳቱ መታ መታ ይደረጋል። ሙሉ ጳጉሜንም ወፍ ባልቀመሠሰው የሌሊት ውሃ ገላን መታጠብ አለ። ይሄ ሣምንቱን ሙሉ ነው። ለዘመን መለወጫ የማይታጠብ ልብስና እቃ አይኖርም። ለመስከረም አንድም ልጁን ሁሉ ከሆድ ህመም ለመጠበቅ ፌጦ ቂጣ የሚባል አለ ማንም ሰው ጠዋት በባዶ ሆዱ አንድ ጉርሻ ቂጣውን ይቀምሳል። ያን ሳይቀምስ እህል የሚቀምስ የለም። ተሳስቶ እንኳን እህል እንካ ቢባል "ያዲስ አመት እህል*

---

[19]መርከብ ማለት ነው፡፡

*ሳልቀምስ?!" ነው የሚል። ያን ቂጣ የቀመሠ ሰው አመቱን ሙሉ ሆድ ቁርጠት የለው፣ በሽታም አይዞረው።*

*ያው እንደምታየው የቅማንት ህዝብ የሚኖረው በበረሃ ስለሆነ እባብ አለ። ያ እባብ እንዳይነክስ የዚያን ቀን ዋዜማ (የመስከረም አንድ ዋዜማ) ማታ መድሃኒት አዋቂ በሆኑ ትልልቅ ሰዎች ስር ይማሣል። ተምሶ ከቤትህ ተቀብሮ ያድርና ጠዋት ተነስተህ ትቀምሳታለህ። መራራ ነው። ያንን ስር የቀመሠ ሰው በጋውን እባብ ቢነድፈው አይሞትም። አንዳንዶቹ ደግሞ ስሯን በራፊ ጨርቅ ሠፍተው ባንገታቸው ያስሯታል። ውሃ ስለሚያረክሳት ሲታጠቡ ያወልቋታል። ያኔ ወይ ይረሷታል፣ ወይ ድንገት ስትራጭም ምንም ስትል ውሃ ይነካታል። ያኔ ረከሠች ማለት አይደለም?! ስለዚህ የሚቀመሠው ነው ጥሩ። ያው እኛጋ ትልቁ በሽታ እባብ ነው። በሬውን ነድፎ የገደለ እባብ ሰውን ግን አይገድለውም (አበይ መኮንን 2005፣ ከርከር (ማንጌ) ፤ መቶ አለቃ ጥጋቡ 2005፣ ጭልጋ/አይከል)።*

ምንም እንኳን ይህ በአል የሚከበርበት ቀን ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የዘመን መለወጫ ቢሆንም ለቅማንት ግን የኖህ መርከብ ከጥፋት ውሃው መንሳፈፍ በኋላ ኖህ ምድር የነካበት ቀን ነው በሚል ነው። ቅማንቶች ሁለተኛው አዳም የሚሉት ኖህ ከነሃሴ ጀምሮ በጥፋቱ ውሃ ላይ በመርከብ ተንሳፎ የጭንቀት ጊዜን አሳልፏል። ከዚያ ጭንቀት ነፃ የወጣው መስከረም አንድ ቀን ነው። ስለዚህ ለቅማንት ማህበረሰብ መስከረም አንድ የነፃነት ቀን ነው።

በምድር ላይ ያሉት ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ከኖህ ጋር ያን የጭንቀት ጊዜ አሳልፈው እፎይታን ያገኙበት ጊዜ ነው- መስከረም አንድ። ስለዚህ ይህ ቀን ለቅማንቶች ያለፈው የመከራ ጊዜ መደምደሚያና የአዲስ ህይወት መጀመሪያ ነው። ያለፈውን ዘመን ሀጥያት ለማፅዳትም ንጋትና ወፍ በላየው የለሊት ውሃ ሰውነታቸውን ሙሉ ጳጉሜን ይታጠባሉ። ውሃው የገላቸውን እድፍ እንዲያሶግድ ሳይሆን ባለፈው አመት የሠሩትን ሀጢያት ለማስወገድ የሚገለገሉበት ነው። የመጀመሪያው አዳም ዘሮች በጥፋት ውሃ አልቀው ኖህ ወደሚቀጥለው ትውልድ ሲያልፍ ሀጥያኑ የጠፋት በውሃ ነው። ስለዚህ ያን በማስታወስ ሀጢያትን ከላያቸው ለማስወገድ በጥፋቱ ጊዜ የመጨረሻ ቀናት (በጳጉሜ) ውሃ ራሳቸውን ከሀጥያት ያነፃሉ።

ለአዲስ አመት ጤንነታቸውም ቅድመ ጥንቃቄን ያደርጋሉ። የሆድ በሽታቸውን በፊጦ ቂጣ፣ እባብን ደግሞ በስራስር ለመከላከል ጥንቃቄያቸውን በዚያን ቀን ያደርጋሉ። ስለዚህ ዘመን መለወጫ ያለፈውን የመከራ (የኖህ ስቃይ) ዘመን መጣያና አዲሱን አመት በሰላም ለመዝለቅ የጥንቃቄ ስንቅ መሰነቂያ ቀን ነው። በዚህ እለት ደስታቸውን ለመግለጥ አዳራቸውንም ጅራፍ

ሲያጮሁ ያድራሉ። ይህ ቀን ለቅማንቶች ፋሲካ ነው። በቀን አንዴ እየበሉ ከነህሴ አንድ ጀምሮ የፆሙት ፆም የሚፈታበት።

### 4.2.5 የደመራ በአል

የቅማንት ማህበረሰብ ከሚያከብራቸው በአላት መካከል አንዱ የደመራ በአል ነው። ይህን በአል የሚያከብሩት ግን የክርስቶስ መስቀል ጠፍቶ ንግስት እሌኒ መስቀሉን ለማግኘት የተጠቀመችበትን መንገድ ለመዘከር አይደለም። እነሱ የደመራን በአል ለምን እንደሚያከብሩ የሚያስረዱበት ተረክ እንደሚከተለው ያለ ነው።

> *እኛ ደመራን በጣም ነው የምናከብረው። አሁን አማሮች ደመራን የሚያከብሩት መስቀል ጠፍቶ ተገኘ ነው ምንድን ነው ብለው ነው። የኛ ግን ሌላ ነው። አንዴ ድሮ ወንድማማቾች ተለያይተው አንዱ ጠገዴ አንዱ ደግሞ ከዚች ተራራ ስር (ክርክር ማንጌ በላይ ያለን ተራራ በጣታቸው እየጠቆሙ·ኝ) ይኖሩ ነበር። ለብዙ ጊዜ ሳይተያዩ ክረምት ይገባና እንዲያው ሲያስቡ ይከርማሉ። እንዲያው ሲጨነቁ በቃ እንዴት ከርሞ ይሆን ወንድሜ? እንዴትስ ሆኖ ይሆን እያሉ ሲያስቡ ከርመው መስከረም አስራ ስድስት ቀን ይገናኛሉ። እንግዲህ ያሳይህ የቀኑን መገጣጠም። በቃ አንገት ላንገት ተናንቀው ናፍቆታቸውን ከተገላለጡ በኋላ "እንዲህ ተለያይተን ልንቀር ነው?" ተባባሉ። "አሁንስ አይንህን አየሁህ እንግዲህ ወደፊትስ ደህና መሰንበትህን በምን አውቃለሁ?" ተባባሉና "እንግዲህ አንተም ባለህበት አገር ተራራ ላይ እኔም ባለሁበት አገር ተራራ ላይ ደህና መክረማችንን ለመግለጥ የደመራ እሣት እናቀጣጥል ቀኗም አሁን የተገናኘንባት ትሁን። ቡቃታው[20] እንዲታየን አንድ ላይም እንድናበራ ድሮ አንዴ ሲጮህ ደመራው ይለኮስ" ተባብለው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እየደመሩ ሰላም መሰንበታቸውን ይነጋገሩ ነበር (አበይ መኮንን 2005፣ ክርክር/ማንጌ)።*

የቅማንት ማህበረሰብ የደመራን በአል የሚያከብረው መስከረም አስራ ስድስት ሌሊት ከዘጠኝ እስከ አስር ሰዓት ገደማ ባለው ጊዜ ነው። በአካባቢያቸው ያለው የአማራ ማህበረሰብ ደግሞ መስከረም አስራ ሰባት ከረፋዱ አራት ሠአት እስከ አምስት ሰአት ገደማ ያከብራል። በሸዋ አካባቢ ይህ የደመራ እሳት የሚለኮሰው መስከረም አስራ ስድስት ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰአት ገደማ ነው። ምንም እንኳን ይህ በአል የሚከበርበት ቀን አንድ አካባቢ ቢሆንም የመከበሩ ምክንያት ግን ከአማራው (የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነትን ከሚከተለው) የተለየ ነው። የአማራ ማህበረሰብ የደመራ በአልን የሚያከብርበት ምክንያት ጠፍቶና ተቀብሮ የኖረን መስቀል በጭስ መሪነት በንግስት እሌኒ አስደማሪነት መገኘትን ተከትሎ ነው። መስቀሉም ክርስቶስ የተሰቀለበት

[20]ቡቃታ ማለት ወጋገን እንደማለት ነው።

እንደሆነ በሚቶቻቸው ያስረዳሉ፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ደግሞ (የህገልቦና እምነትን የሚከተለው) በክርስቶስ አያምንም፡፡ ለዚህ ማህበረሰብ የደመራ ጅማሮ ሌላ ነው፡፡ ተጠፋፍተው የኖሩ ወንድማማቾች ከዚያን በኋላ ሠላም መሰንበታቸውን የሚገላለፁበት ተግባቦት ነው፡፡

የቅማንት ማህበረሰብ የደመራ እሳትን የሚለኩሰው በመስከረም አስራ ስድስት ሌሊት በተራራ ላይ ነው፡፡ ተራራ ላይ ያደረጉበትም ምክንያት ሌላ መንደር የእሳቱ ብርሃን ይታይ ዘንድ ነው፡፡ የደመራ እሳቱን የሚለኩሰው መንደር ሰላም የሰነበተ እንደሆነ ብቻ የደመራ እሳቱን ይለኩሳል፡፡ ከዚያ ውጪ ክረምቱን ሰው ሞቶ ወይ ሌላ ከባድ አደጋ ደርሶ እንደሆነ የደመራ እሳት አይለኩስም፡፡ ማህበረሰቡም በዚህ መንገድ ስለሚግባባ ደመራ ሳይደምር ያሳለፈውን መንደር ምን ችግር ገጥሞት ከርሞ ይሆን በሚል ደመራ ያልለኮሰውን መንደር ሊጠይቅ ይሄዳል፡፡

ስለዚህ ለቅማንት ማህበረሰብ የደመራ በአል ክረምቱን ሰላም መሰንበታቸውን የሚገላለፁበት ምልክት ነው፡፡

ከብዙ ተረኮቻቸው መረዳት እንደሚቻለው የቅማንት ማህበረሰብ የክረምት ውሃ ሙላትን ይፈራል፡፡ ይህ ፍርሃት ምናልባት የአዳምን ዘር ካጠፋው የኖህ ዘመን የጥፋት ውሃ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምክንያቱም የቅማንቶች ፆም (ከነሃሴ አንድ አንስቶ መስከረም አንድ የሚፈታው) ምክንያት የኖህ መርከብ በውሃ ላይ የተንሳፈፈችበት ነው የሚል ነው፡፡ ከሚያከብራቸው በአላት መካከል ደግሞ ሦስቱ ይህን ክረምት የቱን ያህል እንደሚፈሩት ያሣያሉ፡፡ ለምሳሌ ሐምሌ አምስት ቀን የሚያከብሩት የዳኒቃ በአል ምዝገና ከክረምት ውሃ ይጠብቃቸው ዘንድ ነው፡፡ ከጳጉሜ ጀምሮ ጅራፍ እያጮሁ የሚያከብሩት የዘመን መለወጫ በአልም ቢሆን ክረምቱን በሰላም ወጣን የአዳምን ዘር ያጠፋው ውሃ እኛን አልነካንም ሲሉ ነው፡፡ የደመራ በአል መከበር ምክንያትም ቢሆን ክረምቱን በሰላም የወጡ መሆናቸውን ለመገላለጽ ነው፡፡

በአጠቃላይ የቅማንት ማህበረሰብ አንዳንድ በአላትን የሚያከብርበት ምክንያት በአካባቢው ያለው ሌላ ማህበረሰብ ከሚያከብርበት ምክንያት የተለየ ነው፡፡ ይህንንም ከተረኮቻቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 4.3 የቅማንት ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታ በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ

የቅማንት ማህበረሰብ አንዳንድ የጋብቻ ሁኔታዎች ከአጎራባቻቸውና አብሯቸው ከሚኖረው ከአማራው ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታዎች የተለዩ ናቸው። እነዚህንም ጉዳዮች በቃል ተረኮቻቸው ያስረዳሉ። በዚህ ርዕስ ስር የጋብቻ ሁኔታዎች ብዬ ላስረዳ የወደድኳቸው ነገሮች የጋብቻ ዘር ቆጠራ፣ ማርኮዛ፣ የጋብቻ እድሜና ሁለተኛ ጋብቻን ነው። እነዚህ ነገሮች የቅማንትን ማንነት የሚያሳዩ ጉዳዮች (ሁኔታዎች) ናቸው።

#### 4.3.1 የጋብቻ ዘር ቆጠራ

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሁለት አውራ ዝርያዎች (የዘር ግንዶች) አሉ። አንደኛው ክብር ሲሆን ሌላው ደግሞ ይተንቲ ነው። እነዚህን ሁለት የዘር ሀረጎች አስመልክቶ ሀይማኖታዊ ማንነታቸውን ስተነትን ያስተዋወቅሁ ቢሆንም ይህን ጉዳይ እዚህም ማንሳት ተገቢ ነው።

እነዚህ ሁለት ዝርያዎች አንዱ የሌላውን ያገባል እንጂ እርስ በእርሳቸው አይጋቡም። ለምሳሌ የይተንቲ ወንድ የይተንቲዋን ሴት አያገባም፤ የክብርም ወንድ የክብሯን ሴት አያገባም። መጋባት የሚችሉት ክብሩ ከይተንቲዋ ወይም ይተንቲው ከክብሯ ነው። እንዲህም ሆኖ እስከሰባት ዘር መጋባት አይፈቀድም። እዚህ ላይ ሊጤኑ የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ። አንደኛው ጉዳይ እነዚህ ሁለት የዘር ሀረጎች ተጋብተው የሚወልዱት ልጅ የትኛው የዘር ሀረግ ይኖረዋል? ሌላው የክብር ወንድ የክብሯን ሴት ወይም የይተንቲው ወንድ የይተንቲዋን ሴት አያገባም እየተባለ ደግሞ ሰባት ዘር መቁጠር ማለት ምን ማለት ነው? እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች መመለስ የሚገባቸው ናቸው።

ሁለቱ ግንድ ዘሮች ተጋብተው የሚወለደው ልጅ የትኛውን ዘር ይይዛል? በቅማንት ማህበረሰብ የዘር ቆጠራ ወቅት ማንኛውም ሰው የሚይዘው የአባቱን ዘር ነው። የክብር ወንድ የይተንቲዋን ሴት አግብቶ የሚወለዱት ልጆች ሁሉ ያባታቸውን የክብር ዘር ይሆናሉ። የይተንቲው ወንድ የክብሯን ሴት አግብቶ የሚወለዱት ደግሞ የአባታቸውን ዘር ስለሚይዙ የይተንቲ ዘር ይሆናሉ። ይህን ጉዳይ በተረካቸው ሲያስረዱ፦

> *የዘር ርቀት አሁን ለማግባት ሰባት ዘር ተቆጥሮ ነው። ግን ሊያውም የክብሩ የክብሯን አያገባም፤ ይተንቲውም ቢሆን እስበሱ አይጋባም። የክብር ወንድ የይተንቲን ሴት አሊያም የክብር ሴት የይተንቲን ወንድ ታገባለች እንጂ ክብሩ*

*ክብሯን አያገባም፣ የቱንም ያህል ብትርቅ አያገባም፣ እህቱን እንዳገባ ነው የሚቆጠረው። የክብሩ ወንድ የይተንቲዋን ሴት አግብቶ የሚወለዱት ክብር ነው የሚሆኑት። እኛ ጋር ዘር አቆጣጠር ባባት ነው። አሁን እኔ ዘር ብቆጥር ወደ ጎን እናቴን የናቴን እናት አልጠራም። ያባቴን ተከትዬ ነው የምቆጥረው። የይተንቲውም ወንድ ክብሯን አግብቶ የሚወልዳቸው ይተንቲ ነው የሚሆኑት ( አበይ መኮንን 2005፣ ክርክር ማንጌ)።*

ስለዚህ እነዚህ ሁለት የዘር ሀረጎች እርስ በእርስ ሳይሆን አንዱ የሌላውን ያገባል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሰባት ቤት መቁጠር ለምን አስፈለገ? ምክንያቱም አንዱ የሌላን ዘር አይደለም የሚያገባው? የሚል ጥያቄ መፈጠሩ አይቀርም። ምንም እንኳን ከተለያየ ዘር ቢሆኑም የቀረበ ዝምድና የሚፈጠሩባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ወንድምና እህት የሆኑ ሁለት የክብር ዘሮች ከይተንቲ ሲጋቡ የእነዚህ የሁለቱ ልጆች በተለያየ የዘር ሀረግ ውስጥ መግባታቸው ነው። ከወንዱ ክብር የሚወለዱት ልጆች የክብር ዘር ይሆናሉ። ከሴቷ የሚወለዱት ደግሞ የአባታቸውን ዘር ይዘው ይተንቲ ይሆናሉ። ስለዚህ በእነዚህ ሁለት የአንድ አያት ልጆች መካከል ጋብቻ እንዳይፈፀም ሰባት ዘር መቁጠር አስፈለገ።

4.3.2. ማርኮዛ

ማርኮዛ ማለት ምናልባት መባረክ ተብሎ ሊተረጎም ይችል ይሆናል። የክብር ወንድ የይተንቲዋን ሴት ሲያገባ ግንባሯ ላይ ይሰነጥባታል። ይህ የሚሆነው እቤቱ የገባች ዕለት ነው። የምትባረክበት ቦታም ግንባሯ ላይ በሰርኗ አቅጣጫ በሽፋሽፍቶቿ መካከል ነው። ምናልባት ይህ ድርጊት የመነጨው አደራ/አይደረኪ ሲያገባ የባረካትን ሴት መነሻ በማድረግ ሳይሆን አይቀርም። ክብሩ የባረካትን ይተንቲ ማንም ሰው አይመኛትም። እሱም ቢሆን ከባረካት በኋላ በህይወት እያለች ፈፅሞ መፍታት አይችልም። ማርኮዛ ለቅማንቶች የጠበቀ የትዳር መሀላና ቃል ኪዳን እንደሆነ በቃል ተረኮቻቸው ያስረዳሉ።

4.3.3. የጋብቻ እድሜ

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሴት ልጅ በአስራ አምስት አመቷ ወንድ ደግሞ በአስራ ስምንት አመቱ የመጀመሪያ[21] ጋብቻቸውን ይፈፅማሉ። ወንድ በአስራ ስምንት አመቱ ለማግባቱ የሚያነሱት የቀደመ ተረክ ባይኖርም ቤተሰብ ለማስተዳደር የሚያስችለውን አስተሳሰብና ሰርቶ

[21]የመጀመሪያ ጋብቻ የተባለበት ምክንያት ሚስቱ የሞተችበት ወንድ ወይም ባሏ የሞተባት ሴት ለሁለተኛ ጊዜ ስለሚያገባና ስለምታገባ ነው፡፡ ይህ ሁለተኛ ጋብቻ ደግሞ የእድሜ ገደብ የለውም፡፡ ግን ከአስራ ስምንት አመት እና ከአስራ አምስት አመት በላይ ነው፡፡

የመብላት እንዲሁም ሰው የማኖር አቅም የሚያገኘው በዚህ እድሜ እንደሆነ ይገልፃሉ። ሴቷ በአስራ አምስት መአቷ የምትዳርበትንና ከዚያ እድሜ በታች ያለች ሴት መዳር የማይፈቀድበትን ምክንያት ደግሞ በሚከተለው ተረክ ያስረዳሉ።

> *በክመንት ሴት በአስራ አምስት አመቷ ወንድ ደግሞ በአስራ ስምንት አመቱ ያገባል። ከዚህ ባነሰ እድሜ ማግባት የተከለከለ ነው። ይሄ አሁን መንግስት በልጅነት ጋብቻ ምንትስ የሚለው እኛ ጋር አልመጣም። ምክንያቱም እኛ በልጅነት አናጋባም። አደራ ወደ ምድር ለመምጣት በፈለገ ጊዜ በምዝገና ትዕዛዝ ሲወለድ አስራ አምስት አመት ከሞላት ድንግል ሴት ነው ተረግዞ የተወለደ። ስለዚህ ከዚያ እድሜ በታች አትችልም። ጌታም የተወለደው ከደረሰች ሴት ነው (መቶ አለቃ ጥጋቡ 2005፣ ጭልጋ/አይከል)።*

አስራ አምስት አመት የሞላት ሴት ለመፀነስ ብቁ ነች ብለው ስለሚያምኑ ሴት ልጆቻቸውን ከዚህ እድሜ ባነሰ አይድሩም። ለዚህም ፋና ወጊያቸው አደራ (አይደረኪ) ነው። እሱ ልጃገረድ ከሆነች የአስራ አምስት አመት ሴት ነው የተወለደው። ይህች ሴት በቀደመ ዕድሜዋ ከወንድ ያልተገናኘችና ተከብራ የኖረች ናት። ያም የሆነበት ምክንያት እስከዚያ እድሜ ድረስ ራስን ጠብቆ መኖር እንደሚቻል ለማሳየት ነው። ስለዚህ ሴቷ እስከአስራ አምስት አመት የቆየች እንደሆነ በሁለንተናዋ ስለምትጠነክር እስከዚያ እድሜ ድረስ ትጠበቃለች እንጂ በቀደመ እድሜዋ አታገባም።

### 4.3.4. ሁለተኛ ጋብቻ

በቅማንት ማህበረሰብ ጋብቻ ውስጥ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ወይም አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ብቻ ተወስነው ይኖሩ ዘንድ የተገባ ነው። ሀይማኖታቸውም ሆነ ባህላቸው ከአንድ በላይ እንዲያገቡ አይፈቅድም። በቀደመው ዘመን ግን አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት በላይ ያገባ ነበር። ለምሳሌ ክብር (በአንዳንድ ተረኮቻቸው አይደረኪ) ሶስት ሚስቶችን አግብቶ ነበር። ያኔ ይህ የሆነበት ምክንያት ዘራቸው ትንሽ ስለነበር ዘራቸውን ለማባዛት ካለ መሻት እንደሆነ ያስረዳሉ። እንደውም፣ "ድሮን ያነሳህ እንደሆነ ወንድምና እህትም በአንድ ማህፀን ተፀንሶ በአንድ አድጎ ይጋባ ነበር" ይላሉ። ምክንያቱም ያኔ በዚህ መንገድ ካልሆነ በስተቀር ትውልድን ማስቀጠል ስለማይቻል ነበር። አሁን ግን ያ የለም። ነገር ግን በቅማንት ሚስቱ የሞተችበት ወንድ ሌላ ሴት ማግባት ይችላል። ቅማንቶች ይህን አስመልክቶ ሲያስረዱ።

*...ሌላው በእኛ ባህል አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ብቻ የተገባች ናት። ነገር ግን ከሞተችበት ማግባት ይፈቀዳል። አሁን ያማራ ቄስ ሚስቱ የሞተችበት እደሆነና ሌላ ሴት ሊያገባ ከሆነ ቅስናውን አፍርሶ ነው። የክመንት ቄስ ግን ክሶ ያገባል እንጂ ቅስናው አይፈርስም። ... ክሶ ማለት ቆርቦ ማለት ነው። አቁርቦ ቆርቦ ነው የሚያገባ ... ቁርባን እንዴት ነው?! አግቢው ድግስ ይደግሳል። ከዚያ የክመንት ቄሶቸ ተሰብስበው ሲቀድሱ ያድራሉ። ሙሉ ቅዳሴ ሲያድሩ በዋንዛ እንጨት ገበታ[22] ንፁህ ውሃ ይሞላል። ውሃውን በቅል ቀድቶ ከወንዝ የሚያመጣውም ቄስ ነው። ከዚያ ክፍቱን ሲቀደስበት ያድራል። ከዚያ ያ ውሃ እንደፀበል ሆነ ማለት ነው። ከዚያ ጠዋት ያቺ የምታገባዋ ሴትና ያ የሚክሰው ሰውዬ ቅዳሴ በታደረበት የተባረከ ውሃ ይጠመቃሉ። ከዚያ ቄስ በባረከው ስጋ እንዲቀማመሱ ይደረጋል። ይሄ ነው እንግዲህ ቁርባን። አሁን በቅርብ ቄስ አማረም ሚስት ሙታው ቆርቦ የይተንቲዋን ዘር ፈልጐ አግብቷል (መቶ አለቃ ጥጋቡ 2005፣ ጭልጋ/አይከል)።*

ከተረካቸው መገንዘብ እንደሚቻለው በቅማንት ካገቡ በኋላ ፈትቶ ማግባት አይፈቀድም፤ ነገር ግን በሞት የተለያዩ እንደሆነ በሕይወት ያለው ሰው ያገባል። ያም ሲሆን የሀይማኖት ስርአታቸው እንደሚፈቅደው ደግሰውና ቅዳሴ በታደረበት ውሃ ተጠምቀው ነው።

በአጠቃላይ የቅማንት ማህበረሰብ በአንዳንድ ባህላዊ ክንውኖቹ ከአጎራባቾቹ ማህበረሰቦች ይለያል። እነዚህ ልዩነቶቹም የማንነቱ መገለጫዎች ናቸው ሊባሉ ይችላሉ። እነዚህን ማንነቶቹን ደግሞ በተረኮቹ ይገለፃል።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የቅማንት ማህበረሰብ በአሁኑ ወቅት በመግባቢያነት የሚገለገለው የአማርኛን ቋንቋ በመሆኑ ከአጎራባቹ የአማራ ማህበረሰብ በቋንቋ የተለየ አይደለም። አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ግን በሀይማኖቱና በአንዳንድ ባህላዊ ክንውኖቹ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል የተለየ ነው።

---

[22]ከእንጨት የሚሰራ ሣፋ መሳይ የቤት እቃ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ተቀዳሚ አላማ የቅማንት ማህበረሰብ የሚናገራቸውን ዝርው የቃል ተረኮች ሰብስቦ ማንነትን ከመገንባትና ከመግለፅ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መተንተን ነበር፡፡ ይህን አላማ ለማሳካትም ማህበረሰቡ በብዛት ሠፍሮ ከሚገኝባቸው ሁለት ወረዳዎች (ላይ አርማጮሆና ጭልጋ) ውስጥ ከሚገኙ ስድስት ቀበሌዎች (ትክል ድንጋይ፣ ከርከር (ማንጌ)፣ አይከል፣ ተበርሚካኤል፣ ተንብራና አርሁና ጊዮርጊስ) መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡

ከትንተናው በተገኙ ውጤቶች መሠረትም ተረኮቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ማንነትን የመገንባትና የመግለፅ ተግባር አላቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በሃይማኖቱ፣ በአላትን በሚያከብርባቸው ምክንያቶችና በጋብቻ ሁኔታው ከአጐራባቾቹ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚለይበትን ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ተረኮቹ ማህበረሰቡ ከሌሎች አጐራባች ማህበረሰቦች የሚለይበትንና የራሱ መገለጫ የሆኑ ማንነቶቹን መገንቢያና ማንፀባረቂያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

የቅማንት ማህበረሰብ በተረኮቹ የሚያነሳቸው ዋና ዋና የማንነት መገለጫዎች ሃይማኖት፣ በአላትና የጋ ብቻ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ሃይማኖቱን በተመ ለከተ የቅማንት ማህበረሰብ አብዛኛው አባላት የኦርቶዶክስ ክርስትናን የተቀበሉ ቢሆኑም አስቀድሞ የነበራቸውን የህገልቦና እምነትን ይዘው የቀጠሉ የማህበረሰቡ አባላት አሉ፡፡ የኦርቶዶክስ ክርስትና የተቀበሉትም ቢሆኑ ከህገልቦና እምነት አስተሳሰብና አምልኮ ስርአት የፀዱ አይደሉም፡፡

በህገልቦና ሃይማኖት ውስጥ ሁሉን የፈጠረ ምዝገና የሚባል አምላክ ነው፡፡ እሱ በመብረቅ ከድንግል ሴት የወለደው አይደረኪ ደግሞ የሃይማኖታዊ ክንውኖቻቸው ሁሉ አስተማሪ እንደሆነ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡ ይህንን ሃይማኖት በበላይነት የሚመራው ወንበር ሲሆን የአምልኮ ስርአቱን የሚያከናውኑት ደግሞ ቄሶች ናቸው፡፡ ቄሶቹ ሁለት አይነት ናቸው፤ አንደኛው የከመዘና ቄስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የይተንቲ ቄስ ይባላል፡፡ የወንበሩና

የከመዘናው ቄስ የክብር የዘር ሀረግ ያላቸው ሲሆኑ የይተንቲው ቄስ ደግሞ የይተንቲ የዘር ሀረግ ያለው ነው፡፡

የህገልቦና ሃይማኖት ፅሁፍ አልባ ነው፡፡ በዚህ ሃይማኖት ውስጥ እያንዳንዱ ስርአት የሚከናወነው በቃል ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን አንድም ነገርን መዘንጋት እንደሌለ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡ ሃይማኖቱ ከሌሎች ሃይማኖቶች አንፃር እጅግ ጥንታዊ እንደሆነ አማኞቹ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡

የህገልቦና ሃይማኖት የፀሎት ስፍራ ድግና/ዱቢት በመባል ሲታወቅ ይህ ቦታ በደን የተሸፈነ፣ የማይታረስ፣ ከብት የማይሠመራበትና ንፁህ ስፍራ ነው፡፡ የመሥዋዕት ስፍራቸው ደግሞ የተመረጡ ተራራዎች ናቸው፡፡ በዚህ ሃይማኖት ውስጥ የሰስና የአሣ ስጋ መብላት የተከለከለ እንደሆነም ከተረኮቻቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

የቅማንትን ማህበረሰብ የበአላት መከበር ምክንያቶችን በተመለከተ ማህበረሰቡ ከአጐራባቾቹ ማህበረሰቦች በተለየ ምክንያት የሚያከብሯቸው በአላት አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ምዝጋናና ግበሩህ፣ ሽምኩላ (ከረመይኪኩና)፣ ዳኒቃ፣ ዘመን መለወጫና ደመራ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ በአላት በሚከበሩባቸው ቀናት ሌሎች ማህበረሰቦችም የሚያከብሯቸው በአላት ቢኖሩም የመከበራቸው ምክንያት ግን የተለያየ ነው፡፡

ምዝገናና ግበሩህ ወርሃዊ በአላት ሲሆኑ ወር በገባ የመጀመሪያው ሃሙስ ምዝገና ሲሆን አንድ ሀሙስ ዘሎ በሁለተኛው ሃሙስ የሚውለው ደግሞ ግበሩህ ይባላል፡፡ የተቀሩት በአላት ግን አመታዊ በአላት ናቸው፡፡ ሽምኩላ (ከረመይኪኩና) የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ደብረዘይት ብለው በሚያከብሩበት ቀን የሚከበር ሲሆን የመከበሩ ምክንያትም የቀደሙ አባት አያቶቻችን የሙት መንፈስ ሊጐበኘንና ሊባርከን ይመጣል በሚል ነው፡፡ ዳኒቃ ደግሞ የሀምሌ ወር በገባ በአምስተኛው ቀን የሚከበር ሲሆን ይህ በአል የቂጣ በአል በመባልም ይ ታወቃል፡፡ የበአሉ የመ ከበሪያ ምክንያትም ፈጣ ሪያቸው ከክረምት ውሃ ይጠብቃቸው ዘንድ ለመለማመን ነው፡፡ የዘመን መለወጫ በአልም ከኖህ ዘመን የጥፋት ውሃ ጋር በተያያዘ የሚከበር ነው፡፡ ኖህ ከነሃሴ አንድ ቀን እስከ መስከረም አንድ ቀን በመርከብ (ቅማንቶች እንደሚሉት ሳንዱቅ) ውስጥ ሆኖ በጥፋት ውሃው ላይ ሲንሳፈፍ

ቆይቶ መስከረም አንድ በአራራት ተራራ ላይ ለፈጣሪው (ለምዝገና) ምስጋና ያቀረበበት ቀን ነው፡፡ የመንሳፈፊያውን ጊዜ በፆም፣ ነፃ የወጣበትን ደግሞ በደስታ ያከብራሉ፡፡ ሌላው በአላቸው የደመራ በአል ሲሆን የዚህ በአል የመከበሪያ ምክንያትም ከሌላው ማህበረሰብ በተለየ ነው፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ የደመራን በአል የሚያከብረው ሠላም መሠንበቱን ለመግለፅ ነው፡፡

የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫ ከሆኑት ጉዳዮች የመጨረሻው የጋብቻ ሁኔታቸው ነው፡፡ ከተረኮቻቸው መገንዘብ እንደሚቻለው በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሁለት ትልልቅ የዘር ሀረጎች አሉ፡፡ አንደኛው የዘር ሀረግ ክብር ሲባል ሌላው ደግሞ ይተንቲ ነው፡፡ የይተንቲ የዘር ሀረግ ያለው ወንድ የይተንቲን ሴት አያገባም፣ የክብር የዘር ሀረግ ያለውም ወንድ የክብሯን ሴት አያገባም፣ የክብር ወንድ የይተንቲዋን ሴት የይተንቲውም ወንድ የክብሯን ሴት ያገባል፡፡ ሁለቱ ተጋብተው የሚወልዷቸው ልጆች የአባታቸውን የዘር ሀረግ ይይዛሉ፡፡

የቅማንት ሴት የመጀመሪያ ጋብቻዋን ለመፈፀም እድሜዋ አስራ አምስት ሊሆን ይገባል፣ የወንዱ የመጀመሪያ ጋብቻውን የመፈፀሚያ እድሜ ደግሞ አስራ ስምንት ነው፡፡ አግቢው ወንድ ክብር ከሆነ ሚስቱን (ይተንቲዋን) እቤቱ ሲያስገባ ግንባሯ ላይ ይሠነጥባታል፣ ይህም ማርኮዛ ይባላል፡፡

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ በሞት ካልሆነ በስተቀር ፍቺ የተከለከለ ነው፡፡ አንድ ወንድ ሚስቱ የሞተችበት እንደሆነ ግን በካሣ ስርአት ሁለተኛ ጋብቻ ሊፈፅም ይችላል፡፡

## 5.2 የይሁንታ ሃሳብ

- በጥናቱ እንደታየውና ሌሎች ፀሀፍትም እንደሚሉት ቃል ተረክ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ከመግለፅ አንፃር ትልቅ ሚና አለው፡፡ ስለዚህ በማንነት ላይ ትኩረት አድርገው ጥናት ማካሄድ የሚፈልጉ ባለሙያዎች በቃል ተረክ ጥናት ላይ ትኩረት ቢያደርጉ ብዙ የሚጠቅሙ ስራዎችን ይሠራሉ፡፡
- በጥናቱ እንደታየው ቃል ተረኮቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ እውቀትና ማንነት በውስጣቸው ሠፍሮ ይገኛል፡፡ ስለዚህ እነዚህ የቃል ተረኮች ተሠንደው ቢቀመጡ ስ ለማህበረሰቡ ማወቅ ለሚፈልግ

ማንኛውም አጥኚ ስለሚጠቀሙ የየወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች ተረኮችን የመሠነድ ስራ ቢሠሩ ጥሩ ነው፡፡

- አንዳንድ ታሪኮች በታሪክ ፀሀፍቱ አይንና በማህበረሰቡ ትረካዎች ውስጥ የተለያዩ እውነታ ስላላቸው እንዲህ ያሉ ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚያካሂዱ እንደ ታሪክ ያሉ የትምህርት ክፍሎች በጥናታቸው ውስጥ የማህበረሰቡን ትረካዎችም ቢፈትሹ መልካም ነው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ለማ ንጋቱ፡፡ "በየም ብሄረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት 'ምስል' ትንተና፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረምረቃ ትምህርት ቤት 1999፡፡

ማንያለው አባተ፡፡ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሙያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999፡፡

ምንዳ ገብሬ፡፡ "የጌዲኦ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሙያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000፡፡

ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፡፡ <u>የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ፣ ኑብያ-አክሱም-ዛጉዮ እስከ አፄ የኩኑ አምላክ ዘመነ መንግስት 1ኛ መፅሐፍ፡፡</u> አዲስ አበባ፣ ትንሳዔ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1951 ዓ.ም፡፡

ነጋ ጌጤ፡፡<u>የቅማንት ህዝብ ታሪክ፡፡</u> ጐንደር፣ ዳሽን ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡

አለቃ ታዬ፡፡ <u>የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአጭር ቃል የወጣ፡፡</u> አስመራ፣ ወንጌተያት ማህበር ማተሚያ፣ 1920፡፡

አማረ ሞላ፡፡ "የሽካቾ ብሄረሰብ ሃገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሙያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999፡፡

ከሁሉም በላይ፡፡ "የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርአቶች ጥናት፡፡" በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2004፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ <u>መጽሐፍ ቅዱስ፡፡</u> አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ <u>አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡</u> አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የካቲት 1993፡፡

ያሬድ ሀይሌ፡፡ <u>የጐንደር ታሪክ፡ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንፃር፡፡</u> አዲስ አበባ፣ ሜይ ኘሪንተርስ ኃ.የተ.የግ.ማ፣1999፡፡.

ደስታ ተክለ ወልድ። አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

ፊቃደ አዘዘ። "አፋዊ ኪነተ ቃል" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ መጽሔት፣ ቁጥር 2፣ ገጽ 3-26፣ 1984 ዓ.ም።

Abdulkadir Haji Jima. "Some Cultural Elements as Reflected in Somalia Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1982.

Abraham Alemu. "Jima Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2000.

_____ "Narrating Local Identity among the Southwestern Oromo of Ethiopia: Case of Jimma and Gera." African Study Monographs 33(1) pp. 17-47, 2012.

Anna De Fina. Identity in Narrative: A Study of Immigrant Discourse.Clark University, 2003.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore." The Journal of American Folklore society, vol.67, No. 266 (Oct.- Dec., 1954), 333-349, American Folklore Socity, http://www.jestor.org/stable/538099/URL.

___ "The Forms of Folklore: Prose Narrative." The Journal of American Folklore, Vol.78, No.307 (Jan.-Mar.,1965), 3-20, American Folklore, http://www.jestor.org/stable/538099.

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narrative: Ethnic Genres and Social Functions." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature,Addis Ababa University, 1999.

Ben-Amos,Dan. Folklore in context. South Asian puplisher, New Delhi,1982.

Bruce, James M. Travels of Discover the Source of the Nile, 1768-73. (5 Vols.) Edinburgh: G. and J. Robinson, 1790.

Degh, Linda. "Oral Folklore Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) Folklore and Folk life: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dundes, Alen. Folklore Matters.USA, The University of Tennessee press, 1986.

Erikson, Erik H. Identity: Youth and Crisis. New York: Norton, 1968.

Gemst, F.C The Qemant Agaw of Ethiopia: A Study in Cuturee change of apagan Hebraic Culture. Unpublished Ph.D. Thesis, 1967.

______ The Qemant: A Pagam-Hebraic Peasantry of Ethiopia. Case studies in cultural Anthropology. New York: Holt Rinehart and Wilson, 1969.

Hall, S. Who needs identity? In P. Du Gay, J. Evans, & P. Redman (Eds.), Identity: Areader (pp. 15–30). London: Sage Publications and the Open University, 2000.

Jens Brockmeier and Donal Carbaugh (Ed.).Narrative and Identity. John Benjamin's Publishing Co. Amsterdam, 2001.

Kerby, A.Narrative and the self. Bloomington/Indianapolis: IndianaUniversity Press, 1991.

Kroskrity, P. "Identity." Journal of Linguistic Anthropology,Vol. 9(Sep.–Oct.,2000), 111–114.

Lewis P. Hinchman and Sandra K., Hinchman. (eds) Memory, Identity and Community.State University of New York press, 2001.

Mark R. Gover. The Narrative Emergence of Identity.Michigan State University.

Mlakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Monika Fludernik. An Introdaction to Narratology.Taylor &Francis e-USA & Canada, 2009.

Oring, Elliot. Folk Group and Folklore Genres: An Introduction. Logan, Utah: Utah University Press, 1986.

Quirin, James. The Beta Israel (Falasha) in Ethiopian History: Cast Formation and Culture Change.Ph.D Dissertation. University of Minnesota. 1977.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narrative: A Contextual Study" M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

Sims, Martha C. and Martine Stefphens.Living Folklore, An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan, Utah: Utah State University Press. 2005.

Tajfel,H. Humangroups and social categories: Studies in social psychology. Cambridge: Cambridge University Press, 1981.

Tesfaye Gebre Mariam. "A study of Major Themes in Jablawi Folktales" M.A. Thesis, Department of Foreign

Untingford, G.W.B. and Bekingham, C.F Some Records of Ethiopia (1593-1646).Printed for the Hakluyt Society.London, 1954.

Yihenew Jember. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives West Gojam." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Zelealem Leyew. The Kemantney Language: A Sociolinguist and Grammatical Study ofLanguage replacement. PhD: Dissertation. RUDIGER Koppe VerlaG. Kerlag.Loln, 2003.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- ከመስክ የተሰበሰቡ ተረኮች

### ተረክ አንድ

ድሮ የአማራው ህዝብ የቅማንትን ህዝብ ለማጥቃት ያሰበት ጫካ ድረስ ይሄዳል። ይህን የተረዳው የቅማንት ህዝብ በሚኖርበት ጫካ ውስጥ ያለውን ዛፍ ሁሉ በቁመቱ ልክ እየፈለፈለ በውስጡ ይሸሸግ ነበር። በኋላም የአማራው ህዝብ ሲፈልግ ያጣውና ሲመለስ ሲል ቅማንቴው ከተሸሸገበት ፍልፍል ዛፍ ውስጥ በመውጣት የአማራውን ህዝብ ያጠቃዋል። ያኔ ያመለጡት ቅማንቱን ከእንጨት ውስጥ ሲወጣ አይተውታልና የእንጨት ልጅ ነው አሉት።

### ተረክ ሁለት

አንተራ የሚባል ሀገር አለ እዚህ ጭልጋ፡፡ ቴዎድሮስ ሲሸፍቱ ባለቤታቸውን ተዋቡን ጭልጋ ላሉ አጎታቸው፣ ለአባ ኮልባ አደራ ሰጥተዋት ነበር አሉ፡፡ አባ ኮልባም ተዋቡን እቤታቸው ቢያስቀምጧት ጠላት በቀላሉ ሊያጠቃት ይችላል በማለት አንድ ዋሻ ውስጥ ሸሸጓት አሉ፡፡ ዋሻውን ለመጠበቅም የቅርብ ወገን የሆኑ ውስን ሰዎች በየተራ ይጠብቁ ነበር አሉ፡፡ በኋላ አሁን ያንተ ተራ ነው፣ አሁን የኔ ተራ ነው እየተባባሉ በተራ ይጠብቁ ስለነበር ዋሻውን አንተራ አሉት፡፡ “እኒ-ተራ” ማለት በቅማንተኛ የእኔ ተራ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ ዋሻው ያለበት ሀገር በዚህ ስያሜ ይጠራ ጀመር፡፡

### ተረክ ሦስት

ሽውታብ የሚባል ሀገር አለ፡፡ ስሙ የወጣው በቅማንትኛ ነው፡፡ አንዱ፣ ከአንዱ ሀገር ተነስቶ ወደ ሌላ ሀገር ሲሄድ አንድ መንደር ይደርሳል፡፡ ረሀብ ፀንቶበት ስለነበረም “ራበኝ” ቢል፣ “እዚህ አንዱ ጋር ገብተህ ቆሎ አትለምንም?” ይሉታል “ሺዎታታብ” አትለምንም ቆሎ ማለት ነው፡፡ ሰውየውም እንደተባለው ያደርጋል፡፡ ከዚያ ወዲህ ሀገሩ “ሽውታብ” ተባለ፡፡

### ተረክ አራት

ድሮ ነው አሉ አማራ፣ እስላምና ቅማንት የሚተዳደሩበትን ህግ ለመቀበል ወደ ደባ ሄዱ፡፡ እሱም ለአማራው፣ “በል ይሄ ህግህ ደንብህ ይሁን በዚህ ተዳደር” ብሎ መፅሀፍ ቅዱስ

ሠጠው፡፡ ለእስላሙም፣ "በዚህ እደር" ብሎ ቁራን ሠጠው፡፡ ቅማንቱ፣ "ለኔስ" ቢለው፣ "አንተ አስተዋይና የማይዘነጋ ልቦና ስላለህ ህግን በልብህ አኖራለሁ በሱ ህግም ትተዳደራለህ" አለው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቅማንት ማህበረሰብ በተፃፈ ነገር ሳይሆን በልቡ ባለው ህግ ይተዳደር ጀመር፡፡

## ተረክ አምስት

የቅማንት ማህበረሰብ ለገበያ ወደ ሌ ቦታ ሄዶና ተገበያይቶ ሲመለስ ወንዝ ላይ እግሩንና እጁን ተጣጥቦ ይመለሳል። ያልተጠመቀውና በአማራው ባህል ያልተበከለው ቅማንት ለደባ ፀሎት ለማድረስ ንፁህ መሆን አለበት። ክፉ ከሚናገረውና እኩይ ከሚፈፅመው አህዛብ ጋር ገበያ ውስጥ ተደባልቀው ስለነበር ከዚያ ህዝብ ተነጥለው ወደራሳቸው ቤተስብ ከመቀላቀላቸው በፊት በውሃ ይታጠባሉ። ስድብን፣ ክፉ ነገርን ሀጢያትን ይዘው ወደቤታቸው ላለመግባት።

## ተረክ ስድስት

ከበረሃ ግንድ እየመጣ ግንድ መጣያ እየተቀመጠ የፋሲል ግንብ ተሠራ። ግንቡ ሲሠራም ግንባዛቹሳ የሚባል አሠሪ ነበር። ይህ ሰው ሙሉ ለሙሉ ቅማንት ነው። ግን ግንቡ ሲነሳ ፋሲልን እንጂ ግንባዛቹሳን የሚያነሳ የለም። በግንቡ ስራ ላይ ሙሉ ለሙሉ ይሳተፉ የነበሩትም ቅማንቶች ናቸው። ግን እነሱን የሚያነሳ የለም።

## ተረክ ሰባት

ወንበር ጅክሪም በአንድ ጊዜ ወንበር፣ ወረዳና ጭቃ የሚባል ሦስት ስልጣን ይዘው ነበር አሉ፡፡ ሰው ስለታጣ ይሁን እንጃ አንዴ ጐንደር ይሄዱና ከጠቅላይ ሹሙ ፈረሶች ወደ ጭልጋ አምጥተው እስከ መስከረም እንዲጠብቁ ይታዘዛሉ፡፡ እሳቸውም፣ "ሀገራችን ፈረስ አይሆንም የቆላ ዝንብ ነድፎ ይገድለዋል፡፡" ቢሉ፣ "ቢነድፈውም የሞተውን እየጣሉ ያለውን ይጠብቁ፡፡" ብለው አርባ ፈረስ ይሠጧቸውና ይዘው ወደ ጭልጋ ይመጣሉ፡፡ እንግዲህ አርባ ፈረስ መዋያው ችግር ነው ለመጠበቅም ይከብዳል፡፡ እንጨት አምባ የሚባል ተራራ አለ እዚያ ገደል ውስጥ ደልድለው አገቧቸው፡፡ ከዚያ ሀገሬው፣ "ሳር የምናጭድበትን ተራራ የባዕድ ፈረስ አምጥተው እያጋጡ እኛ ከብቶቻችንን ምን ልናበላ ነው? ቤታችንንስ በምን ልንከድን ነው?" ብለው ወደሳቸው ደጃፍ ይገፋሉ፡፡ ግን መጠበቁ ስላቃታቸው አንዴ ያንዱን ሰብል ሌላ ጊዜ የሌላውን ዝር ሲበሉ ሀገሬው ተመካከረና አንድ ቀን ሌሊት የፈረሶቹን ምላስ ምላሳቸውን ቆረጧቸው፡፡ ከብት ምላስ ከሌለው ሳር መጋጥ አይችልም፣

መብላትም አይሆንለትምና ፈረሶቹ እንዳለ አለቁ፡፡ ከዚያ ወንበሩ ወደ ጐንደር ሄደው፣ "እኔ ቀድሞውንም ነግሬያችሁ ነበር፡፡ ሀገሩ ለፈረስ አይመችም፤ ይሞታሉ ብያችሁ ነበር፡፡ እንዳልኩትም ፈረሶቹ ሁሉ ሞቱ፡፡" ብለው ተናገሩ፡፡ ከዚያ ሹሞቹም፣ "ከሞቱ ምን ይደረጋል?" ብለው እንደተቀመጡ አሽሟጣጭ፣ "ምን የቆላ ዝንብ ይገድላቸዋል! የደሃ ሰብል ውስጥ ገብተው ሰዉ ስለተመረረ ምላስ ምላሳቸውን ቆርጦ ነው የገደላቸው" ብለው ተናገሩ፡፡ "ለካስ እንዲህ አርገው አስገድለው ነው? በሉ አሁን አርባውን ፈረስ ሰማኒያ አድርገው ይክፈሉ!" ተብሎ ተወሰነባቸው፡፡ ከዚያ መጥተው ሲጨነቁ በኋላ፣ ሀገሬ ቀልቱኝ ብለው ሰራባን፣ ዋልድባን፣ ይዘው እስከ ጮንጮቅ ሄደው ተቀልተው ጭልጋ እምቢ ሲል ፈረስ አምጥቶ አስበልቶብናል በሚል ነጣላውንም የሰጠ አለ፤ ሁሉም ያለውን አውጥቶ ገንዘቡን በእጥፍ አስገቡ፡፡ ነቀላ የትም ተዝካር ቢመጣ ለወንበር ነቀላ ሳይገባ አይሆንም፡፡ ከናራም፣ ጭልጋም፣ ፈፈሪ ኪዳነምህረትም፣ ጮንጮቅም፣ ሳቤራም፣ ሁሉም ከፍሎ ሲከተል ሲከተል እዚህ ደረሰ፤ "እንዴት እኛ ተቸገርን፣ አንድ ፍርድ ይስጡን!" ሲሉ፣ "ምን ችግር አለ? ምን የተቀየማችሁት ነገር አለ?" "እኛማ አዎ የቅማንት ተዝካር ይሄ ሲባል ስጋው ሲሰነብት ለምን ስጋው ሠነበተ ይባላል እንዳይገባ ይመሻል ሀገሩ ሩቅ ነው እንዴት አድርገን ነው እዚህ ላይ አንድ ፍትህ ይስጡን" ሲሉ፣ "አይ የናራን ነቀላ ነቅያለሁ በቃ እኔ ትቻለሁ ግን ኋላ የሚተካ ወንበር እንዳይወቅሰኝ እንዲህ አድርገን ችግራቸውን ወጥተው ነቅሎ ሞተ እንዳይለኝ የሚተካው ልጅ እንዳይሠድበኝ በአመት እየዞረ እየመረቀ የመረቀውን እንድትሠጡ እኔ ግን ነቅያለሁ ብለው ነቅለው ሞቱ ይባባል፡፡

## ተረክ ስምንት

አንድ ጊዜ አንዲት ሴት፣ ልጇ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ይሞትባታል፡፡ አስከሬኑም ሳይገኝ ይቀራል፡፡ ሴትዬይቱም በሃዘን ተቆራምዳ ስትኖር አንድ ቀን ሰዎች አሣ ሲያጠምዱ አንድ በጣም ትልቅ አሳ ይይዛሉ፡፡ የአሳውን ሬብ ለማውጣት ሆዱን ሲሰነጥቁትም የሟቹ ቀለበት ይገኛል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለህገልቦና እምነት ተከታይ አሳ እርም ሆነ፡፡

## ተረክ ዘጠኝ

በድሮ ጊዜ ሦስት ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ አንደኛው ወንድማቸው ሰው ገድሎ፣ "በሉ እንሂድ እንጥፋ" ይሉና ጠፍተው ከገለባ መሃል ይደበቃሉ፡፡ ከዚያ የሟች ወንድም በፈረስ እየጋለበ ይከተላቸው ነበር፡፡ ከዚያ አንደኛው የገዳይ ወንድም ፈረሱ በስሩ ሲጋልብ እተደበቀበት ገለባ ውስጥ እንዳለ፣ "አንተ እንዳትረግጠኝ፡፡" ይላል፡፡ ከዚያ የሟች ወንድም፣ "እኸ እዚህ

ነው ያለህ?" ይልና በያዘው ጦር ወግቶ ይገድለዋል፡፡ ከዚያ ሁለተኛው፣ "አይ ዝም ቢል እኮ አይገለውም ነበር፡፡" ይላል፤ ከዚያም እሱም ይገደላል፡፡ ከዚያ ሦስተኛው፣ "በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ" ሲል እሱንም ገደለው፡፡ ከዚያ ሦስቱንም ገድሎ ተመለሰ ይባላል፡፡

## ተረክ አስር

ሦስት መንድማማቾች አባታቸው ሲሞት ለአንደኛው አንድ ሳጥን ወርቅ፣ ለሌላኛው አንድ ሳጥን እበት፣ ለሦስተኛው አንድ ሳጥን አፈር ቆልፈው ጉረቤት ያስቀምጡና፣ "አደራ ይህን ሳጥን፡ ይሄን ለከሌ፣ ይሄን ለከሌ፣ ለአቅመ አዳም ሲደርሱ ይስጡልኝ፡፡" ብለው ይናዘዛሉ፡፡ ልጆቹ ሲያድጉ የታዘዘው ጉረቤት እንደታዘዘው ይሠጣቸዋል፡፡ ከዚያ እበትና አፈር ይደረሳቸው፣ "እንዴት እንዲህ ይሆናል?" ይሉና አልስማማ ይላሉ፡፡ ከዚያ አዋቂ ፈላስፋ ጋር እንሂድ ይባባሉና መንገድ ይጀምራሉ፡፡ ከዚያ መንገድ ላይ አንድ እንዳይበላ የተለጉመ ፈረስ ያያሉ ነገር ግን ያ ፈረስ የተለጉመው በሳር መካከል ሳለ ነው፡፡ እልፍ ሲሉ ደግሞ አንድ በቅሎ በባዶ ሜዳ ላይ ያለመጠን ጠግቦ ያገኙታል፡፡ አሁንም እልፍ ሲሉ ነብሡጡር ውሻ ቁጢሎቿ በሆዷ እየተገላበጡ እሷ ተኝታለች፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ከፈላስፋው ቤት ይደርሳሉ፡፡ ፈላስፋዎቹ ሦስት ነበሩ፡፡ መጀመሪያ ያገኙት በእድሜ የመጨረሻውን ትንሹ ነበር፡፡ ግን በጣም አርጅቶ ነበር፤ መናገርም አይችልም፡፡ የመካከለኛው ጋር ሲሄዱ ትንሽ ሻል ይላል፡፡ በኋላ ታላቅየው ጋር ሄዱ፡፡ እሱም ከሁለቱ ወንድሞቹ በእድሜ ቢበልጥም ነገር ግን ከሁለቱ የተሻለ ወጣትነት ነበረው፡፡ ከዚያ ሁሉንም ነገር ነገሩት፡፡ አባታቸው ትቶላቸው ከሄደው ነገር አንስቶ ሲመጡ የጋጠማቸውን ሁሉ ለዚያ ፈላስፋ ነገሩት፡፡ "እየው አሁን እዚህ መጀመሪያ ያገኛችሁት የሁላችንም ታናሽ ነው ቀጥሎ ያገኛችሁትም የኔ ታናሽ ነው፡፡ እኔ ግን በእድሜ የሁለቱም ታላቅ ነኝ፤ ነገር ግን እነሱ አርጅተዋል፤ እኔ ደህና ነኝ፡፡ ምክንያቱም ሚስቴ ትመቸኛለች፤ ብዙም ችግር የለብኝም ቤቴም ሙሉ ነው፡፡ የኔ ታናሽ ቤተሰቡም ችግሩም በመካከለኛ ስለሆነ ከመጨረሻው ወንድሜ ይሻላል፡፡ የመጨረሻው ወንድሜ ግን ነዝናዛ ሚስት ስላለቸውና ቤቱ ስለማይመቸው ነው፡፡ የኔ ሚስት ግን ተኝቼ እንኳን ፀጉሯን ተንተርሼው ከሆነ እንዳልነቃና እንቅልፌ እንዳይቋረጥ ፀጉሯን ቆርጣ ነው የምትነሳው፡፡ ከመጀመሪያው ስትመጡ ተርቦ ያገኛችሁት ፈረስ በ8ኛው ሺ ባላባቶች የሚቸጋገሩበትን ጊዜ የሚያሳይ ነው፤ ጠግቦ ያገኛችሁት በቅሎ ደግሞ በህብረተሰቡ የገሌ ልጅ የማይባል ተራ ምናምንቴ የተሻለ በልቶ የሚያድርበት ጊዜ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ያቺ ውሻ ደግሞ ልጆቹ እንዲያ በሆዷ

ሲፈነጥዙ ያያችሁት በ8ኛው ሺ የሚፈጠሩ ልጆች፣ "አባቴ ቆይ እናቴም ቆይ" እያሉ እነሱ እኛ እናውቃላን እያሉ እኛ እንናገር የሚሉት ናቸው፡፡ "አባታችሁ ብስል ሰው ነው፡፡ ላንተ አፈር የሠጠህ ሙያህ በግብርና ነውና አርሠህ ኑር ሲልህ ነው፡፡ ላንተ እበት የተወልህ ክፍልህ ከብት እርባታ ነው ሲልህ ነው፡፡ ላንተም ወርቅ የተወልህ ክፍልህ ንግድ እንደሆነ እየነገረህ ነው፡፡" ብሎ አሠናበታቸው ይባላል፡፡

## ተረክ አስራ አንድ

አይደረኪና ሚስታቸው አንዴ ሲጓዙ ይውሉና ሲመሽ አንድ ዋሻ ውስጥ ለማደር ይገባሉ፡፡ ዋሻው ውስጥ ወልዳ ተኝታ የነበረች ሰስ ኖራለች፡፡ እነሱን ስታይ ልጇን ትታ ደንብራ ወጥታ ሳትመ ለስ ት ቀራለች፡፡ በማግስቱም ብትታይ የለችም፡፡ ከዚ ያ ግ ልገሏን ሰስ የአይደረኪ ባለቤት ጡታቸውን እያጠቡ ለቅጠል እስክትበቃ አሳደጓት፡፡ በዚህም "የኔ ፍጥረት የሆናችሁ ይህች ሰስ ጡቴን አጥብቼ ያሳደኳት ልጄ ናትና እንዳትገድሏት፣ እንዳትበሏትም፡፡" ብለው አዘዙ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰስ እንበላም፡፡

## ተረክ አስራ ሁለት

ሁለት ባልና ሚስቶች ሲኖሩ አንድ ወቅት ክፉ ቀን ይገባና የሚቀምሱት ያጣሉ፡፡ ከዚያ በጣም ርቧቸው እሱም ከምድጃው ዳር፣ እሷም ከምድጃው ዳር ተቀምጣለት፡፡ "አንቺ" ይላታል፡፡ "እባክሽ እሱን ጅልሽን ክደኘው"ይላታል፡፡ "እሺ" ትልና ቀሚሷን ክድን! እሷም፣ "አንተም እሱን ጅልህን ክደን!" ስትለው፣ "ወጥቼ ቆርጬ ጥዬው ልምጣ?" ሲላት፣ "እሺ ቆርጠህ ጥለኸው ና ምን ያደርግልናል?" ትለዋለች፡፡ ከዚያ ወጥቶ፣ "ቆርጬው መጣሁ" ይላታል ውሸቱን፡፡ ከዚያ ያ ቀን ያልፍና ሙሬ የሚባል ጤፍ ደርሶ ሙቅ እያፈሉ ሲጠጡ፣ "አንቱዬ" ትለዋለች፡፡ "አቤት" "ያ ነገር ጐማዳው እንኳን የለንም?" ትለዋለች፡፡ "የለ ከስሩ ነው ጐምጄ የጣልኩት፡፡" ይላታል፡፡ "አይገዛም?" "ይገዛል" እንግዲያስ ያለ የሌለውን ንብረት ይሸጡና ሄደው ገዝተው ያምጡ!" ትለዋለች፡፡ ከዚያ፣ "እሺ" ብሎ ሲሄድ ከአፋፍ ላይ ሚዜውን ያገኘውና ይነግረዋል፡፡ ከዚያ ሚዜው፣ "እስኪ ምን ያህል ላምጣ በላት" ይለዋል፡፡ "አንቺ አንቺ..." አላት፡፡ "አቤት" "ያን ያልሸኝን ምን ያህል ላምጣ? እጇን እያሳየች፣ "ይህን ያህል" (እሳቸውም/ተራኪው/ ክዳቸውን ሙሉ እያሳዩኝ) አለች ይባላል፡፡

## ተረክ አስራ ሦስት

አንዱ ባሏ እያረሰ እሷ ጉልጓሎውን እያቋረጠች ቀድማ ወደቤት እየሄደች ገንፎ እያገነፋች ትበላለች፡፡ ከዚያ ይህን ጉዳይ ለሚዜው ሲነግረው፣ "እሷ እየሄደች ይምትበላው ነገር ስለሚኖር ከሄደች በኋላ ትንሽ ቆየት ብለህ ተከትለሃት ሂድ!" ይለዋል፡፡ ከዚያ ሴትዬይቱ እንደ ሄደች ትንሽ ቆይቶ ሮጥ ብሎ ይሄድና እስክታገነፋ ከጓሮ ይደበቃል፡፡ ከዚያ አገንፍታ ጭርስ ስታደርግ፣ "ደህናዋላችሁ?" ብሎ ጥልቅ ሲል ይዛ ገንፎውን ከማጀት ትደብቀዋለች፡፡ ከዚያ፣ "ምን ሆነህ ነው አቋርጠኸው የመጣህ?" ትለዋለች፡፡ "አይ ጨርሻዋለሁ ትንሽ ናች የቀረችኝ፡፡" ሲላት፣ "ምን ያህል ይሆናል?" ስትለው፣ "ከዚህ እንደገንፎው ቀርቶኛል፡፡" ይልና ገንፎውን እንዳየው ያመላክታታል፡፡ ከዚያ ገንፎውን አቅርባ አብረው በሉ ይባላል፡፡

## ተረክ አስራ አራት

አማሮች እየሱስ ክርስቶስ እንደሚሉት ሁሉ የኛ አባት ደግሞ አይደረኪ ነው፡፡ እነሱ "አምስት ሺ አምስት መቶ አመት ከገዛ በኋላ መልሶ ተፀንሶ ተወለደ" ነው የሚሉ፡፡ እኛ ግን ወለደ ነው የምንል፡፡ እነሱ "ከሠማየ ሠማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ወልዶ" ይላሉ እኛ ግን ከሠማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ሴት ወልዶ ነው የምንል፡፡ የአይደረኪ አወላለድም እንዲህ ነው ደባ አንዷትን ድንግል ሴት በመብረቅ ነጐድጓድ ብልጭ አድርጐባት ፀነሠች፡፡ እነሱም (አማሮች) "ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተፀነሠ" ይላሉ፡፡ ወዲህ ደግሞ "እሳት ነው" ይላሉ፡፡ እሳት ዘጠኝ ወር እንዴት በማህፀን ይተኛል? የኛ በተፀነሰ በሰባተኛው ቀን ሴ ቲቱ ልትችለ ው አልቻለችምና ወ ደቀች፡፡ ያኔ የከረን ታ፣ "ፍጡርህ እንዴት ያለ ነው ሴቲቱ እኮ ልትቀደድ ሆነ፤ አልቻለችውም እንዴት ይሁን?" ቢለው፣ "አይ አውርጂው በላት አውርዳው ትረፍ" አለውና በሰባተኛው ቀን ተወለደ፡፡ እንደተወለደም ጥጋቡ አልቻል አለ፡፡ እጅግ ሀይለኛም ስለነበረ ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ ለአርባ ቀናት ታሠረ፡፡ በአርባኛው ቀንም ተፈታ፡፡ ከዚያም በወጣትነቱ በጨዋታም ይሁን በሌላ ሌላ ሰው ሊተካከለው አልቻለም፡፡

አንድ ቀን ጋላ (የገና ጨዋታ) ሲጫወት ሩሯን (ኳሷን) የሚለጋትም የሚቀልባትም እሱ ሆነ፡፡ እንደው ለሌላው ሰው አላቀምስ አለ፡፡ ከዚያ አንዱ ሀይለኛ፣

"አባትክን ማን አውቆ፣

ጐርፍ ያመጣህ ዝቆ፤

አባትክን ንገረኝ፣

ለስድብ ችገረኝ" ይላል፡፡

ምክንያቱም በመብረቅ ነገር የተፈጠረ ልጅ ነው፤ አባቱ አይታወቅም፡፡ እሱም ዝም ይላል፡፡ በኋላ ግን በጣም እየደጋገመ ሲሰድበው፣ "ምነው ትሠድበኛለህ አትስደበኝ እንጂ" ይላል፡፡ ከዚያ ያ ጎይለኛ፣ "ምን ሠደብኩህ እስኪ ንገረኝ የማን ልጅ ነህ? እኔ የከሌ ልጅ ነኝ፡፡ እሱም የከሌ ልጅ ነው፡፡ እስኪ ንገረኝ ያንተ አባት ማን ነው?" ይለዋል፡፡ በዚህም ይጣላሉ፡፡ ጎይ ለኛውም፣ "እንግዲህ ልመታህ ነኝ፡፡" ይላል፡፡ ከዚያ አይደረኪ፣ "በል እንግዲህ እንግጠም ያጠቃ ያጥቃ፡፡ አንተም ብትገለኝ እኔም ብገልህ ደም እንዳይነሳ ፀቡ በእኔና ባንተ ብቻ ይቅር" አለው፡፡ ያም ተስማማና ግይድ ገቡ፡፡ ከዚያም አይደረኪ አነሳና በብብራ አሳር ቢመታው ሰውነቱን ቀዶ ወደ ምድር ሀያ ክንድ ገባ፡፡ ከዚያ ጎይለኛው ወዲያው ሞተ፡፡ ከዚያ የሚች ወንድሞች አኮረፉና አይደረኪን አገለሉት፡፡

አንድ ቀን የሚች ወንድም ሚስት ያጭና ሴቷን ሊያመጡ የመንደሩ ጐረምሶች ሁሉ ወደ ሴቲቱ መንደር ሂደው ኖሯል፡፡ አይደረኪም፣ "ዛሬ የዚህ መንደር ሰው ሁሉ ምን ገባ መንደሩ ጭልል ብሏልሳ?" ብሎ ሲጠይቅ፤ "ኧረ አንተን ደመኛ አድርገውህ ነው እንጂ ያ የገደልከው ወንድም ዛሬ ሊዳር ነው የመንደሩ ሰው ሁሉ እሱን አጅቦ ሴቲቱን ሊያመጣ ሄዷል፡፡" ይሉታል፡፡ ከዚያ ያው ይታየዋል ይገሰግስና ሰተት ብሎ አግቢዋ ቤት ይሄዳል፡፡ ሙሽራይቱም ገና ከጐጆ ወደ ሙሽራው ጋር አልወጣችም ነበር፡፡ እዚያ እንደደረሰም ወዳለችበት ይገባና ጥላውን ጣል ያደርግባታል ከዚያ ትፈቅደዋለች፡፡

ከዚያ አማቺቱ ላይም ጥላውን ጣል ያደርግባታል፡፡ እሷም ለልጇ ትፈቅደዋለች፡፡ ከዚያ ይዟት ሊሄድ ሲል ቤተሰቦቿን እንዲህ ብሎ ሙግት ያስተምራቸዋል፡፡ "በሉ አሁን ሚስታችንን ሲሏችሁ 'እሷ ጐበዝ አይታ ሄዳለች፡፡ ያባት እዳ ለልጅ እንጂ የልጅ እዳ ላባትና እናት አይሆንም፤ እኛ አንጠየቅም፡፡ ሴት ወለድን እሷም ቆነጀችና ጐበዝ ወደዳት በዚህም አግድማ ሄደች፡፡ እኛን ምን አድርጉ ትሉናላችሁ?!' በሉ" ብሎ "ይገልድጉ ጉሽ" ይላል በቅማንትኛ "አንተ ግድግዳ ልቀቅ" ሲል የጐጆው ግድግዳ ይለቅና በዚያ ሾልኮ

ይዟት ይሄዳል፡፡ ከዚያ ተነስተው፣ "ሚስታችንን ስጡን" ቢሉ፣ "ይህች ሴት የለችም፡፡" ይላሉ፡፡ "ከምን ሄደች ከምን ሄደች?" ይባባላሉ፡፡ ከዚያ ቤተሰቦቿም እንዳስተማራቸው ይመልሳሉ፡፡ ምን ያድርጉ? እነዚያም "ሰርግ ብዬ" እያሉ ከቆዩበት ቆይተው ቢመጡ አንዱ አሽሟጣጭ፣ "አይጐበዝ! እሱ ብቻውን ተወልዶ በቀረ! እሱ ትናንት ይዟት የገባውን ሰርግ ብዬ እያልክ ስትናፍፍ" ይላል፡፡ ይህን ሲሰሙ አይደረኪ ጋር ሰተት ብለው ይመጡና፣ "ምን ብለህ ሚስታችንን ይዘሀት መጣህ?" ቢሉት፣ "እኔ ሚስት ታጨ አታጨ አላውቅም የናንተ ሚስት ከሆነችማ ውሰዷት" ይላል፡፡ ቅማንቶች ግንባራቸውን ይቀደዳሉ የሚባልበት ምክንያት ያኔ "ኪዱስ" ብሎ ግንባሯን ቀዶ ስለባረካት ነው ይባላል፡፡ ከዚያ ገብተው ሲያይዋት ባርኳታል፤ "አይይ... ባርኳት የለ! እንግዲህ ምን እናደርጋታለን?!" ይሉና ይመለሳሉ፡፡ ከዚያ፣ "ይሄ ሰውዬ ከዚህ ቀደም ወንድማችንን ገደለ አሁን ደግሞ ሚስታችንን ቀማ ምን ይሻለናል?" ብለው ተመካከሩና፣ "ዘመቻ ይሁን ብለን እናሳውጅና እዚያ ዘመቻ ላይ እሱም ስለሚመጣ እንገድለው፡፡" ብለው ተማከሩና ለዳኛውም ነግረው ዘመቻ ታዘዘ፡፡ በዘመቻው ላይም ማንም ሰው እንዳይቀር ታወጀ፡፡ እሱ የዘመቻው ለት እቤቱ ተቀመጠ፡፡

ዘመቻው ለምን እንደሆነ አውቋልና፡፡ ከዚያ እናቱ፣ "ዘመቻ ተብሏል ውጣ እንጂ" ብላዋለች፤ "እናቱ ትዝመት አባቱ" ይላል፡፡ "ተው እንጂ ልጄ ወይ ወንድም የለህ፣ እህት የለህ፤ ወገን የለህ፣ ጓደኛ የለህ፤ ብቻህን የተፈጠርክ ሰው ተው እንጂ" አለችው፡፡ "እኔ ሦስት ጊዜ ኪዱስ ብል፣ ሰባት ጊዜ ረግጩ የምወጣው ርካብ ያለው ፈረስ ተደጃፌ መጥቶ ይቆማል፤ ከጭንጫው ላይ ውሃ የማፈልቅ፣ ከባህሩ ላይ እሳት የማነድ ወንድ እኮ ነኝ፡፡ ሦስት ጊዜ ኪዱስ ብል ሦስት ጀንፎ ያለው ጦር ከጄ መጥቶ ይገባል፡፡ እና ከእኔ ጋር ነው እነሱ እኩል የሚሆኑት?!" ብሎ ተበሳጭቶ ሲነሳ እናቱ፣ "ኧረ ተው ልጄ ተው እባክህ" ትለዋለች፡፡ ንጋት ይነሳና፣ "ኪዱስ... ኪዱስ... ኪዱስ..." ብሎ በሚናገርበት ጊዜ ሰባት ርካብ ረግጦ የሚወጣው ፈረስ ከደጃፉ መጥቶ ቀጥ! ሦስት ጀንፎ ያለው ጦር ከጁ መጥቶ ጥልቅ! ያኔ ተበሳጭቶ ሲነሳ የከረንታ ፈጣሪውን፣ "ልጅህን አስቁመው እንጂ ሊጨርሳቸው እኮ ነው፡፡ ተነሳኮ ቆረጠ ከፈረሱ ላይ እየወጣ ነው ታዲያ ማን ይተርፊዋል ምድርን እኮ ወና ሊያደርጋት ነው፡፡" ሲለው ደባም፣ "ሂድና ና ብለህ ጥቀሰው፡፡" ይለዋል፡፡ ከዚያም ይጠራዋል፡፡

ሲጠራውም አራቱን ርካብ ጨርሶ አምስተኛውን ረግጦ ነበር፡፡ ከዚያ ወደ ሰማይ ያረጋሉ፡፡ ደባ ጋር ሲደርስም፣ "እንዴት ነው?" ብሎ ጠየቀው፡፡ "አይ አባቴ እኔ ለመኖር

አልተመቸኝም እየተጣላሁ፣ እየተደባደብኩ፣ እየተዳማሁ ነው ያለሁት፡፡" አለው፡፡ "አይ አንተም አታጐልብት በጉልበት እኮ አይሆንም ስራ አይሠራም በጉልበት፡፡ የምትፈልግ ከሆነ ወይ ግዛትህን ለብቻ በባህር ከልዬ ልስጥህ" አለው፡፡ "መስዬ ተመሳስዬ ልኑር፡፡" አለ፡፡ "አይ ካልክማ ከዚህ በኋላ እንዲህ ብለህ በኋይልህ ልትጠቀም እንዳትሞክር ጦርም በጅህ እንዳይገባ፡፡ በተበደልክ ጊዜ ፊትህን ወደ ፀሃይ መውጫ አድርገህ 'ኪዱስ...' ብለህ ንገረኝ፡፡ እኔ ያኔ ጨቅላ እርር ብሎ ሲያለቅስ እናቱ 'ልጄ ወደቀን' ብላ እንደምትደነግጠው ደንግጬ እሠማሀለሁ፤ እረኛ ከብቶቹን እየጠበቀ ቢጣራ፣ አባቱ 'ከብት ወደቀ፣ ከብት ተቀጋ' ብሎ ደንግጦ እንደሚሠማው እሠማሀለሁ፤ ቃሌ ይሁን፡፡ አንተ ግን መደብደብ መቸንከር ነው እንጂ ያለብህ በሃይልህ አይሁን አግጄሀለሁ" ብሎ መልሶ ወደ ምድር ሰደደው፡፡

ከዚያ ወደ ምድር መጥቶ እየተሠደበ፣ እየተደበደበ፣ እየታሠረ፣ እየተፈታ ኖረ፡፡ ቦር የሚባል አለ በዚህ በደብረሳሙኤል ወዲያ ሆኖ ኳሪቾ ቢል ቋራ አሉት፡፡ ኳሪቾ ማለት በቅማንተኒ ፀሃይ ሃገር ማለት ነው፡፡ እዚያ ገብስ ዘርተው ነበርና ልጁን፣ "ሂድና ምርቱን ሰብስብ፡፡" ቢለው፣ "ይህን ሁሉ በረሃ እንዴት ብዬ ነው?" ብሎ መለሠለት፡፡ አይደረኪ ደግሞ ቃል ተገብቶለት ሲመጣ የተነገረው ምልክት ነበር፤ "የወለድከው ልጅህ መልስ በሠጠህ ጊዜ አንተ ወደኔ ትመጣለህ፡፡" ብሎት ነበርና ሊጠራ እንደሆነ አወቀ፡፡ ከዚያም ደብድበው ገደሉትና ወደ መንደራቸው ተመለሱ፡፡ መቼም ሴት ነገረኛ ነውሐ፤ "ደብድበን ገደልነው" ሲሏቸው፣ "አይ እንደሱ ያለውን ጀግናማ አትችሉትም ከሆነስ ችብችቦውን (ክንድና ክንዱን) ቆርጣችሁ ባመጣችሁት ነበር" ሲላቸው እንዳሏቸው ለማድረግ ቢሄዱ አይደረኪ የለም አርጓል፡፡

## ተረክ አስራ አምስት

አንድ ሌባ ካንድ ሀብታም ቤት ሲገባ የሀብታምየው ኮት በሙሉ ከግድግዳ ላይ ተሠቅሏል፡፡ ከዚያ ያን ኮት ሁሉ ሲፈትሽ ሲፈትሽ ይቆይና የመጨረሻው ኮት ጋር ሲደርስ ሀብታሙ፣ "አይ አያ ሌቦ! እኔ በቀን ስፈልግ ውዬ ያጣሁትን ገንዘብ አንተ በጨለማ ፈልገህ ልታገኝ ነው? አትድከም፡፡" አለው ይባላል፡፡

## ተረክ አስራ ስድስት

ላይ አርማጮሆ ቦለቃ የሚባል ሀገር ቄስ ሸዋይ የሚባሉ የቅማንት ቄስ ነበሩ፡፡ ፈጣሪን በጣም የሚያምኑና የሚለምኑ ነበሩ፡፡ አውሬ ቢመጣ ምን ቢመጣ ከተቀመጡበት ወይ ከቆሙበት ንቅንቅ አይሉም፡፡ "ፈጣሪ አዞ ከሆነ ያሻውን ያድርግ በኔ መሸሽ አልድንም፡፡" የሚሉ ነበሩ፡፡ አንድ ቀን አንድ ነብር የግራጫ እሾህ በጥፌ ሲማታ እሾሁ በሡንጣው (በመዳፉ) ይገባበትና ቢል ቢል አልወጣልህ ይለዋል፡፡ በጥርሱም ቢግጥ እምቢ ይለዋል፡፡ ከዚያ በጣም አብጦበት መላወስም ተሳነው፡፡ ከዚያም እንደተጨነቀ ቄስ ሸዋይ ካሉበት መጣ፡፡ እሳቸውም ከአፋፍ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ነበር፡፡ መቼም የሰው ግንባር ተፈሪ ነው ፊቱን ዞሮ ቁጭ አለ፡፡ ከዚያም አንዴ ሲዞር ወደሳቸው ይመጣ ዘንድ ጠቀሱት፡፡ (ተራኪው እጃቸውን ና በሚል ምልክት ያወራጫሉ፡፡) ከዚያም ነብሩ መጣና እጁን ጭናቸው ላይ አስቀመጠ፡፡ እጁን ቢያዩት ግምኛ ተጐድቷል፡፡ በጥርሱም በምኑም አገኝ አገኝ ሲል ጫጭሮታል፡፡ ከዚያ ባንድ ገፅ መቀንጠጫ ባንድ ገፅ ደግሞ ወረንጦ የምትባል እቃ አለች እሷን ሚስታቸውን አምጭልኝ ብለው ሰርስረው በመቆንጠጫዋ ስበው አውጥተው ያበጠውን አፍረጥርጠው ቅቤ ቀብተው ሂድ ሲሉት ሦስት ጊዜ ሠግዶ "ነውር" አለ ይባላል፡፡ በሂደ በሠባተኛ ቀኑም አንድ አውራ ድኩላ መትቶ ይዞ መጣ አሉ፡፡ ከዚያን በኋላም በተደጋጋሚ እያመጣ ሦስት አመት ገበረ ይባላል፡፡

## ተረክ አስራ ሰባት

አንበሳና ጦጣ እሷም እሱን ስታየው ሮጣ ዛፍ ላይ ላትወጣና ላትሸሸው፣ እሱም ላይበላት ይማማላሉ፡፡ ከዚያ ሲሄዱ... ሲሄዱ... አንበሳ ሊበላት ያስባል፡፡ ከዚያ፣ "እንጠራራኝ" ይላታል እየተንጠራራ (ተራኪውም እየተንጠራሩ) ከዚያ እሷም፣ "እኔንም ሰው ጠራኝ" ብላ ዘላ ዛፍ ላይ ወጣች ይባላል፡፡

## ተረክ አስራ ስምንት

ሰዎች ባሪያ ይገዛሉ፡፡ ለባሪያቸውም ስም የሚያወጡት አሳዳሪዎቹ ናቸው፤ የሚያወጡትም በምሳሌ ነው፡፡ ከዚያ አንዷቱን ባሪያ የቀጠሩ አሣዳሪ፣ "አድራለሁ ቁሜ" ብለው ይሠይሟትና፣ "አድራለሁ ቁሜ" ተብላ ስትጠራ፣ "ስለምን የጌታዬን እድሜ" ብላ አቤት እንድትል ትደረጋለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ብዙ ሲኖሩ ጌትየው ይሞታል፡፡ ከዚያ ሚስቲቱ፣

"አድራለሁ ቁሜ" አለቻት፤ ባሪያዋም ንቃት ኖሮ፣ "ተገትረሽ ቅሪ ለራስሽ ብለሽ" አለቻት ይባላል።

## ተረክ አስራ ዘጠኝ

አንዴ አንድ የጐንደር ንጉስ የቅማንትን ህዝብ ለማጥፋት ያሴራል። በዚህም እንደነገ ዘመቻው እንዲሆን ይወሰናል። ወታደሮቹ በቅማንት ህዝብ ላይ ከመዝመታቸው በፊት ይበረቱ ዘንድ የሚመገቡት ምግብና የሚጠጡት ጠላና ጠጅ ሲሰናዳላቸው ታደረ። ከዚያም ጠዋት የተዘጋጀውን በልተውና ጠጥተው ለመሄድ ሞሰቡን እንክፈትህ ቢሉት አልከፈትም አለ። ወጡም፣ ጠላውም፣ ጠጁም... ሁሉም አልከፈትም አለ። በኋላ፣ "አማሮች ይፀልዩ" ተባለና መጡ። ሲፀልዩ ቢውሉ የተከደነው ሁሉ ሊከፈት ቀርቶ ንቅንቅም አላለ። "እስቲ እስላሞች ይምጡ" ተባለ። እነሱም በምነታቸው ቢፀልዩ ሊከፈት አልቻለም። "እስኪ እነዚህ ቅማንቶች የተባሉት ይመጡና ይሞክሩት" ተባለ። እንደነሱ ሲፀልዩ አልዋሉም። ያው እንደ አባታችን ኪዱስ .. ኪዱስ.. ኪዱስ.. ብቻ አሉ። ምርጉ ሁሉ ተከፈተ። ነገር ግን መጠጡ ደም ምግቡ ትል ሆኖ ተገኘ። ከዚያም፣ "ምን የመከራችሁት ነገር ነበር? ይህንንስ ምግብ ለምን አይነት ክፋት አሰባችሁት ነበር? እውነቱን ንገሩን ጌታ የሚወደው እውነትን ነው።" አሉ። ከዚያም ለምን እንዳዘጋጁት ይነግሯቸዋል። ቅማንቶችም፣ "እኛ ምን በደልናችሁ ምንስ አጠፋን የፈጣሪ ተገዢ ነን፤ የፈጣሪ ለማኝ ነን፤ የፈጣሪ ፀሏች ነን ምን አደረግን እኛን የምታጠፉን?" ሲሉ ያ መንግስት ተፀፅቶ ተዋቸው አሉ።

## ተረክ ሃያ

በቴዎድሮስ ግዛት ጊዜ ቤተክርስቲያን ውስጥ አለመስማማት ነበር። ቴዎድሮስ የማይስማሙበትን ምክንያት ሲፈትሽ ብዛታቸው ሆኖ አገኘው። ባንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ቄሶች፣ ዲያቆኖች፣ ደብተሮችና መርጌታዎች ነበሩ። ቴዎድሮስም በጣም ይናደድና፣ "ከዚህ በኋላ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ያለበት ቄስና ዲያቆን አምስት ብቻ ነው እንጂ ቤተክርስቲያን ሠፍሮ የደሃ እህል መብላት የለም። እናንተም ብትሆኑ ከቅዳሴ በኋላ ስራ ስሩ።" ብሎ ያስጠነቅቃል። በኋላ በሌላ ቀን ካንዱ ቤተክርስቲያን ቢሄድ ከተባለው ቁጥር ውጪ ሃያ ዘጠኝ ቄስና ዲያቆኖች ተከማችተው አገኘ። ከዚያ አንዱን አገልጋዩን፣ "በል እነዚህን ባጠቃላይ አቃጥልልኝ።" ቢለው

አገሊጋዩ፣ "ስንቱን ላቃጥላቸው?" አለ፡፡ ቴዎድሮስም፣ "ሰላሳውንም አቃጥላቸው አለው፡፡" "ጌታዬ ሃያ ዘጠኝ ናቸው እኮ!" ቢለው፣ "ሰላሳኛው አንተ ነህ" አለው ይባላል፡፡

## ተረክ ሃያ አንድ

የድሮ ልጅ እንዳሁን ራሱ በራሱ አይጋባም፡፡ ቤተሰብ ተጫጭቶ ነው፡፡ ለዚያውም አማጩ ሲሄድ ልጅቱ ሳታውቅ ቁጭ ብላ ሥራ ትሠራለች፤ ቡና ታፈላለች፡፡ ከዚያ አማጩ ዝም ብሎ ይመለከታታል፡፡ ከዚያ ሴትነቷን (ሙያዋን) ይፈትሻል፡፡ አንዱ አንዲህ አማጩ ይሄድና ቡና አፍልታ የቡና ቁርስ ቆሎ እየቆላች ዝም ብላ ትችማለች (ትቅማለች) በኋላም ውሃ ትጠጣለች፡፡ ከዚያ አማጩ፣ "እየውልሽ እምዬ" "አቤት" "እናትሽን ስትያቸው ቆሎ ቆርጥሞ ውሃ ችልስ የተባባልነው አለፍርስ ብለሽ ንገሪያቸው ከንግዲህ አንመጣም፡፡" ይሏታል፡፡ እሷም እናቷ ስትመጣ፣ "ሰዎች መጥተው እኮ እንዲህ አሉኝ፡፡" ትላለች፡፡ ከዚያ እናቲቱ፣ "ቆሎ ቆርጥሞ ውሃ እማይጠጣ እስኪ ፈልገህ ካገርህ አምጣ በይው!" አለቻት ይባላል፡፡

## ተረክ ሃያ ሁለት

የአፄ ቴዎድሮስ አባት ኀይሉ የሚባሉ የታወቁ ከብት አርቢ ቅማንት ነበሩ፡፡ ከብቶቻቸውን ይዘውም ከወዲያ ወዲህ እያሉ በዘላንነት የሚኖሩ ስለነበር ሚስታቸውን ወንበዴ ነጠቃቸው፡፡ በዚያን ጊዜ አንዲትን እንቆቆ ሻጭ ደሀ ልጃገረድ ሴት አብራቸው ትተኛ ዘንድ ይጠይቋታል፡፡ ሰውየው ነብይነትም ስለነበራቸው ከዚህች ሴት የሚወለደው ወንድ ልጅ ሀገርን አንድ አድርጎ የሚመራና ተአምረኛ እንደሚሆን ያውቁ ነበር፡፡ ሴትዬይቱም "ከእርስዎ መድረስ አቅሜ ከሆነ እሺ" በማለቷ ይህ ልጅ ተረገዘ፡፡ አባቱም አብሯት ባደረ ማግስት ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ነግሯት ሄደ (ጠፋ)፡፡ ከዚያ በኋላ አልተገናኙም፡፡

ቴዎድሮስ ሲወለድም ላም ግባት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የመንደሩ ከብት ሁሉ በርግጎ በረቱን እየሠበረ ሄደ፡፡ ባለከብቱ ሁሉ "ምንድን ነው የኔ ከብት በርግጎ"፣ "የኔም"፣ "የኔም" ይባባል ጀምር፡፡ ያኔ አንዲት ሴት መውለዷንና ይህ ሁሉ የሆነው የሷን መውለድ ተከትሎ እንደሆነ ተነጋገሩ፡፡ እንዲህማ ከሆነ ይሄ የከብት ጠር ነው" ብለው ልጁን ለመግደል እንደተማከሩ ባወቀች ጊዜ እናቱ ይዛው ወደ ቋራ ተሠደደች፡፡ በስደት ላይም ሳለች አንድ ቦታ ስትደርስ የቀን ስራ እየሠራች ልጇን ለማሣደግ የሙያ ተቀጠረች፡፡ በእርሻ ቦታ እየሠራችም አረፍ

ብላ ልጇን እያጠባች ሳለ ልጁ ቢፀዳዳ ሽንትና ቅዘኑ የነካው ሳር ሁሉ ጨሰ፤ ደረቀ፤ ተቃጠለ፡፡ የዚህን ጊዜ ያዩ ሰዎች "እንዴት ያለ ሰው መጣ ሳርን በሽንትና በቅዘኑ የሚያሳርር" ሲሉ ተደነቁ፡፡ የዚህ ጊዜ እናቱ "አወቁብኝ" ብላ ይዛ ደግሞ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ እንዲሁ ደግሞ ሌላ ሀገር ሄዳ የቀን ስራ ስትሠራ ልጇን ማሳ ዳር አስቀምጣው ነበር፡፡ በኋላ ይገለበጥብኝ (ይወድቅብኝ) ይሆን ብላ ስትመለከት እንኳን ሊወድቅ ዘንዶ ዙሪያውን ተጠምጥሞ አቅፎት ልጁም ዘንዶውን ዘንዶውም ልጁን ሲላላሱ አየች፡፡ አብረዋት ይሠሩ የነበሩት ሁሉ ይህን ታምር ሲያዩ ደነገጡ፡፡ አሁንም ልጇ እንዳይጋለጥባት ይዛ ተሠደደች፡፡ ከዚያ እናቲቱ ቋራ ላይ ሞተች፡፡ በዚህ ጊዜ "ይሄ ህፃን ለመንግስት ይግባ" ተብሎ በጊዜው ለነበሩት የጐንደር ገገር ተሠጠ፡፡ በዚያም አደገ፡፡ ሲያድግም ተዋቡ አፈቀረችው፡፡ ከዚያም እናቷን፣ "ይህን ሰው ወደድኩት" ብትል፣እናቲቱ አይሆንም ደግሞ ይህን ቅማንት አንቺ የምታገቢው ሞቼ ነው ቆሜ" ብትል፣ ልጅቱ፣ እንዳው ከሱ ውጪ አሻፈረኝ አለች፡፡ ከዚያም ተጋቡ፡፡

በኋላ ግብር በሚደረግበት ጊዜ ለቅማንትና ለአማራ የተለያዩ መስተንግዶ ዝቅና ከፍ ተደርጐ ይደረግ ጀምር፡፡ ብዙ የሚገብረው የቅማንት ህዝብ ሆኖ ሳለ ለሱ ያነሰ፣ ይልቁንም ትንሽ ለሚገብረው አማራ ከፍ ያለ መስተንግዶ ይደረግ ጀመር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ልዩነቶችን ስለሚያይ ከጀግንነቱ የተነሳ ተመረረ፤ ተከፋ፡፡ ተዋቡ በጣም ሲከፋ ስታየው፣ “ማድረግ የሚገባህና የምትችለው ነገር ካለ አድርግ” አለችው፡፡ እሱም፣ “አንቺን ይከፋሻል ብዬ ነው እንጂ እኔም ከፍቶኛል፤ ሆድ ብሶኛል” አላት፡፡ እሷም፣ “እኔስ እየተገለልኩ አይደሎወይ መች እንደ ልጅ ተቆጠርኩ አሁን አታመንታ ያሻህን አድርግ፡፡” አለችው፡፡ ከዚያም ከሱ ጋር አብረው ሲገለሉ የነበሩ ቅማንቶችን ይዞ የሚሠራውን ጀብዱ ሁሉ ሠርቶ ሦስት ቤት አቃጥሎ ሲወጣ ተዋቡን፣ “እንግዲህ ምን ይዋጠኝ?” ቢላት እሷም፣ “አንተንም ያገርህ በርሃ፣ የዞርከው ያየኸው ይዋጥህ፤ እኔም የሚውጠኝ ቦታ አላጣም” አለች፡፡ ከዚያ እሷን ጭልጋ ለአባ ኮልባ አደራ ከሰጠ በኋላ ወደቋራ ሸፈተ፡፡ ከዚያ ድል እያደረገ ጠላትን እየጠረማመሰ ዘልቆ ሲገሠግስ፣ “ስምህን ንገረን” ሲሉት “ስሜን ስሜን ላይ ስደርስ እነግራችኋለሁ” እያለ ዘልቆ ሁሉን ነገር ድል ካደረገ በኋላ አልጋ ያዘ፡፡ ከዚያ ወዲያው ተዋቡን አምጡልኝ ቢል አሽሟጣጭ፣ “አባኮልባ ሚስትህን እኮ ለልጁ ለአባ ዘውዱ ወስዶ ሠጥቷት ነበር፡፡” አሉት፡፡ ከዚያ መቼም ቴዎድሮስ መለኛ ነው እንዲች አድርጎ ለማንም ምንም ሳይተነፍስ ተዋቡን ካስመጣ በኋላ ድግስ ይደግስና የአካባቢውን መኳንንት

ሁሉ ይጠራል፡፡ እነ አባ ኮልባና አባ ዘውዱም የድግሱ ታዳሚ ነበሩ፡፡ በድግሱም ላይ ተዋቡን አሳላፊ ያደርጋል፡፡ ከዚያ ጠጅ ስትቀዳ፣ "ለዘውዴ ስጪው" ቢላት ወስዳ ለሌላ መኳንንት ሰጠች እንጂ ለዘውዴ አልሠጠችውም፡፡ አሁንም፣ "እንዴት ለዘውዴ አልሰጠሽውም ስጪው እንጂ" ቢላት አሁንም ለሌላ መኳንንት ሠጠች፡፡ በኋላ፣ "ምን ነክቶሻል ለዘወዴ ስጪው ነኮ የምልሽ!" ቢላት፣ "እኔኮ ዘውዴን አላውቀውም" አለች፡፡ ከዚያ ለአባኮልባና ለነዘውዱ ሽልማትና ሹመት ሰጥቶ አሠናበታቸው ይባላል፡፡

## ተረክ ሣያ ሦስት

እቴጌ ምንትዋብ ወሰን ቢሰውር የሚባል ወንድም ነበራት፡፡ አንዴ ቴዎድሮስ አስሮት ውሃ በጣም ይጠማውና አንዲት ዋንጫ ውሃ በአምስት መቶ ብር ልግዛህ ብሎ ሲለምነው ቴዎድሮስ እምቢ ይላል፡፡ በዚህም በውሃ ጥም ይሞታል፡፡ ከዚያ እህቲቱ ስታለቅስ፣

"ጌታ የጌታ ልጅ ወሰን ቢሰውር
ውሃ ልግዛ ይላል ባምስት መቶ ብር
አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ
አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ፈጃችሁ፡፡
ይህንን ሲሰማ ያጐራል አመሉ
ማነች ያለ እንደሆን ምንትዋብ ነች በሉ፡፡"

ብላ ተቀኘች፡፡ ከዚያ ቴዎድሮስ አስመጣትና፣ "ምን አልሽ?" ቢላት ያንኑ ደግማ ተናገረች፣ "እሽ አንቺ በኔ እጅ ሞተሽ መንግስተ ሠማያትን ልትወርሺ አልገልሽ!" ብሎ ሳይገድላት ቀረ፡፡

## ተረክ ሣያ አራት

ድሮ ቴዎድሮስ ህገ ወጥ ሰዎችንና ብለሹ ሥነምግባር ያላቸውን ሰዎች እያነሳ ገደል ሲጨምር አንድ ቄስ ካፋፍ ቆሞ ዝም ብሎ ይመለከታል አሉ፡፡ ከዚያ ቴዎድሮስ ሰዎቹን ወርውሮ ከጨረሰ በኋላ ቄሱ ጋር ሄዶ፣ "አንተ አረግራጊ፣ አቴና ወጊ፣ ወገቡን ሠባቂ! ምን ቆመህ ታየኛለህ ወይ አላገዝሽኝ ወይ አልገዘትከኝ" ይልና ቄሱንም አንስቶ ገደል ሠደደው ይባላል፡፡

## ተረክ ሃያ አምስት

የፋሲል ግንብ በሚሠራበት ወቅት ከበረሃ ትልሚ የሚባል ግንድ እየተቆረጠ ይመጣ ነበር፡፡ ከዚያ አንድ መንደር እዚህ የኛ መንደር ያርፋል፡፡ በዚህም ያቺ መንደር ግንድ መጣያ ትባላለች፡፡ ግንቡንም የሠሩት ቅማንቶች ናቸው ይባላል፡፡

## ተረክ ሃያ ስድስት

ፈጣሪ የሠውን ልጅ ከጭቃ አድቦልቡሎ ሊሠራው ወደደ፡፡ ከዚያም አድቦልቡሎ ሠራውና ይጠነክር ዘንድ በእሳት ጠበሠው፡፡ ከእሳት ውስጥ የወጣውም ሰው እጅግ ያረረ ስለበረ በጣም ጥቁር ነበር፡፡ ከዚያም ያንን ጥቁር ፈጣሪ አልወደደውም (የሚፈልገው መልክ ስላልሆነ)፡፡ እንደገናም ሌላ ጭቃ አድቦለበለና ወደ እሳት ከተተው፡፡ የመጀመሪያውን ማረር አይቷልና ይህም እንደዚያው እንዳይሆንበት ቶሎ አወጣው፡፡ ነገር ግን ያለቅጥ ሊጥ ሆነ፤ ነጣም፡፡ ፈጣሪ አሁንም የተመኘውን መልክ ባለማግኘቱ ይኸኛውንም ጣለና ሦስተኛ ሰው አድቦለቦለ፡፡ ከዚያም እንደ መጀመሪያውም ሳያር እንደ ሁለተኛውም ሊጥ ሳይሆን የተስተካከለ ሰው አገኘ፡፡ በዚህም እጅግ ተደስቶ ወዳጅ አድርጎት ይኖር ጀመር፡፡

## ተረክ ሃያ ሰባት

አይነርና እንተላ ቀደም ሲል ሰው በሌለበት የከርከር በርሃ ይኖሩ ነበር፡፡ ያኔ ዲዛ የሚባል እንጨት በቁሙ ፈልፍለው እዚያው ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ አኗኗራቸውም የዱር አውሬ እየደበደቡ እየበሉ ነበር፡፡ ሰው ሣያያቸው አርባ ዓመት በዚያ በረሃ ኖሩ፡፡ ቀደም ሰው ሣይፈጠርም ይሁን እንጃ፡፡ ከዚያ ሲወጡ ሰው ያያቸዋል፤ ከዚያ ያያቸው፣ "ይሄ ምን ሰው ነው?" ሲል፣ "አነይር አነይር" አለ፡፡ "አነይር ማለት "የኛ ሰው" ማለት ነው በቅማንተኛ፡፡ አሁን እሱን ይዘው ቅማንቶች የእንጨት ልጆች ናቸው ይሉናል ግን አይደለም፡፡ እነዚህ ሰዎች ከእንጨት ወጡ እንጨቱ ወለዳቸው ብለው፡፡

## ተረክ ሃያ ስምንት

አንዴ ቴዎድሮስ ከነገሰ በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ የሰው ሀገሩ ወዴት ነው? የእህል ሀገሩስ ወዴት ነው? የከብት ሀገሩስ ወዴት ነው? ብሎ ጠየቀ አሉ፡፡ አንዱ ሲመልስም፣ "የሰው ሀገሩ ቋራ፣ የከብት ሀገሩ ደራ ፎገራ፣ የእህል አገሩም ፈኑ (እድሉ) ነው" አለ አሉ፡፡ ቴዎድሮስም፣ "አይ ሞኞች እኔ አንድ ሰው ከቋራ ስለተገኘሁ የሰው ሀገሩ ቋራ ነው

ትላላችሁ?! እስቲ ቋራ ማን አፍርቶ ያውቃል? የሰው ሀገሩ ባህሪው ብቻ ነው፡፡ የሰው ሀገሩ ግብሩ፣ የከብት ሀገሩ ጌታው፣ የእህል አገሩ ቀኑ ነው" አለ አሉ፡፡

## ተረክ ሃያ ዘጠኝ

አንድ ንጉስ ደግሞ ቅማንቶችን እየፈለገ በጊንጥ ጅራት ሲያስበላ ይኖርና ንጉስ እድሜ የለውም ይሻርና አንዱ ይገባል፡፡ እነዚያም የሞቱ ሞተዋል የተረፉት በዱር በገደል ቆይተዋል፡፡ ከዚያ ሰባት አመት ድርቅ ይከሠታል፡፡ የዚያኛው ንጉስ ስቃይ ለዚህኛው ይደርሳል፡፡ ከዚያ ንጉሱ በጣም ይጨነቅና ግራ ይጋባል፡፡ ከዚያ አንድ ነብይ፣ "የቅማንቶች ግፍ ነው ድርቅ ያደረገው አሁንም እነሱ ካልፀለዩ ዝናብ አይመጣም ስለዚህ እነሱን ካሉበት ሀገር አስፈልግና መጥተው ይፀልዩ፡፡" ሲል፣ "የት ነው ያሉ?" ብሎ ፍለጋ ይገባል፡፡ ደግሞ ዛሬም የተሸመው የፈለገን ሊፈጀን ነው፡፡" ብለው ሲደነግጡ፣ "አይደለም መንግስት ለሌላ ነገር ፈልጓችሁ ነው እንጂ ልትጠፉ አይደለም፡፡" ይላቸዋል፡፡ ከዚያ ቀረቡ፡፡ ከዚያም፣ "እባካችሁ ፀልዩና ዝናብ አምጡ ያለናንተ አይሆንም ተብሏል፡፡" ብሎ ይማፀናቸዋል፡፡ "እንዲህ አላችሁ?" "አዎ" "በኛ አቅም ይሆናል?" "አዎ" "እንግዲያው በኛ አቅም ከሆነ ዛሬ አንፀልይም ቀን ይመደብ፡፡ ሰባት አመት የቆየ ዝናብ ከብት አለ፣ ቤቱን ያላዘጋጀ አለ፣ ስለዚህ በመንግስት አዋጅ ይደረግ፣ በዚህ ቀን ስለሚፀልዩ ተብሎ ይነገር በዚያ ቀን ከብቱም ምኑም ተከውኖ ይቀመጥ ድንገት የኖረ ዝናብ ሲመጣ ጥፋት እንዳይሆን" ተባለ፡፡ ሰፋ ያለ ቀጠሮ እስከ ሁለት ወር ተያዘ፣ ከዚያ ታወጀ፡፡ ከዚያ በዕለቱ በስርአቱ፣ በማዕረጉ፣ በወጉ ሲፀልዩና መስዋዕት ሲያቀርቡ በጣም ከባድ ዝናብ ዘነበ፡፡ ያኔ የዘነበው ዝናብም መሬትም ለመቻል ከበደው ይባላል፡፡

## ተረክ ሰላሳ

አንድ ሌባ ነበር፡፡ ያ ሌባ ከብት እየሠረቀ ይሸጣል፡፡ አንድ ቀን ከብት ሠርቆ ይሸጥና በቅሎ ገዝቶ አለንጋውን በእጁ ይዞ አንድ ሽማግሌ ያየዋል፡፡ ከዚያ፣ "ጤና ይስጥልኝ" ብሎ ሽማግሌው ሠላምታ ያቀርባል፡፡ ከዚያም፣ "በቅሎ ገዝተህ ነው?" ይለዋል፡፡ ያ ሌባም፣ "አዎ" ይላል፡፡ "ኧረ ጥሩ በቅሎ ገዝተህ የል እስኪ አለንጋይቱን ስጠኝ ልይልህ" ብሎ ይቀበልና መሬቱን ሾጥ ሾጥ አድርጐ፣ "አይ በዚህ አለንጋስ በቅሎህን ሳይሆን ያን የበሬ ሌባ ነበር መግረፍ" አለው ይባላል፡፡

## ተረክ ሰላሳ አንድ

አንዴ ለአፄ ቴዎድሮስ ሄደው አንድ ቸኮል የሚባል ባሶ ገበያ የምትባል ቦታ ላይ የውንብድና ሥራ የሚሠሩ ሰውዬ ነበሩ፡፡ በፋስ እየደበደቡ ይዘርፉ ነበር፡፡ ቴዎድሮስም፣ "ወንበዴውን ይቅርታ ላድርግለት አቅርቡት" ብለው አስቀረቡትና፣ "በምንድን ነው ስትሠራ የነበርከው?" ብለው ቢጠይቁት፣ "በፋስ እየደበደብኩ ነው፤ እንደው እግዜር አሳብዶኝ ነው፡፡" "ወይኔ ቴዎድሮስ ወይኔ መይሣው እኔም እኮ አንዳንድ ቀን ወፈፍ እያረገኝ ነው፡፡" ብለው ተገርፎና ተሰቅሎ እንዲሞት አደረጉ፡፡ የዚያ ሰውዬ ልጅ፣

"ቸኮል ባሶ ገበያ ተሹመህል አሉ፤

ተዋጋ አትበለጥ እንደወትሮህ ሁሉ፡፡"

እያለች በየለቅሶው ላይ ትገጥም ጀመረ፡፡ ቴዎድሮስም እስኪ አቅርቧት ብሎ ያስቀርባታል፡፡ "ምንድን ነው አበራሽ ቸኮል ምን ብለሽ ነው ይህንን ያልሽው? እኔን እየሠደብሽስ እኔ ገበያ ምን ብለሽ መምጣት ደፈርሽ?" ይላታል ቴዎድሮስ፡፡" እሳት፣ ውሃ፣ ዳኛ አንድ ናቸው፡፡ እሳት ንብረታችንን ቤታችንን አቃጥሎ ግን የምናበስልበት ነው አንተወውም፤ ውሃም ልጃችንን ንብረታችንን ወስዶብን ግን አንጠላውም፤ መጠጣችን መታጠቢያችን ነው፤ ንጉስም ቢበድለንም ከሱ ውጪ አንሆንም ዞረን ከጉያው አንወጣም፡፡ በርግጥ በደሌ በደል ነው ተበድያለሁ፡፡" ትላለች፡፡

## ተረክ ሰላሳ ሁለት

በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሦስት ሌቦች ነበሩ፡፡ የሚሠርቁትም ማርና ቅቤ ብቻ ነበር፡፡ አንድ ቀን አንደኛው በህልሙ ያየውን እንዲህ ሲል ለሁለቱ ጓደኞቹ ነገራቸው፡፡ "በህልሜ ፈጣሪ 'እነዚህ ሀገር አጥፊ ሌቦች ናቸው፡፡ ስለዚህ ያንተ ናቸውና አጥፋቸው' ብሎ ለዲያብሎስ ሲሰጠን አየሁ፡፡ ዲያብሎስም አርባ ክንድ ጥርሱን አግጥጦ እንገት አንገታችንን ፍጥርቅ አድርጎ ነክሶ ወዲያና ወዲህ ውን ውን አድርጐ (አወዛውዞ) እንጥሮጦስ ሲያስገባንና እሳት ሲበላን ብንን አልኩ፡፡ ስለዚህ እኔ ከንግዲህ ስርቆት ይቅርብኝ ብሎ ነገራቸው፡፡"

ሌላኛው ደግሞ፣ "ኧረ እኔም እንዴት ያለ አስፈሪ ህልም ነው ያየሁት፡፡ ማር ይመስለኛል ሰርቄ ስሄድ ባለቤቶቹ ደርሰውብኝ 'አብረን እየዋልን፣ ከእርሻው፣ ከለቅሶው ከሠርጉ፣ ባጠቃላይ ከማህበረሰቡ ጋር አብረህ እየኖርክ የኛን ቅቤና ማር ከቤታችን እንዴት

ትወስዳለህ? እንዳንተ ያለውን እግሩን አስሮ እየጐተቱ ግራጫ ጉድጓድ ውስጥ ነው መጨመር’ ብለው እጅና እግሬን ግጥም አድርገው የኋሊት አሠሩና እየጐተቱ ወስደው የግራጫ ጉድጓድ ውስጥ ከተቱኝ፡፡ ከዚያም ‘ከዚህማ ይወጣል’ ብለው ትልቅ ድንጋይ ሲጭኑብኝ ብንን ብል በህልሜ! ከዚህ በኋላ መስረቅ ይቅርብኝ” አለ፡፡

ሦስተኛው ምንም አልተናገረም፡፡ ከዚያ ሁለቱ፣ “በቃ ትናንት የሠረቅነውን እንብላና እንበታተን ከዚህ ወዲያም አንስረቅ፡፡” አሉና ቢያዩት እቃው ባዶ ሆኖ አገኙት፡፡ ለካ ያ ሦስተኛው በልቶት ኖሯል፡፡ “እንዴ ማን በላው?” “እኔ” “ምን ብለህ እኛን ትተህ?” “ኧኸ ምን ይላል?! እግዜር በሠማይ ሰው በምድር ሲያሯሩጡን እጅ ከፍንጅ እንዳንያዝ ብዬ ነዋ!” ከዚያ ሦስቱም ስርቆታቸውን ትተው ይኖሩ ጀመር፡፡

## ተረክ ሶስት

ባልና ሚስት ሲኖሩ ሲኖሩ ያው ሴትየዋ በውጪ ተላምዳለች ካንዱ፡፡ ገበያ ምናምን ስትሄድ በዚያው እየለመደች ትሄዳለች፡፡ አንድ ቀን፣ “በል እንግህ የሆነ ምልክት ስጠኝ” ትለዋለች፡፡ እሱም ምልክት ሠጣትና ይገናኙ ጀመር፡፡ ሲመጣ ቀሚሷን መሀረቧን ወስዳ ትሠጠዋለች፡፡ ከዚያ ያንን ቀሚስ ለብሶ ያንን መሀረብ አስሮ ሄደና ከቤቷ ገባ፡፡ እሷም እህቴ መጣች ትልና ይታረዳል፡፡ ከዚያም በሉ፤ ጠጡ፡፡ ሲመሽም እኔ ከእህቴ ጋር ነው የምተኛው ብላ ተኛች፡፡ ሲነጋ ሚስት ገበያ ልትሄድ እህቴ ላለችው ውሽማዋ፣ “ይሄን ይሄን ስሪ” ብላ አቀራርባ ወደ ገበያ ሄደች፡፡ ያን ሰራርቶ እንዲያ ሲል ባል ይጠራጠርና ሊይዛት ሲል ቢያያት ወንድ! ከዚያ እየሮጠ ይሄድና ከመንገድ ይጠብቃታል፡፡ “ምን ሆነህ ነው?” “አይ እኔማ ባልሽ እንዲህ እንዲህ...” “በልና ዝም ብለህ፤ እንዲህ እንለው የለ! እ ዛሬ ገበያ ያየነው ጉድ መአት አየሁ ወንዱ ሴት ሴቱ ወንድ ሆነ እንዲህ ሳይ ሮጬ መጣሁ እለው የለ!” ይሉና ተመልሰው ያን ይነግሩታል፡፡ እሱም ያንቺም እህት እዚህ እንደዛ ሆና የለ ብሎ መለሠላት፡፡

## ተረክ ሰላሳ አራት

ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ብዙ ሀብትና ንብረት አፍርተው ሲኖሩ ሚስትየዋ ከአንድ ሽፍታ ትለምዳለች፡፡ በኋላም ሽፍታው ተሸሎ ስላገኘችው አግብታው ለመቀመጥ ትወዳለች፡፡ ከዚያ አመመኝ ብላ ትተኛለች፡፡ ባልየውም፣ “ምነው ምን ሆነሻል?” ይላታል፡፡ እንዳመማት

ትነግረዋለች፡፡ "ታዲያ ምን ይሻላል? ወደ አዋቂ ጋር ልውሰድሽና ታዪ እንጂ" ይላታል፡፡ "አዋቂ ማጋ ሄጂ ነበር" "ታዲያ ምን አለሽ?" "በጉም ተቀጥላ የተጠመቀ ጠላ ካልጠጣሽ አትድኚም አለኝ፡፡" ትለዋለች፡፡ "በይ ስንቄን አዘጋጂልኝ ሄጄ ይገኘ እመጣለሁ፡፡" ይልና ስንቁን ይዞ ጉዞውን ይጀምራል፡፡ ከዚያ አንድ ሽማግሌ ያገኙትና፣ "ወዴት ትሄዳለህ ልጄ?" ሲሉት ነገሩን ያጫውታቸዋል፡፡ "በል ተመለስ ይህች ሴት አንተን መግደል አስባለች ማለት ነው፡፡ የጉም ተቀጥላ እይዛለሁ ብለህ ገደል ገብተህ እንድትሞት አሊያም ጉም አይያዝምና የደረስክ እየመሰለህ ስትጓዝ ካገር ጠፍተህ እንድትቀር አስባ ነው፡፡" ይሉታል፡፡ "ታዲያ ምን ይሻለኛል?" "አሁን እኔ መንገደኛ መስዬ እቤታችሁ አሳድሩኝ እላለሁ፡፡ አንተንም ባቁፋዳዬ ውስጥ ይዤህ እገባለሁ ከዚያ እዚያ የሚሆነውን ታያለህ፡፡" ይሉትና ባቁፋዳቸው ይዘው አሳድሩኝ ብለው ይገባሉ፡፡

መሸት ሲልም ያ ሽፍታ መጣ፡፡ ሲበሉ ሲጠጡ አምሽተው ማታ ሲተኙ አቁፋዳቸውን ይፈቱና ባልየው ይወጣል፡፡ ባልም የዚያን ሽፍታ አንገት ቆርጦ ይዞት ይሄዳል፡፡ ሚስት ጠዋት ስትነሳ አልጋዋ በደም ጨቅይቶ! የዚያ ሽፍታም አንገት ተቆርጦ ታያለች፡፡ "አንቱ የትናንቱ ሰው አንገት አልነበረውም?" ትላለች ደንግጣ፡፡ "አንቺ ታውቂ" ይሏታል፡፡ ከዚያ "በይ እንግዲህ ይህን ሬሳ በጋን ወስደሽ ገደል ስደጂው፡፡" ይሏትና ጋኑ ከሠውነቷ እንዳይፈታ አድርገው ያሣዝሏታል፡፡ ከዚያም ያን ሬሳ ከነጋኑ ገደል እሠዳለሁ ብላ አብራ ገደል ገብታ ሞተች ይባላል፡፡

## ተረክ ሰላሳ አምስት

አንድ ሴት አዳሪ አንድ ወንድ ትወድና ትይዛለች፡፡ ከዚያ አንድ ቀን አንዱ ይመጣባትና ለወዳጇ፣ "ዛሬ አባቴ መጥቷልና እንዳትመጣ፡፡" ትለዋለች፡፡ "አባቴ መጥቷል?!" "እዎ" "በይ እሺ" ይልና ይሄዳል፡፡ የድሮ ቤት ቀዳዳ አይደል! ከዚያ ያ ሰውዬ ይጠራጠርና ማታ ሄዶ በቀዳዳ ያያል፤ ተኝተው ያያል፡፡ ከዚያ ይሄድና፣ "አንቺ እከሌ" "አቤት" "አባት ባገርሽ ያደርጋል?" አላት ይባላል፡፡

## ተረክ ሰላሳ ስድስት

በአንድ ሀገር የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ አንዴ ባልየው ስጋ ሊያመጣ ሄዶ ውሽማዋ ይመጣል፡፡ ከዚያ እየተጫወቱ ሳለ ባልየው ስጋውን ይዞ ሲመጣ ውሽማዋን ከጐተራ ውስጥ ትደብቀዋለች፡፡ ከዚያ ያን ስጋ እየጠበሱ ሲበሉ፣ ሚስት፣ "ከጐተራው ውስጥ ያለው ቆሌ እኮ ስጋ ያምረዋል፡፡" ትልና ጥሬ ስጋ ወደ ጐተራው ውስጥ ጣል ታደርጋች፡፡ ባልየውም፣ "አይ በምን ጠብሶ ይበላው ብለሽ?" ይልና እሳት ሲከት እሷ ደግሞ "ውይ በምኑ ያወራርደዋል?" ትልና እንዳይቃጠልባት ውሃ ትደፋለች፡፡ ከዚያ ውሽምየው "እረ አንገርግበው ቆሉኝ" አለ ይባላል፡፡

## ተረክ ሰላሳ ሰባት

ያሁን ልጅ ስለ ኑሮው አያስብም፡፡ ድሮ ግን ህግ ነበር፤ አንድ ሺ ከብት የሌለው ደግሶ ማግባት አይችልም ነበር፡፡ አሁን አንድ ሰውዬ አንድ ሺ ከብት አለው፡፡ ለዚህም መረጃ ማቅረብ ነበረበት፡፡ ያገር ሽማግሌዎች ይቀመጡና መስክረው ነው መደገስ የሚችለው እንጂ እንደ አሁን ልጅ ተበድሮ አያገባም ነበር፡፡ ከዚያ ይሄ ሰውዬ ከብት ያርድና የሚታረደው ከብት አይቆጠርም፡፡ ከዚያ ሰውየው ያለው አናቱ ላይ አንድ ሺ ከብቶች ነበሩ፡፡ ከዚያ በመጨረሻው ሲያስቆጥር አንዲት ዶሮ ሞታ ተገኘች፡፡ አሁን ልግዛ ቢል አይሆንም ምክንያቱም ሽማግሌዎቹ ችሎት ላይ ናቸው፡፡ ከዚያ አንድ ስለሚጐድልህ ደግሰህ ማግባት አትችልም ተብሎ ተደናቀፈበት ይባላል፡፡

## ተረክ ሰላሳ ስምንት

አንዴ ፈጣሪ አዳምና ሄዋንን ሊጐበኛቸው መጣ፡፡ ከዚያም፣ "ሄዋን ልጆችሽ የታሉ አስተዋውቂኝ" አላት፡፡ እሷም፣ "ያኔ እኔና ባሌን አባረረን ደግሞ ዛሬ ልጆቼን ወዴት ሊያጠፋብኝ ነው?" ብላ አስባ ቆንጆ ቆንጆዎቹን ልጆቿን ሸሽጋ መልከ ጥፉ መልከ ጥፉዎቹን አሣየችው፡፡ ፈጣሪዋም፣ "እነዚህ ያሳየሽን ይታዘዙሽ፤ ይርቡልሽ፤ ይሸማገሉ፤ ይማከሩ፤ ል ጅና ዘመድም ይ ሁኑሽ፡፡ የደ ብቅሻቸው ካሉ ግን እንደተሠወሩ ይ ቅሩ፤ ለወንድሞቻቸውም እሾህ፣ እንቅፋት፣ ሣል፣ ጉንፋን ይሁናቸው፡፡ አጐንብሰው ያጉሩ ቋንቋቸው የተለየ ይሁን፡፡" ብሎ ረገመ፡፡ ከዚያም ተደብቀው የነበሩት ቆሌ፣ ዛር፣ ውቃቢ ሆኑ፡፡

## ተረክ ሰላሳ ዘጠኝ

አንዱ ሌባ አራት ሰንበቴ ይጠጣል፡፡ ከዚያ የሱ ተራ ይደርስና ለመደገስ ካንዱ ጐተራ ጥልቅ ይላል፡፡ አንዱን ጓደኛውን ከውጪ አድርጐ እየዛቀ ያቀብላል፡፡ ከዚያ ባለቤትየው ከተፍ ሲል ተቀባይ ያመልጣል፡፡ ሌባው ግን መምጣቱን ስላላወቀ እየዛቀ ያቀብላል፤ ያኔ ባለቤትየው ይቀበላል፡፡ በቃህ ይለዋል (ተራኪው ድምፃቸውን ዝቅ እያደረጉ ነው የሚናገሩት እያንሾካሾኩ)፡፡ "እረ እባክህ ወንድሜ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ፣ ማርያም… አይበቃኝም ዝም ብለህ ቶሎ ቶሎ ተቀበለኝ" ይላል፡፡ "እረ በቃህ ውጣ" ቢለው፣ "ምነው ድምፅህ ተቀየረ?" ይላል፡፡ ከዚያ "በል ና ውጣ" ብሎ በጦር ቢለው ይወጣና ይሮጣል፡፡ ውሻውም እያሯሯጠ ይዘነቻችረዋል፡፡ መንደሩ ባጠቃላይ ይታወካል፡፡ በኋላ ያመልጥና ታክሞ ይድናል፡፡ ከዚያ ይዝታል፡፡ "እንደው ይህ ፈሳም ሰውዬ ይችን ረዥም ምንሽሩን ነው የምቀማው፡፡" ከዚያ በጨረቃ ወደ ሰውየው ቤት መጣ፡፡ የባላገር ቤት ነው፡፡ ፈልቀቅ አድርጐ ገባ፡፡ ሰውየው አገር አማን ብሎ ሚስቱን አቅፎ ያንኮራፋል፡፡ ከዚያ ሌባው ጠመንጃዋን ብድግ ሊያደርግ ከሠደፏ ሲደርስ ሰውየው ንቅት ይላል፡፡ ከዚያ ያ ጠመንጃውን ይዞ ይሮጣል፤ ይህም ይከታላል፡፡ ከዚያ ጣጥሎት ሲሮጥ ይሄኛው ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ያም እቤቱ ይደርሳል በሌላ ቀን የተሠረቀው ሚስቱ ግብር ውሃ ወጥታ ስትመለስ አልቤን ቤቷ ቆሞ ታያለች፡፡ "ምነው አንተ ደግሞ ይሄንንም ይውሰደው? "ምኑን?" አለ ባልየው፡፡ "ጠመንጃውን ነዋ!?" ከዚያ በሽማግሌ ገብቶ ጠመንጃውን ይመልስለታል፡፡ ግን ያ ሰውዬ ቂሙን አለቀቀም ነበርና፣ "ነገ ደግሞ የምሠርቀው ነኝ" አለ፡፡ ከዚያም አድብቶ ጓደኛውን ይዞ በጉን መስረቅ ፈልጐ ከበጉ ጉረኖ ገባና አንዱን በግ አውጥቶ ለጓደኛው ያቀብላል፡፡ ነገር ግን ባለ በጉ መጀመሪያ በሩ ሲከፈት ሰምቶ ነበርና ሲወጣ ጓደኛው አምልጧል፡፡ ከዚያ ለቤቱ ባለቤት አንድ ወደል በግ አሸከመው ከዚያ ትንሽ እንደሄደ፣ "አልተመቸኝም ይህን ጠመንጃም እንካ ያዝ" ይልና ይደርብለታል፡፡ ከዚያ በተለያየ መንገድ ይሄዱና በኋላ በፉጨት ይጠራራሉ፤ ይገናኛሉም፡፡ ግን የተገናኘው ከእውነተኛ ጓደኛው ጋር ነው የበጉ ባለቤት በግና ጠመንጃውን ይዞ ወደ ቤቱ ነው የተመለሰው፡፡ በኋላ ሲገናኙ፣ "በጉስ?" "እንጃኔ" "ጠመንጃየስ?" "እንጃኔ" "ለማን ሠጠኸው?" ከዚያ ሌባው "ጡጡጡጡ" ይላል፡፡ ከዚያ ሀገር፣ "አንተ ምንድን ነው?" ይለዋል፡፡ "እረ ጠመንጃዬን አያ እገሌ ሰረቀኝ" ቢል፣ "አይ አያ ገሌ አይሠርቅም ያረከው ነገር ቢኖር ነው እንጂ ብሎ ጥበቃ ጓድም፣ ሊቀመንበርም ሠውየውን የሚደግፌው አጣ፡፡ ከዚያ፣ "ያያ ገሌ

ቤት ይፈተሽልኝ::" ይላል:: "አይ የሱ ቤት አይፈተሽም ያረከው ነገር እንዳለ ሽማግሌ ስደድና ታረቅ" ይሉታል:: ከዚያ ሽማግሌ ሰዶ ታረቁ እልሃለሁ::

## ተረክ አርባ

አንድ አቶ ካሳ የሚባሉ ሰው ነበሩ:: እኚህ ሰው ያለቅጥ ደግና እንግዳ ተቀባይ ነበሩ:: ከለታት ባንዱ ቀን ሦስት እንግዶች መሽቶባቸው በተከታታይ ወደ ቤታቸው መጡ:: የመጀመሪያው እንግዳ ዝናብ ነበር::

ዝናብ፣ "እንደምን አመሻችሁ አቶ ካሣ?" "እግዜር ይመስገን፤ ማነ ነህ?" "እኔ ነኝ ዝናብ፤ መሸብኝና ብታስጠጉኝ ብዬ መጣሁ::" "እንዳንተ ያለውን በእንግዳነት አልቀበልም:: እኩሌታውን እያጠገብክ እኩሌታውን ድርቅ የምታደግር ነህና አንተን እንግዳዬ አላደርግም::" ይሉና አሻፈረኝ ይላሉ:: ሁለተኛው እንግዳቸው እግዜር ነበር:: እሱም እንደ ዝናብ ሁሉ፣ "እንደምን አመሹ አቶ ካሳ?" ይላቸዋል:: እሳቸውም "እግዜር ይመስገን ማነህ?" ይላታል:: ይመልስና፣ "እኔ ነኝ እግዜር መሸብኝና ታስጠጉኝ ብዬ መጣሁ::" አላቸው:: እሳቸውም፣ "የለም አንተም የኔ እንግዳ አይደለህም ከአንድ ሆድ የወጡትን አንዱን ደሃ አንዱን ሀብታም፣ አንዱን ነጭ አንዱን ጥቁር፤ አንዱን ረጅም አንዱን አጭር፤ አንዱን ጤነኛ አንዱን በሽተኛ የምታደርግ ነህና አንተ እንግዳዬ ልትሆን አትችልም" ይሉታል:: ሦስተኛ እንግዳቸው ሞት ነበር:: እሱም እንደፊተኞቹ ሁሉ፣ "እንደምን አመሹ አቶ ካሳ?" ይላቸዋል:: "እግዜር ይመስገን ማን ነህ?" "እኔ ነኝ ሞት መሸብኝና ብታሣድሩኝ ብዬ መጣሁ::" "ና ግባ አንተ እንግዳዬ ነህ ሁሉን እኩል የምትዳኝ ለሀብታም፣ ለደሃው፣ ለነጭ ለጥቁሩ፣ ለቀጭን ለወፍራሙ፣ ለረጅም ላጭሩ የማትቀር ነህና አንተስ ና ግባ::" ብለው አስገብተው እግሩን አጥበው መልካም መብልና መጠጥ ጋብዘው በመልካም መኝታ ላይ አሣደሩት ይባላል::

## ተረክ አርባ አንድ

ኃይለ ስላሴ ልጃቸው ይሞትና፣ "ገዳም የምገባ ነኝ" ብለው ይወራጫሉ:: ንስሃ አባትየው፣ "ገዳም ከገቡ ንዛዜ ይናዘዙ" ይሏቸዋል:: ከዚያ ጠየቋቸው፤ "የት የት ሀኪም ቤት ታክሞ ነበር?" "እንግሊዝ፣ አማሪካ ታክሞ ነበር::" "እንግሊዝ አማሪካ?!" "አዎ" "እናሳ ማር ይበላ ነበር? ቅቤ ይበላ ነበር?" "አዎ" "ታዲያ እግዜር ና ብሎት ለሞት ለዚህ ነው እንዴ ገዳም

የሚገቡት!" "እና ለልጅ ገዳም ያልገባሁ" "አይ ፍርድ አጉድለዋል፡፡ እንግዲያው እውነተኛ ክርስቲያን ከሆኑና ገዳም የሚገቡ ከሆነ ንሰሃ ልንገርዎት" አላቸው፡፡ "ለህገሩ በኡጋዴን በረሃ እየወደቀ፣ በኮዳ ውሃ እየቀመሠ የሚወድቅ ወታደር አለ ለሱ ንሰሃ ቢገቡለት አይሻልም?" ቢላቸው ዘለው ካልጋቸው ይቀመጡና፣ "ለካስ እንዲህም አለ! ዙፋኔን አለቅም፡፡" አሉ ይባላል፡፡

## ተረክ አርባ ሁለት

አሁንም አለ ተቀባ የሚባል ሰው ነበር፡፡ ከዚያ ሩዜ የምትባልን ሴት ይወሽማል፡፡ ከዚያ ሲሳይ እንደሻው ይህን ጉዳይ ያውቃል፡፡ ሌላው ሰው ግን ብዙም አያውቅም፡፡ ከዚያ ሩዜን ያያትና፣ "ውይ የተቀባ ሙሽራ ትመስያለሽ፡፡" ይላታል፡፡ ከዚያ ትሄድና ለውሽማዋ፣ "እረ ዛሬስ አንዱ አሞገሰኝ፤ 'የተቀባ ሙሽራ መስለሻል' አለኝ፡፡" ትላለች፡፡ "እረግ ተቀባን ውሽምነት ይዘሻል ማለቱ ነው፡፡" ከዚያ ትናደዳለች፡፡ ከዚያ ተቀባ ደግሞ በዚያ ሲሄድ ያገኘዋል ይኸው ሰው፡፡ "ተቀባ እንዴት ዋልክ?" "እግዚአብሔር ይመስገን" "እንደው ይሄ የኑሮ ውድነት እኮ አስቸገረ" "እዎተወዶ!" "ጤፍ ስንት ገባ?" "እረ በጣም ተወደ.ል" "ለነገሩ አንተ ምን ችግር አለብህ ሩዝህን ትዝቃለህ" አለው ይባላል፡፡

## ተረክ አርባ ሦስት

የኔ እሚታ ሁለት ሚስት ነበረው፡፡ አንዷቷ ወደል፣ አንዷቷ ቀጭን ናት፤ የኔ እሚታ ቀጭን ናት፡፡ ከዚያ ያቺ ወደሏ ዘፈን ገባች፤ "እንካ ብላ ብለው ስጋና ብርንዶ እንቢያለ ጌትየው አክርካሪት ለምዶ" ትላለች፡፡ ከዚያ ቀጭኒቱ የኔ እሚታ ቀበል አድርጋ፣ "ምን ያረገር.ጋል እንደ ሽቦን አል.ጋ እንቢ ብሏችኋል ከኔ ነው ሚረ.ጋ" አለች ይባላል፡፡

## ተረክ አርባ አራት

አንድ ሰውዬ ክፉ ቀን ገብቶ እሱ ለራሱ አንድ ጉድጓድ ውሃ አዘጋጅቶ አበጅቶ ይኖር ነበር፡፡ በወቅቱም ውሃ ጠፍቶ ስለነበር ባለውሃ እሱ ብቻ ነበር ይባላል፡፡ ሁሉም ፍጥረት ተቸግሮ ስለነበር አንድ ሰው ይሄድና፣ "መቼም ሰው ከሰው ነው እባክህ ውሃ አጠጣኝ፡፡" ይለዋል፡፡ ያ ሰውም ያስጠጋዋል በኋላም መልሶ አንዲት አይጥ፣ "እባክህ እስጠጋኝ፡፡" ትለዋለች እሷንም አስጠጋት፡፡ ከዚያም ዝንጀሮ፣ "እባክህ አስጠጋኝ፡፡" ይላል፡፡ እሱንም ያስጠጋዋል፡፡ ደግሞ እባብ ይሄዳል፡፡ ከዚያም፣ "አስጠጋኝ፡፡" ይለዋል፡፡ "አንተን እንዴት

አድርጌ ላስጠጋህ አንተና እኔ እንዴት ብለን አብረን እንኖራለን?" ይለዋል፡፡ "ግዴለህም ብብስ ብብስ ክፋቴ ከሰው አይብስም፤ ዘጠኝ ጊዜ ክፉ ልሁን እንጂ ከሰው አልብስም እባክህ አስጠጋኝ፡፡" ይለዋል፡፡ ያኔ፣ "አይ እንግዲህ እግዜር የሠጠኝ ውሃ አይደለም?!" ይልና፣ "በል በሰአት እየመጣህ ተጠግተህ ጠጣ፡፡" ይልና ሁሉንም ይፈቅዳል፡፡ በኋላ ሲኖሩ ሲኖሩ ቀኑ ወጣና ውሃ በየቦታው ተገኘ ሁሉም ተበተኑ አይጥም ሄደች፤ እባብም ሄደ፣ ዝንጀሮም ሄደ፣ ሰውየውም ሄደ፡፡ ሁሉም በየፊናቸው ሄደው ተዋለዱ፡፡ ከዚያ እግዜር ለውጠኛ ነው ያን ደግ ሰውዬ አደኸየው፤ ደካማ ሆነ፤ የሚያደርገው ቅጡ ጠፋው፡፡ ከዚያ አስቀድሞ ተጠግቶት የነበረውን ሰው መክበር ሰምቶ ነበርና፣ "እስኪ ሄጄ ልጠይቀው፡፡ መልካም ሠርቼለት ነበር፤ እስኪ ወረታ ቢያውቅ!" ብሎ ሲሄድ አይጥ መንገድ ወልዳ ሲጥ ሲጥ ሲጥ ስትል ታየዋለች፡፡ "ምነው ምን ሆኑ?" ስትለው፣ "እኔማ ደህይቼ ክፉ ቀኑ ደግ ሆኖልኝ ደግ ቀኑ ክፉ ሆኖብኝ ደህይቼ ከሰውዬው ልመና አይሄድኩ ነው፡፡ ሰውየው ትንሽ የሚቸርልኝ ከሆነ" "ኧረ ... አየ ጉድ አይ ጉድ... " ብላ አዘነች፡፡ ከዚያ፣ "እስቲ ይቆዩኝ የአቅሜን የምለው ቢኖረኝ" "አይ... አንቺ ምን ትያለሽ? ምንስ ታደርጊያለሽ?" ሲላት፣ "እንዴ አንድ መንደር ሄጄ በከረጢት የተቋጠረ ብር አይቻለሁ፡፡ እርሶ 'ደህይቻለሁ' ነው ያሉት እነሱ ተርፏቸው ነው ያስቀመጡት ይጠጉና አሳዮታለሁ፡፡ እኔ መጐተት አይሆንልኝም ወደዚህ ስቤ ሳመጣ እርስዎ እንዲወስዱ ኑ እንሂድ፡፡" ትልና ሲመሽ ይዛው ትሄዳለች፡፡ ከዚያ ሲደርሱ ጐትታ እስከ ግድግዳው የተወሰነ ድንጋይ ብር ታመጣለችና ይዘው ይመለሳሉ፡፡ ከዚያ፣ "ለሠውየው እንዳያሳዩት ያሳዩት እንደሆነ አግኝተሃል ብሎ እሱ ከሚሰጥዎት ይቀንስብዎታል፡፡" ትልና ወረታዋን በመመለሷ ተደስታ እሱም ገንዘብ በማግኘቱ ደስ ብሎት አመስግኗት ሄደ፡፡ ከዚያ ከሰውየው ደረሰ፡፡ ሰውዬውንም ከብሮ አገኘው፤ ደህና ኑሮም ይዟል፡፡ ከዚያ፣ "እየውልህ እኔ ደህይቼ ተቸግሬ ብትረዳኝ ብዬ ወዳንተ መጣሁ አይጥ እንኳን ይገርምሃል ባቅሟ ይህን ብር ሠጠችኝ አለ፡፡" "እኔማ ዛሬ የለኝ፤ ግን አንተ እንዲህ ከተቸገርክ በፈለከው ቀን አስቤ ነው የማመጣልህ፡፡" ይልና አብልቶ አጠጥቶ ልሸኝህ ብሎ ይከተለውና እያወጉ ብዙ እየተጨዋወቱ ከገደል አፋፍ ሲደርሱ ያን ገንዘብ ይነጥቅና ሠውዬውን ወደገደል ይገፋዋል፡፡ መቼም በጐ ስራ በጐ ነው፡፡ ገደል ሲሰደው ከገደሉ መሀል ትልቅ እንጨት አለ እሱ ላይ ይንጠለጠልና ይድናል፡፡ እዚያ ዝንጀሮ ያገኘዋል፡፡ ያ ዝንጀሮም በዚያ በክፉ ቀን ውለታ የተዋለለት ነበር፡፡ ከዚያ፣ "ምን ሆነህ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ እሱም መንጋ ሆኖ ነበር፡፡ ከዚያም የሆነውን ሁሉ ያጫውተዋል፡፡ "አይጥ ውለታ ብትሠራ ሰው እንዲህ አደረገኝ፡፡ አሁን

ከዚህ የገደል መሀል እንዴት ብዬ ነው የምወጣው?" "በል ዝም በል እንኳን ተረፍክ እንጂ እዚህ አገግመህ ነው የምትሄደው ስለ ሁሉም ነገር አንተን የሚያገባህ ነገር የለም::" ይልና ያ ዝንጀሮ ልጆቹን ይዞ ሰዎች አጥበው ካሰጡት ልብስ እየጠቀለሉ ይዘው ወደ ገደሉ! ከዚያ እያጠፉ ይደለድሉና፣ "በል እዚህ ተኛ::" ይሉና ያስተኙታል:: ከዚያ አንዱ ይሄድና የሚበላ ካንዱ ጋር እየሠረቀ ይዞ ይመጣል:: ሌላው ከሌላ ይዞ ይመጣል:: አንዱ ካንዱ ቤት ካራ ያመጣል፤ አንዱ ከዱር ፍየል ያመጣል፤ ከዚያ አየቀቀሉ እያበሉ እንዲያገግም ያደርጉታል:: ሰውዬውም በጣም ተመችቶት በደንብ ሲያገግም "እኔስ ዳንኩ ላገሬ ልበቃ ነው ግን እንዴት ብዬ ነው ይህን ገደል የምወጣው?" ሲል፣ "ስለመውጫው አታስብ እኛ እናውቃለን::" ይሉና ወር ከቆየ በኋላ፣ "እንግዲህ እኛ የምንሠጥህ ነገር የለም ይህን ብረት ድስትም ውሰድ፤ይህን ልብስም ውሰድ፤ ይህን ካራም ውሰድ:: ብለው ሰርቀው ያመጡትን ባጠቃላይ እውጪ ያወጡና አንድ ሌላውን ተያይዘው እቃውንም እሱንም ከዚያ ገደል አውጥተው ያስቀምጡታል:: ከዚያም ተሠነባብተው ይለያዩና ሲሄድ እባብን ያገኘዋል:: "ምነው ምን ሆንክ?" ቢለው የሆነውን ሁሉ ነገረው:: "አይጥ ብር ሰጥታኝ ሰው ቀምቶኝ ገደል ሠደደኝ ዝንጀሮም ገደል ውስጥ አግኝቶ ተንከባከበኝ፣ ይህን ልብስና እቃም ከየት እንዳመጡት እንጃ ሠጥተው ሠሰደዱኝ::" ይለዋል:: "እየዋ! ብብስ ብብስ ከሰው አልብስም አላልኩህም ያኔ?!" "አዎ አንተማ ብለሀል::" "አዎ ሰው ክፉ ነው:: እርስዎ መላክ ሆነው ነው እንጅ ሰው ክፉ ነው:: አሁን እኔ ነኝ መጠቀሚያዎን የማመቻቸው:: ያ ደግ ባደረጉለት ክፉ የዋለልዎት ሰው ባለፀጋ ሆኗል:: የሱ ብቸኛ ልጅ ታገባለች፤ ሠርጓ ነገ ይሁን ከነገ በስተያ ነው:: እኔ ተሹለክልኬ ሄጄ እነድፋታለሁ:: የእባብ መድሃኒት ይሄ ነው፤እርስዎ ይሄዱና አድኜ ላግባት ይኳቸዋል:: ሌላ ምንም እንስጥህ ቢሎት እንዳትስማሙ:: የምወጋትም ሙሽራው የገባለት ነው::"ይለውና ይለያያሉ:: ከዚያም ያ ሰው ባለሠርጎቹ ጋር ይጠጋል ያው መንገደኛ ነው:: ዝግጅቱን ሁሉ ያያል እንሶስላው ምን... በኋላ የሠርጉለት እባብ ይመጣና ሲቲቱን ሙሽራና አባትየውን ይነድፋቸዋል::

ከዚያ ይተረማመሳሉ ያዘው ያዘው ብለው ይሯሯጣሉ እባብም ያመልጣል:: ከዚያ አባትየው ወዲያው ይሞታል:: ያቺ ልጅ ተዝለፈለፈች፤ መላው ጠፋ ቢያነሱ ቢጥሎ ቢጨነቁ ምን ቢሉ ምንም አልሆነ:: "ኧረ ሞተች፤ ሞተች፤ ኧረ ደከመች::" ሲሉ፣ "አይ እኔኮ የእባብ መድሀኒት አውቃለሁ ሲል፣ "አድናትና ይህን ያህል ብር እንስጥህ አሉት::" "እኔ ብር

አልፈልግም፡፡" "እንግዲያስ ምን ትፈልጋለህ?" ቢሉት፣ "እሷን ለኔ የምታጋቧት ከሆነ ላድናት፡፡" እንዴት አድርገን እናጋባሀለን? ሰውየው መጥቶ ተቀምጦ እያየኸው!" ይሉታል፡፡ "አይ እንደፍቃዳችሁ እኔ አድኜ ላግባት አልኩ እንጂ ግድ አላልኩም፡፡" ይላል፡፡ ከዚያ ሰውየው (አግቢው) ቢያያት ትንፋሿ እየደከመ፣ "ምን ያው ሞተች አይደል! ከሆነለት ትዳንና ይውሰዳት እንጂ ገና በእድሉ ለምትድን ወይ እድሏ ከኔ ባይሆን ይሆናል፡፡" ይልና አድኖ ሊወስድ ይስማማል፡፡ ከዚያ ያቺን መድሃኒት የምትተኮሰውንም የምትቆረጠመውንም ቢያደርግላት ያቺ ልጅ ብድግ ትላለች ከዚያም በውላቸው መሠረት ያገባታል፡፡ ከዚያም ከብሮ ኖሮ ሞተ ይባላል፡፡

## ተረክ አርባ አምስት

አንድ ወንድሜ ሦስት በሮች ይዞ በህዳር ይራባል፡፡ አሁን እቤቱ ሄድኩኝ ወደ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ልጆች አሉት፡፡ እቤቱ ስደርስ የሚያቀርበውም የለው፡፡ "እየወልህ ሰው ውሎብኝ አዝመራዬ ሁሉ ፆም አደረ፡፡" አለኝ፡፡ "ታዲያ ይሄን እኔ እሽረው የለ!" አልኩት፤ ዝም ብዬ፡፡ "መሻሪያ አለህ?" "አዎ" "በል አምጣው" "መሬትክን አሣየኝ" መሬቱን ቢያሳየኝ ልዩ ነው፡፡ "ልጆችህ ጥራ" አልኩት፤ መጡ፡፡ "አንቺ ከዚህ እስከዚህ ሽንኩርት ክፍልሽ ነው፡፡" መሬቱን እየለካሁ፡፡ "አንቺ ደግሞ ቃሪያ ክፍልሽ ነው፤ አንተ ቲማቲም፣ አንተ ነጭ ሽንኩረት፣ ይሄኛው በሬ ተሸጦ ዘር እንዲገዛበት፤ ላባትየውና ለሚስቲቱ ድንች፣ ከዚያ ዙሪያውን ከብት ከጠቀጠቀውም መድሃኒቱን ይሽረዋል" አልኳቸው፡፡ በህዳር ብሄድ አንድ ማድጋ ድንች ካልወሰድክ ብለውኝ እምቢ አልኩ፡፡

## ተረክ አርባ ስድስት

አንዴ ስሸጥ ጉሊት አንዷ ሴትዮ ጉትቻ ሰረቀችኝ፡፡ ሊያውም የቅርብ እህቴ ናት፡፡ ከዚያ እኔ ነዶኝ ሊላውን ንብረቴን በትኜ ፍለጋ ስነሳ አንዷ ዘመዴ ስትቋጥር አሻግራ አይታት ኖሮ፣ "አንተ እሷ ናት የወሠደችው" አለችኝ፡፡ አይ እዚህ ሰረቀች ብዬም እህቴን አላዋርዳትም አልኩና፣ "ይህን የገበያ ሰው ሁሉ ላስፈሳው ነው፡፡" "ምን ብለህ?" "አዎ በቃ ላስፈሳው ነው፤ ላጮኸው ነው፤ ዝም ብለሽ አዳምጪው ብቻ" አልኳት፡፡ "ጉትቻዬን የወሰደ እጁ ይንቀጠቀጣል፤ ምድሩ ይንጫጫበታል፤ ፈስ በፈስ ይሆናል፤ ተመልከች ብቻ" ስላት፣ "ኧረ ተንጫጫብኝ" አለችኝ፡፡ ከዚያ፣ "ጥለውብሽ እንዳይሆን እስኪ ወደዚያ እይው" ስላት፣ "ይሄው እግሬ ጋር ወድቆ" ብላ ሰጠችኝ፡፡

## ተረክ አርባ ሰባት

እስላም ወደ አላህ ይለምንና አላህም ሳይሠማው ይቀራል፡፡ ከዚያ ልጁ፣ "ባባ ልሠርቅ ነኝ እርቦኛል" ይላል፡፡ አባቱም፣ "ተው ልጄ ይህን አላህ አይወደውም" ይለዋል፡፡ "አይ መራብንም እኛ አንወድም እኮ" ብሎ ለስርቆት ሲነሳ አባትየው፣ "አይ ካመረርክማ ጠብቀኝ አብረን እንሂድ ብሎ ተነሳ፡፡ ከዚያ እንዲሁ በድፍረት አይሰረቅም በብልሃት ነው፡፡" ይልና አባትየው ካንድ ባለፀጋ ቤት ይገባና፣ "ላምን በርሃ ክተቱት ኩታራውን ከቤት አግቡት ሊመረቅ ነው ይሄ ቤት ስለዚህ እውጪ ያለ እንዳይወጋ ወደቤት ይግባ" ይላል፡፡ ከዚያ ላምን በረሃ ሰደው ኩታራውን ከቤት አገቡት፡፡ ከዚያ ቡና ተፈላና ባርከው እስኪጠጣ እውጪ የወጣ ይወጋል ተባለ፡፡ ከዚያ በሉ፤ ጠጡ፤ ተመረቁ፡፡ ከዚያ ልጅ እነዚያን ከብቶች ይዞ ጠፋ ይባላል፡፡

## ተረክ አርባ ስምንት

የአፄ በካፋ እናት የመነኩሴዎች ገረድ ነበረች፡፡ አፄ በካፋም የተወለደው ጃኒካው በሴት ገዳም ውስጥ ነው፡፡ ያው አፄ በካፋም ቅማንት ነው፡፡ ያኔ ሞኒና የሚባል ቦታ ንጉስ ነበር፡፡ ከዚያ ንጉሱ ሞኒና ቆይተው ጃኒካ ሲመጡ ገረዲቱ እግር እጠቢ ተብላ ብትሄድ ሰውየው ተኛት፡፡ ከዚያም በካፋ ተወለደ፡፡ በካፋ የተባለበትም ምክንያት ለከፍካፋ ተብሎ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩ መሪዎች ባጠቃላይ ዲቃላዎች ናቸው፡፡

## ተረክ አርባ ዘጠኝ

ደምበቃ የሚባል ሰው ነበር፡፡ መጀመሪያ ደምበቃ፣ ዳንበቃ ማለት ትልቅ ለምለም ዛፍ አለ፤ አርማጭሆና ጠገሬ ሲጋደሉ እዚያ ዛፍ ዙሪያ ይታረቃሉ፡፡ የታረቁትም ሰዎች ወደ መቶ ይደርሱ ነበር፡፡ ከዚያ ደም ከዚህ በኋላ አይኑር በሚል ደምበቃ ተባለ፡፡

## ተረክ ሃምሳ

አንድ አባይ ጠንቋይ እንዲሁ ይገፋል፡፡ ከዚያ ካንድ ንጉስ ይከሰሳል፡፡ ንጉሱ፣ "ምን እድርገው ነው?" ቢል፣ "ትከፍላለህ አትከፍልም እያለ ሰው ሁሉ እየገፈፈ እያፋታ ነው፡፡" አሉት፡፡ "አምጣና እሠርልኝ" አለ ንጉሱ፡፡ ከዚያ አምጥተው አሠሩት፡፡ ከዚያ፣ "ንጉሱ ለመሆኑ አዋቂ ነው የሚባል?" ብሎ ይጠይቃል፡፡ "አዎን"፡፡ ከዚያ ይሄድና፣ "አንተ እኔ የምሞትበትን ታውቃለህ?" ቢለው፣ "አዎን እንዴታ!" አለ፡፡ "መቼ ነው?" ቢለው፣ "እኔ

በሞትኩ በነገው" ከዚያ ንጉሱ፣ "እየው ጐበዝ ገበሬን ብንገለው በረሃብ ስለምንሞት ይህን ሰው እንልቀቀው፡፡" ብሎ አሠናበተው አሉ፡፡

## ተረክ ሃምሳ አንድ

ግብረሰላም አርገህ ቄስን ትጠራዋለህ፡፡ አጅሬ ቄስ ይመጣና ይጠጣል፤ ይበላል፡፡ አንተ ደግሞ ማታ አማቾችህን እጠራለሁ ብለሃል፡፡ ጠላው አነስም ሲልህ አንድ አራት ጋን ጠላ ሲቀርህ ቆጠብ ታደርጋለህ፡፡ ቄስ ደግሞ እዚያ ቤት ምን ያህል እንደተጠመቀ ሹክ ተብሏል፤ ያውቃል፡፡ ያው ካሳላፊው ጋር ተሻርኮ ነው የሚያውቀው፡፡ "ጠላው የጠላትህ ይሁን አሳላፊው ወዳጅህ ይሁን" ነው የሚባለው መቼም፡፡ ከዚያ ቄሱ፣ "ናስቲ" ይልና አሳላፊውን፣ "እዚህ ቤት ስንት ቄስ፣ ስንት ዲያቆን፣ ስንት መነኩሴ አለ?" ቢለው፣ "አንድ ሁለት መነኩሴዎች ሦስት ዲያቆኖችና አራት ቄሶች አሉ፡፡" ይለዋል፡፡ አራት ቄስ፣ አራት ጋን ጠላ ማለት ነው፤ ሦስት ዲያቆን ሦስት ኮረችራ ማለት ነው፡፡ ከዚያ እነዚህን ለማምጣት ስልት ይፈጠራል፡፡ የቀኑ እንግዳ ተሸኝቷል የማታው እንግዳ አማምቻው ነው የቀረው፡፡ ከዚያ በዜማ

"ኧኧኧኧ... ይህ ጠላ መጣሙ
አምጡና ድገሙ
ጠላ ና ወዲህ ጠላ ና ወዲህ
አንተም እንዳትመጣ እጅ እግር የለህ
እኔም እንዳልመጣ ከሰው ማጀት ነህ
መኖር ክፉ ሰው ነው ትሸብታለህ
በመስቀሉ ባርከን እንቀዳድስህ
ሴቱ እማወራ ከሚያረክስህ
በመስቀሉ ባርከን እንቀዳድስህ"

ይላል ቄስ ሁሉ፡፡ ከዚያ እውነቱን ነው ይባልና አንድ ጋን ጠላ ቱግ ይላል፤ ይጠጣል፡፡ አሁንም እሱ ሲያልቅ ይዘመራል፤ ደግሞ ይመጣል፡፡ ከዚያ በዚህ መንገድ ቄስ ያለውን ጠላ ሁሉ ጥርግርግ አድርጎ ጠጥቶ ሄደ ይባላል፡፡

## ተረክ ሃምሳ ሁለት

"ይህን ውሃ ምን ያጮኸዋል?" ቢለው፣ "በውስጡ ያለው ድንጋይ አለ አሉ፡፡" አንዱ ሰው እኛ ጋር በሬ ይጠፋዋል፡፡ በሬውን የሠረቀውንም ያውቀዋል ግን በህግ እንዳይጠይቅ መረጃ የለውም፡፡ ከዚያ ሌሊት ይገባና እሱም ይሠርቀዋል ከዚያም ሽማግሌ ያን በሬ ሳይሆን የሚያየው ከሆዱ ያለውን ድንጋይ ነው፡፡ ከሌሎች ሰዎች የተለየ ለምን እሱን ጠረጠረው ሳያየው ብሎ ሽማግሌ ይመረምራል፡፡ ምክንያቱም የቀደመ በደል ስለነበረበት ነው፡፡ ይልና ሽማግሌ ይጠይቃል አዎ ሠርቆ መደራደር ህግ አልሠራ ሲል ነው፡፡

## ተረክ ሃምሳ ሦስት

ጐንደር ውስጥ አንድ ሌባ ነበር፡፡ የሚሠርቀውም በግ ነው፡፡ እህኔ (ተረቱን ሲያወሩኝ ደንገዝገዝ ብሏል፡፡) ቤቱን ያያል፡፡ ይወጣና ዙሪያውን አይቶ ካንዱ ጉረኖ ይገባና በጉን ተሸክሞ ማታ ወስዶ ካንዷ ሴት አዳሪ ቤት ያሳድርና አርዶ ቀን ወጡን እየሰራ ይሸጣል፤ይባላል፡፡ ከዚያ አንድ ቀን አንድ ቤት ይገባና በግ አገኘሁ ብሎ ወደል ውሻ ተሸክሞ ገባ አሉ፡፡

## ተረክ ሃምሳ አራት

አማኒ የሚባል ረጅም እድሜ የኖረ አንድ ባሪያ ነበር፡፡ አንዴ አሳዳሪው ይሞትና ለልጁ ያድራል፡፡ ከዚያ ሌሎች ሊወስዱት ያስቡና ጠላ እያጠጡ፣ "እከሌ ሞተ ከዚያም ልጁ እከሌ ወረሰህ" "አዎ" "አሁን እሱ ቢሞት ደግሞ ማን ይወርሰሃል?" ቢሉት፣ "የዚህ አለም ሰው ጨርሶ ሞኝ ነው እንዴ? መቼ ነው የሚሠለጥነው? ምነው እኔ መሞት አላውቅም እንዴ? አለ ይባላል፡፡

## ተረክ ሃምሳ አምስት

አንዴ አማኒ ነው ይሞትና ሁለት በሮች ነበሩት በሮቹ ለእዝን ይታረዳሉ፡፡ ያን ያየ አልፎ ሂያጅ መንገደኛ፣ "አይ የዚህ ሀገር ሰው ሁለት ጥፋት አይ ጉድ!" ይላል፡፡ "ምነው?" ቢሉት፣ "ሰውየው መሞቱ ሳያንስ ደግሞ በሮቹም መሞታቸው፡፡" አለ አሉ፡፡

# ተረክ ሃምሳ ስድስት

አፄ ቴዎድሮስ ደረስጌ ማርያም ላይ ሊነግሱ ሲሉ ንጉስ ሚካኤልን ከማረኩ በኋላ፣ "አይ እርስዎ ሊነግሱ አይችሉም የንጉስ ዘር አይደሉም" ተብለዋል። የንጉስ ዘር የሚባለው የሰለሞን ዘር በንግስት ሳባ የሚፈጠር የሴም ዘር ያለው አማራ ወይ ትግሬ ነው። እሳቸው ደግሞ ያኔ መንገስ አይችሉም መባላቸው የሴም ዘር ስላልሆኑ ነው። ነገር ግን እንዳይነግሱ የሚከለክላቸው ሃይል ስላልነበረ እንደአማራጭ የተወሰደው፣ አፄ ቴዎድሮስ የሚባል ሰው ከሠለሞን ዘር ውጪ የሆነ ይነግሳል እሱም ሀገሪቱን አንድ አድርጎ ይገዛል የሚል ንግር ስለነበር በዚያ ስም ይንገሱ ተብለው ነው የነገሱት።

# አባሪ ሁለት

## የመረጃ አቀባዮች

### 2.1 ቃልፍ የመረጃ አከባዮች

| ተራ ቁጥር | የመረጃአቀባዩ ሙሉስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያስፍራ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወንበር ሙሉነህ መርሻ | 82 | ወ | ጭልጋ (ተበርሚካኤል) | የህገልቦና ሀይማኖት መሪ |
| 2 | ቄስ አማረ ሙሉነህ | 45 | ወ | ጭልጋ (ተበርሚካኤል) | የህገልቦና ሀይማኖት ቄስ |
| 3 | አቶ ተስፋ አቦ | 40 | ወ | ጭልጋ (ተንብሬ) | ግብርና |
| 4 | አቶ አበራ ታከለ | 74 | ወ | ትክልድንጋይ | የመንግስት ስራ |
| 5 | ወ/ሪት ዘመናይ አበራ | 22 | ሴ | ትክልድንጋይ | የመንግስት ስራ |
| 6 | ወ/ሮ ማታ ችኮል | 48 | ሴ | ትክልድንጋይ | አነስተኛ ንግድ |
| 7 | አቶ ስዩም ወንድይፋሪው | 47 | ወ | ጭልጋ (አይከል) | የኔብጤ |
| 8 | አቶ ካሳ በለጠ | 69 | ወ | ትክልድንጋይ | ንግድ |
| 9 | መቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ | 52 | ወ | ጭልጋ (አይከል) | የመንግስት ስራ |
| 10 | አቶ አስራት ቢለው | 62 | ወ | ትክልድንጋይ | ንግድ |
| 11 | ወ/ሮ የሺእመቤት ይርዳው | 59 | ሴ | ጭልጋ (አይከል) | የቤት እመቤት |
| 12 | ወ/ሮ አቡኔ ነጋ | 65 | ሴ | ጭልጋ | የቤት እመቤት |
| 13 | መ/ር አለማየሁ በላይ | 23 | ወ | ጭልጋ (አይከል) | የመንግስት ስራ |
| 14 | ቄስ አየልኝ ተሰማ | 76 | ወ | ጭልጋ (አርሁናጊዮርጊስ) | ቅስና |
| 15 | አቶ ዘርጋው ነገሰ | 55 | ወ | ትክልድንጋይ | ንግድ |
| 16 | አቶ አበይ መኮንን | 90 | ወ | ከርከር (ማንጌ) | ተጠዋሪ |

2.2 ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አከባዮች

| ተራ ቁጥር | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያስፍራ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ነጋ ጌጤ | 63 | ወ | ጎንደር | የዘመናዊ መድሃኒት ንግድ |
| 2 | አቶ አዲሱ ታረቀኝ | 42 | ወ | ጎንደር | የመንግስት ስራ |
| 3 | አቶ ደረጀ ወርቃየሁ | 29 | ወ | ጎንደር | የመንግስት ስራ |
| 4 | አቶ አወቀ አስማረ | 47 | ወ | ጎንደር | የመንግስት ስራ |

# መግለጫ

ይህ ጥናት የእኔ ወጥ ሥራ ሲሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኳቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

____________________________

ስም

____________________________

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ታህሳስ 2005 ዓ.ም

# የፎቶ አባሪ



አጥኚውና አቶ
አበይ መኮንን



በግራ በኩል አቶ አበራ ታከለ፣ በመካከል አጥኚው፣ በቀኝ በኩል



አጥኚውና አቶ አየልኝ ተሰማ



አጥኚውና ወ/ሮ አቡኔ ነጋ



አጥኚውና አቶ ነጋ ጌጤ




DG
7
ALCIO